
# ኤዱኬሽን ፎር
# ሰስተነብል ዲቨለፕመንት

## ሞጁል አንድ

# የልጆች ስነ-ባህሪ
# Child Psychology




## የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን
## ስልጠና ሞጁል

ጥቅምት 2004 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ESD

# ኢዱኬሽን ፎር ሰስተነብል ደቨሎኘመንት

## የልጆች ስነ-ባህሪ

## Child Psychology

## የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን ስልጠና ሞጁል

**አማካሪ ፡** ፍሮምሲስ የትምህርትና ስልጠና አ.ማ

**አዘጋጅ ፡** ዮሴፍ ሹሜ

## ምስጋና

ይህ ሞጁል የተዘጋጀዉ በፍሮምሲስ  የትምህርትና ስልጠና አ.ማ እና በኢዱኬሽን ፎር ሰስተነብል ዲቨለፕመንት ትብብር ሲሆን ለዚህም  ማህበሩ ለኢዱኬሽን ፎር ሰስተነብል ዲቨለፕመንት ከፍ ያለ ምስጋና ያቀርባል። በተለይም በፍሮምሲስ  የትምህርትና ስልጠና አ.ማ ስር ሆነዉ በሞጁል ዝግጅትና በስልጠ በየሞያ ዘርፋቸዉ አስተዋፅኦ ያደረጉትን ባለሙያዎች ከልብ ያመሰግናል ።

በመጨረሻም የኢዱኬሽን ፎር ሰስተነብል ዲቨለፕመንት ሰራተኛች ለስልጠናዉ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን በማስተካከል ስልጠናዉ የተሳካ እንዲሆን ላደረጉት አስተዋፅኦ ማህበሩ  ምስጋናዉን ያቀራባል።

ESD

# ማዉጫ

ገጽ


ምስጋና ........ iii

መግቢያ ........ vi

ምዕራፍ አንድ ........ 2

የስነ-ባህሪ መሰረታዊ ሃሳቦች ........ 2

1.1 የስነ-ባህሪ ትርጉም ........ 2

1.2 ተፈጥሮና አካባቢ በባህሪ ላይ ያላቸው ሚና ........ 3

1.3 የልጆች ስነ-ባህሪ ትርጉምና አስፈላጊነት ........ 4

1.4 የልጆች ባህሪ ሳይንሳዊ የማጥኛ ዘዴዎች ........ 5

1.5 የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ መለማመጃ ጥያቄዎች ........ 9

**ምዕራፍ ሁለት** ........ 11

የሰው ልጅ የመዳበር ሂደት ........ 11

1.6 የቁልፍ ቃላቶች ትርጓሜ ........ 11

1.7 የመዳበር ገፅታዎች ........ 13

1.8 የመዳበር መርሆዎች ........ 14

1.9 መሰረታዊ የመዳበር እውነታዎች ........ 14

1.10 የሰው ልጅ አብይ የመዳበር ወቅቶች ........ 17

1.11 የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ መለማመጃ ጥያቄዎች ........ 18

**ምዕራፍ ሶስት** ........ 20

የቅድመ ልደት የመዳበር ወቅት ........ 20

1.12 የቅድመ-ልደት የመዳበር ወቅት ንዑሳን ክፍሎች ........ 21

1.13 በቅድመ-ልደት በፅንሱ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች ........ 22

1.14 የቅድመ-ልደት የመዳበር ወቅትን ማጥናት አስፈላጊነት ........ 24

1.15 የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ መለማመጃ ጥያቄዎች ........ 25

ምዕራፍ አራት ........ 27

የድህረ-ልደት የመዳበር ወቅት ........ 27

1.16 የጨቅላነት ወቅት ........ 28

1.17 የሕፃንነት ዕድሜ ወቅት ........ 29

1.17.1 የሕፃንነት የመዳበር ወቅት ዋና ዋና ባህሪያት ........ 29

1.17.2 የህፃንነት ወቅት የአካል መዳበር ........ 31

1.17.3 የህፃንነት ወቅት የእንቅስቃሴ መዳበር ........ 31
1.17.4 የሕፃንነት ወቅት አእምሮአዊ መዳበር ........ 32
1.17.5 የሕፃንነት ወቅት የቋንቋ መዳበር ........ 33
1.17.6 የሕፃንነት ወቅት የኃይል-ስሜት መዳበር ........ 35
1.17.7 የሕፃንነት ወቅት ማኅበራዊ መዳበር ........ 37
4.2.8 የሕፃንነት ወቅት የስነ-ምግባር መዳበር ........ 37
1.18 ቀዳማይ የልጅነት ወቅት ........ 38
1.18.1 የቀዳማይ የልጅነት ወቅት ባህሪያት ........ 38
1.18.2 የቀዳማይ የልጅነት ወቅት አካላዊ መዳበር ........ 39
1.18.3 የቀዳማይ የልጅነት ወቅት የእንቅስቃሴ መዳበር ........ 41
1.18.4 በቀዳማይ የልጅነት ወቅት አእምሮአዊ መዳበር ........ 42
1.18.5 የቀዳማይ የልጅነት ወቅት የቋንቋ መዳበር ........ 43
1.18.6 የቀዳማይ የልጅነት ወቅት ኃይለ ስሜት መዳበር ........ 48
1.18.7 የቀደማይ ልጅነት ወቅት ማኅበራዊ መዳበር ........ 49
1.18.8 የቀዳማይ የልጅነት ወቅት የስነ-ምግባር መዳበር ........ 52
1.18.9 በልጅነት ዘመን የሚከሰቱ የባህሪ ችግሮች ገፅታና የማሻሻያ ዘዴዎች ........ 59
1.18.10 ለልጆች ትምህርት ስኬታማነት የሚረዱ መሰረታዊ ጉዳዮች ........ 73
1.19 የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ መለማመጃ ጥያቄዎች ........ 81
ማጠቃለያ ........ 82
ዋቢ መጻሕፍት ........ 84
አባሪዎች ........ 85
1.20 አባሪ - 1፡ የየምዕራፎቹ ማጠቃለያ መለማመጃ ጥያቄዎች መልስ ........ 85
1.21 አባሪ - 2፡ የአካላዊ እንቅስቃሴ መዳበር ምልከታ መከታተያ ቅጽ ........ 87
1.22 አባሪ - 3፡አካባቢን የማወቅና የመረዳት ግንዛቤ መዳበር ምልከታ መከታተያ ቅጽ ........ 88
1.23 አባሪ - 4፡የማኅበራዊና ስሜታዊ ክንዋኔ መዳበር ምልከታ መከታተያ ቅጽ ........ 89

## መግቢያ

የልጆች ስነ-ባህሪ ሞጁል ሰልጣኞች የስነ-ባህሪን መሰረታዊ ሃሳቦችንና የሰው ልጅ የመዳበር ሂደትን እንዲረዱ ያግዛል፡፡ በተለይም የቀዳማይ የልጅነት ወቅት ባህሪያትንና በዚህ የመዳበር ወቅት የሚታዩ የአካል፣ የእንቅስቃሴ፣ የግንዛቤ፣ የቋንቋ፣ የኃይል-ስሜት፣ የማኅበራዊ ሕይወትና የስነ-ምግባር ለውጦችን እንዲያውቁና ለትምህርት ያላቸውን እንደምታ እንዲረዱ ያስችላል፡፡

ይህ የስልጠና ሞጁል በአራት ምዕራፎች የተከፈለ ሲሆን ምዕራፍ አንድ የስነ-ባህሪ መሠረታዊ ሃሳቦችን ይገልፃል፡፡ ምዕራፍ ሁለት የሰው ልጅ የመዳበር ሂደትን ይተነትናል፡፡ ምዕራፍ ሶስት የቅድመ-ልደት የመዳበር ወቅትን ይገልፃል፡፡ በመጨረሻም ምዕራፍ አራት የድህረ-ልደት የመዳበር ወቅትን ያብራራል፡፡

ለሰልጣኞች እንዲረዳ አጠቃላይ የሞጁሉ ዓላማዎችና የየምዕራፎቹ ዓላማዎች እንዲካተቱናየተደረገ ሲሆን በተጨማሪም ጥያቄዎችና ተግባራቱም ከዓላማዎቹ ጋር እንዲተሳሰሩ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ይህን ሞጁል በጥንቃቄ በማንበብ ተግባራቱንና ጥያቄዎቹን በአግባቡ ስሩ፡፡የየምዕራፎቹ ማጠቃለያ መለማመጃ ጥያቄ መልሶች በሞጁሉ መጨረሻ ክፍል አባሪ ተደርገዋል፡፡ ስለዚህ እነኝህን መለማመጃ ጥያቄዎች ከሞከራችሁ በኋላ መልሶቻችሁን አባሪ ከተደረገው መልስ ጋር በማነፃፀር በምዕራፉ ውስጥ የተካተቱትን ይዘቶች ምን ያህል እንደተረዳችሁ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ እነዚህን መለማመጃ ጥያቄዎች መስራት በስልጠናው ውጤታማ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡

### የሞጁሉ ዓላማዎች

ሰልጣኞች ይህንን ሞጁል ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የስነ-ባህሪን ትርጉም ይገልፃሉ፤
- የልጆች ስነ-ባህሪ ትረጉምና አስፈላጊነትን ይገነዘባሉ፤
- የልጆች ባህሪን ሳይንሳዊ የማጥኛ ዘዴዎች ያብራራሉ፤
- የሰው ልጅ መዳበር መሰረታዊ ሃሳቦችን ይለያሉ፤
- የልጆች መዳበር መርሆዎችን ይገልፃሉ፤
- ተፈጥሮና አካባቢ በባህሪ ላይ ያላቸውን ሚና ያብራራሉ፤

- የሰው ልጅ የመዳበር ዘርፎችን ይተነትናሉ፤
- የቅድመ ልደት የመዳበር ወቅትን ንዑሳን ክፍሎች ባህሪያት ይዘረዝራሉ፤
- የጨቅላነት የመዳበር ወቅት ዋና ዋና ባህሪያትን ይገነዘባሉ፤
- የሕፃናትን የአካል፣ የእንቅስቃሴ፣ የግንዛቤ፣ የቋንቋ፣ የማኅበራዊ ሕይወትና የስነ-ምግባር መዳበር ይገልፃሉ፤
- የቅድመ ትምህርት ቤት ዕድሜ ልጆችን የአካል፣ የእንቅስቃሴ፣ የግንዛቤ፣ የቋንቋ፣ የማኅበራዊ ሕይወትና የስነ-ምግባር መዳበር ይለያሉ፤
- በቀዳማይ የልጅነት ወቅት ጨዋታ ለዕድገት ያለውን አስተዋጽዖ ይገልፃሉ፤
- በልጅነት ዘመን የሚከሰቱ የባህሪ ችግሮች ገጽታና የማሻሻያ ዘዴዎች ያብራራሉ፤
- ለልጆች ትምህርት ስኬታማነት የሚረዱ መሰረታዊ ጉዳዮች ይዘረዝራሉ።

## ምዕራፍ አንድ

## የስነ-ባህሪ መሰረታዊ ሃሳቦች

**መግቢያ**

ይህ ምዕራፍ የስነ-ባህሪ መሰረታዊ ሃሳቦች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ምዕራፉ በተለይም የስነ-ባህሪ ትርጉም፣ ተፈጥሮና አካባቢ በባህሪ ላይ ያላቸውን ሚና፣ የልጆች ስነ-ባህሪ ትርጉምና አስፈላጊነት እና የልጆች ባህሪን ሳይንሳዊ የማጥኛ ዘዴዎች ይገልፃል፡፡በምዕራፉ ሰር ያሉ እርዕሶችን ግልፅ ለማድረግ የተለያዩ ምሳሌዎች ተካተዋል፡፡የመለማመጃ ጥያቄዎችና ተግባራትም ከምዕራፉ ዓላማዎቹ ጋር እንዲተሳሰሩ ተደርገው ቀርበዋል፡፡

**የምዕራፉ ዓላማዎች**

ሰልጣኞች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የስነ-ባህሪን ትርጉም ይገልፃሉ፡፡
- ተፈጥሮና አካባቢ በባህሪ ላይ ያላቸውን ሚና ይለያሉ፡፡
- የልጆች ስነ-ባህሪ ትርጉምና አስፈላጊነት ያብራራሉ፡፡
- የልጆችን ባህሪ ሳይንሳዊ የማጥኛ ዘዴዎች ይዘረዝራሉ፡፡

### 1.1 የስነ-ባህሪ ትርጉም

ስነ-ባህሪ ማለት ምንድነው?

____________________________________________________________

______________________________________________

____________________________________________________________

________________________________________________

የተለያዩ የስነ-ባህሪ ባለሙያዎች ለስነ-ባህሪ የተለያየ ትርጓሜ ሰጥተዋል፡፡ ከነዚህ ትርጓሜዎች ውስጥ ሁለቱ እንደሚከተለው ተገልፀዋል፡፡

- **ስነ-ባህሪ፡-** የሰዎችንና የእንስሳትን ባህሪ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚያጠና ዲስኘሊን ነው፡፡
- **ስነ-ባህሪ፡-**ባህሪንና የአእምሮ አስተሳሰብ ሂደትን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚያጠና ዲስፒሊን ነው፡፡

ከነዚህ የስነ-ባህሪ ትርጓሜዎች የምንረዳው ሁለት ነገሮችን ነው፡፡ የመጀመሪያው ስነ-ባህሪ የሚያጠናው ስለ ባህሪና የአስተሳሰብ ሂደት መሆኑን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የስነ-ባህሪ ባለሙያዎች ባህሪንና የአስተሳሰብ ሂደትን የሚያጠኑት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መሆኑን ነው፡፡

- **ባህሪ፡-** የሰው የአስተሳሰብ፣ አመለካከትና ድርጊት ውጤት ነው፡፡ በቀጥታ ሊቃኝ፣ ሊመዘገብና ሊለካ የሚችል ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሊታወቅ የሚችል ሊሆን ይችላል፡፡

**የስነ-ባህሪ ግቦች**

የስነ-ባህሪ ግቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ባህሪን መግለጽ፤
- የሰውን ባህሪ በተለያየ የእድሜ ክልልና ሁኔታ መግለጽ፡፡
- የተለያዩ ባህሪያትን መንስኤ ማብራራት፣
- ወቅታዊ የባህሪን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የወደፊቱን መተንበይና፤
- ባህሪን ማሻሻል (ማስተካከል) ናቸው፡፡

የሰው ልጅ መልካምና መልካም ያልሆኑ ባህሪያትን ሊያጎለብት ይችላል፡፡ መልካም ያልሆነውን ባህሪ በተለያዩ የስነ-ባህሪ ዘዴዎች መለወጥ ሌላኛው የስነ-ባህሪ ግብ ነው፡፡

**ተግባር 1**

አራቱን የስነ-ባህሪ ግቦች በምሣሌ አስደግፋችሁ ግለፁ፡፡

## 1.2 ተፈጥሮና አካባቢ በባህሪ ላይ ያላቸው ሚና

የሰው ልጅ ባህሪ የውርስ (heredity) እና የአካባቢ (environment) የጋራ ውጤት እንደሆነ የተለያዩ የስነ-ባህሪ ባለሙያዎች ይገልፃሉ፡፡ይህ ጉዳይ በስነ-ባህሪ ጠበብቶች ዘንድ ለብዙ አመታት አከራካሪ የሆነ ርዕስ ነበር፡፡ አንዱ ወገን ባህሪ መሠረቱ ተፈጥሮ (nature) ወይም ውርስ (heredity) ነው ሲል፤ ሌላው ወገን ደግሞ አካባቢ (nurture or environment) ነው ይላል፡፡ በዚህ ዙሪያ (nature-nurture controversy) ብዙ ምሁራን በክርክር ጊዜያቸውን መስዋዕት አድርገዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በዚህ ጉዳይ ላይ የተደረሰበት ስምምነት ተፈጥሮና አካባቢ ሁለቱም ለባህሪ መዳበር አስተዋጽኦ እንዳላቸው ነው፡፡ ይህ ማለት አንድ ሰው በተፈጥሮ የያዘው (ያገኘው) እና የሚያድግበት አካባቢ ለባህሪ መዳበር የየራሳቸው አስተዋጽኦ አላቸው ማለት ነው፡፡

## 1.3 የልጆች ስነ-ባህሪ ትርጉምና አስፈላጊነት

### ሀ. የልጆች ስነ-ባህሪ ትርጉም

የልጆች ስነ-ባህሪ የልጆችን ስነ-ህይወታዊ፣ ማኅበራዊ፣ አእምሮአዊና ኃይል-ስሜታዊ ለውጦች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚያጠና የስነ-ባህሪ ዘርፍ ነው (Hetherington and Parke, 1986)፡፡

የልጆች ስነ-ባህሪ ባለሙያዎች በተለይ ሁለት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡ የመጀመሪያው ልጆች እየጎለበቱ ሲሄዱ እንዴት ይለወጣሉ? ሁለተኛው ደግሞ እነኝህን ለውጦች የሚወስኑ ጉዳዮች ምንድን ናቸው? የሚሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም የልጆች ስነ-ባህሪ የልጆችን መዳበር ለውጦች መግለጽና መንስኤዎቻቸውን ማብራራትን ያካተተ መሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ያሰምሩበታል፡፡

### ለ. የልጆች ስነ-ባህሪ አስፈላጊነት

የልጆች ስነ-ባህሪን ማጥናት ያስፈለገበት ምክንያት፡-

- የጥናት ውጤቶች ዘገባ በአብዛኛው እንደሚያመለክተው የልጅነት ዘመን ለተከታዮቹ የሰው ልጅ የዕድገት ዘመኖች መሠረት ወሳኝ መሆኑን ነው፡፡ በዚህም የተነሣ **"የዛሬው ልጅ የነገው ጎልማሳ አባት ነው"** ይባላል፡፡ ይህ አባባል በልጅነት ዘመን የሚቀረፁ ባህሪያት በጉርምስናና በጎልማሳነት ዘመን ለሚታዩ የባህሪ ገፅታዎች አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ያመለክታል፡፡ ስለሆነም የስነ-ባህሪ ባለሙያዎች ሰው በልጅነቱ ዘመን የሚያካብተውን ልምድ፣ የዕድገትና የባህሪ ለውጦች ሂደት በመመርመር እንድናውቀው ያደርጋሉ፡፡
- የልጅነት የመዳበር ሂደትን በማበልፀግ፣ በመግታት ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ የአስተዳደግ ስልቶችንና ሌሎች አካባቢያዊ ተፅዕኖዎች በማጤን እንዲታወቁ ያደርጋሉ፡፡ ይህም ግንዛቤ ሁኔታዎች ከመበላሸታቸውና ከቁጥጥር ውጪ ከመሆናቸው በፊት ለመከላከልና ተገቢ እርምጃዎች ለመውሰድ ይረዳሉ፡፡
- በልጅነት ዘመን አእምሮ ውስጥ የተቀረፀ በጎም ሆነ መጥፎ አስተሳሰብና ልምድ በጉርምስና ወይም በጎልማሳነት ዘመን ለማስወገድ አዳጋችና እልህ አስጨራሽ መሆኑን ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ስለዚህ ይህን እምቡጥና ለጋ የልጅነት ዘመን ለማበልፀግ፣ ለማራመድና ፈር ለማስያዝ ብሎም ሊከተሉ ከሚችሉ አደጋዎች ለመከላከል ምን መደረግ እንዳለበት የልጆች ስነ-ባህሪ ባለሙያዎች ይገልፃሉ (እንዲታወቅ ያደርጋሉ)፡፡

ስለዚህ ወላጆችም ሆኑ መምህራን ወይም ሌሎች የልጆች አሳዳጊዎች ተገቢውን እንክብካቤ በስርአቱ ለማድረግ እንዲያስችላቸው የልጆችን የመዳበር ሂደት ሕግጋትን መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህን ግንዛቤ በመፍጠር የልጆች ስነ-ባህሪ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

### 1.4 የልጆች ባህሪ ሳይንሳዊ የማጥኛ ዘዴዎች

ጥናትና ምርምር ሳይንሳዊ ዘዴን በመከተል ሰዎች ለችግሮቻቸው ቋሚና ዘላቂ መፍትሄ የሚፈልጉበት መንገድ ነው፡፡ ዳንኤል አንበሴና ፍቅሬ (1994) የጥናትና ምርምር ባህሪያት ከዚህ እንደሚከተለው ገልፀዋቸዋል፡፡

- የጥናትና ምርምር ስራ ችግሮችን በመፍታት ላይ ያተኮረ ነው፡፡
- ጥናትና ምርምር ሳይንሳዊ ይዘት አለው፡፡ ባጋጣሚ ወይም በዘፈቀደ የሚመራ ሳይሆን በውል በተጤነና በታሰበበት ችግር ላይ ያተኩራል፡፡
- የጥናትና ምርምር ግኝቶች አዲስ እውቀት እንዲፈጠር በማስቻላቸው የሰው ልጅ ያለውን እውቀት እንዲያጎለብት ይረዳል፡፡
- ጥናትና ምርምር የሚታዩ ተሞክሮዎችንና ተጨባጭ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ ይንደረደራል፡፡
- ጥናትና ምርምር ተገቢነት ያላቸውን የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች በመጠቀም ከተጠኚዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን በአግባቡ በማደራጀት፣ በመተርጎም፣ በመተንተን፣ ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሣብ ይጠቁማል፣ አዳዲስ ሃሣቦችንና እውቀት ይሰጣል፡፡
- ጥናትና ምርምር ግላዊ ስሜትና ፍላጎትን ማንፀባረቂያ አይደለም፡፡
- ጥናትና ምርምር ትኩረትን የሚሻ ሥራ በመሆኑ እርጋታና ትዕግስትን እንዲሁም ፍላጎትን ይጠይቃል፡፡

የልጆች ባህሪ ማጥኛ ስልቶችን ግለፁ?

________________________________________

________________________________________

የልጆች ባህሪን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለማጥናት የሚከተሉትን የጥናት ዓይነቶች መጠቀም እንችላለን፡፡

**ሀ. አሳሽ /ቃኝ/ ጥናት**

ይህ የምርምር ስልት ችግሮችን ወይም ሁኔታዎችን ጠቅለል ባለ መልኩ የሚዳስስና አጠቃላይ ግንዛቤን የሚሰጥ ነው፡፡ ትምህርታዊም ይሁን ሌሎች ማኀበራዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ መረጃዎችን አሰባስቦ በመተንተን አጠቃላይ እውነታን ማስጨበጥ ያስችላል፡፡ ችግሮችን በጥልቀት ባይመረምርም ወደፊት በጥልቀት ለማጥናት ለሚፈልጉ አጥኚዎች ፍንጭ በመስጠት ረገድ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

**ለምሣሌ** መምህራን አሳሽ ጥናቶችን በሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ማካሄድ ይችላሉ፡፡

- በተማሪዎች ፈጣን የመማር ሁኔታ ላይ ተጽእኖ የሚያደርጉ የመማር-ማስተማር ሂደቶች፤
- የተማሪዎች መውደቅ መንስኤዎች፡፡

**ለ. ውስን ጥናት**

ይህ ስልት የአንድ ሰው፣ ቤተሰብ፣ ትምህርት ቤት፣ ቡደን፣ ማኀበረሰብ ወዘተ ድርጊት ሁኔታ በዝርዝርና ጥልቀት የሚመረምር ስልት ነው፡፡ ውስን ጥናት በግለሰብ ደረጃ ለሚደረግ ጥናት ተገቢ የሆነ ስልት ነው፡፡ ምክንያቱም የአንድን ችግር የተወሰነ ገጽታ በአጭር ጊዜ ውስጥ በጥልቀት ለማጥናት ያስችላል፡፡

**ለምሣሌ** በሚከተሉት ችግሮች ላይ ውስን ጥናቶችን መምህራን ማድረግ ይችላሉ፡፡

- ለተማሪዎች ማርፈድና ከክፍል መቅረት መንስኤው ምንድነው?
- ለአንዳንድ ተማሪዎች ዝቅተኛ ውጤት መንስኤው ምንድነው?

**ሐ. አዛማጅ ጥናት**

የዚህ ዓይነቱ የምርምር ስልት በሁለት ወይም ከሁለት በላይ ጉዳዮች መካከል ያለውን የዝምድና ደረጃ ለማጥናት የሚያገለግል የአጠናን ዘዴ ነው፡፡

በአጠቃላይ መምህራን በአዛማጅ የአጠናን ስልት የሚከተሉትን ርዕሰ ጉዳዮች ማጥናት ይችላሉ፡፡

**ለምሣሌ** . በዕድሜና በቋንቋ ችሎታ መሃከል ያለውን ግንኙነት፤

. በፆታና በባህሪ መሃከል ያለውን ዝምድና፡፡

**መ. ዕድገት ተኮር ጥናቶች**

መምህራን ልጆች በተለያዩ የዕድሜ ደረጃዎች ስለሚኖራቸው አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ ማኀበራዊና ስሜታዊ ዕድገቶች ጠቃሚና አስተማማኝ መረጃ እንዲኖራቸው ይገባል፡፡ ምክንያቱም ስርዓተ ትምህርቱን፣ የማስተማሪያ ስነ-ዘዴዎችን፣ የመርጃ መሣሪያዎችን፣ የመገምገሚያ ስልቶችን ወዘተ ለመምረጥ የተማሪዎችን አጠቃላይ የእድገት ደረጃና ገጽታ መገንዘብ የግድ ይሆናል፡፡

ስለዚህ ልጆቹ በተለያዩ እድሜ ውስጥ የሚያሳዩትን የባህሪ ለውጦች በሚገባ ለመፈተሽ እድገት ተኮር ጥናቶችን ማካሄድ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚህ የጥናት ዘዴ ሁለት ዓይነት የአጠናን መንገዶች አሉ፡፡

**1. በተከታታይ /ለረዥም ጊዜ/ የሚደረግ ጥናት**

በአንድ ወቅት በተመረጡ የጥናት አባላት ላይ እድሚያቸው በጨመረ ቁጥር የሚያሳዩትን የባህሪ ለውጥ ለረዥም ጊዜ ተከታታይነት ባለው መልክ የመመርመር ስልት ነው፡፡ በሌላ

አገላለጽ በአንድ ጉዳይ ላይ በረዥም ጊዜ ሊታይ የሚችለውን ለውጥ ለማጥናት አገልግሎት ላይ የሚውል ስልት ነው፡፡

**ለምሣሌ** የክፍል ደረጃና የማስላት ክህሎትን ግንኙነት ለማጥናት የሚከተሉትን ነጥቦች በቅደም ተከተል ማከናወን ያሻል፤

1ኛ. የአንድን የክፍል ደረጃ ተማሪዎችን መምረጥ /የ1ኛ ክፍል ተማሪዎችን እንውሰድ/፣

2ኛ. 1ኛ ክፍል ላይ ያላቸውን የማስላት ክህሎት መመዘን፣

3ኛ. በየዓመቱ ባሉ ተከታታይ የክፍል ደረጃዎች /2ኛ፣ 3ኛ፣ 4ኛ … ወዘተ./ ቀደም ሲል ከ1ኛ ክፍል የተመረጡትን እነዚህኑ ተማሪዎች የሚያሳዩትን የማስላት ክህሎት መመዘን፣

4ኛ. በመጨረሻም በየክፍል ደረጃው ያሳዩትን የክህሎት እድገት መገምገም፡፡

## 2. አወዳዳሪ ጥናት

በተለያዩ የእድሜ ደረጃ ያሉ ናሙናዎችን በአንድ ወቅትና ሁኔታ ውስጥ የማጥናት ስልት ነው፡፡ ዓላማውም በተለያዩ እድሜዎች የሚታዩትን ባህሪዎች በማነፃፀር ላይ ያተኩራል፡፡ ሁለት ወይም ሦስት ጉዳዮችን ለማነፃፀርም የሚካሄድ የአጠናን ስልት ነው፡፡

**ለምሣሌ** በተለያዩ እድሚዎች የሚገኙ ልጆች የሚያሳዩት የማንበብና የቋንቋ ክህሎትን ማጥናት ይኸውም የ3፣ 4፣ 5፣ 6 እና የ7 ዓመት እድሜ ያላቸውን ልጆች በአንድ ጊዜ በናሙናነት በመውሰድ በእነርሱ ላይ ጥናቱን በአንድ ጊዜ ማካሄድ።

**ተግባር 2**

አንድ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህርት ዕድገት ተኮር ጥናትን በምን በምን ጉዳዮች ላይ ልታጠና እንደምትችል ግለፁ?

**ምልከታ**

የልጆችን ባህሪ ለማጥናት ምልከታ እንደዋነኛ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ያገለግላል፡፡ ምልከታ መረጃን ለመሰብሰብ ከምንጠቀምባቸው መሳሪያዎች አንዱ ነው፡፡ ምክንያቱም ምልከታ ማንበብና መፃፍ ከማይችሉ ልጆችና አዋቂዎች መረጃን ለማሰባሰብ የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡ የሰዎችን ባህሪና ድርጊት ለማወቅና መረጃ ለማግኘት ግልጽ በሆነ መልክ የሚያከናውኑትን ጉዳይ መመልከት መረጃውን መመዝገብ፣ መተርጎምና መተንተን አስፈላጊ ነው፡፡ በትምህርት ቤት ላይ ያተኮረም ጥናት ለማካሄድ የክፍል ምልከታ ጠቃሚ ሚና እንደሚጫወት ይታመናል፡፡

ምልከታ የተለያየ ቅርፆችን መያዝ ስለሚችል በአንድ ጥናት ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን ይረዳል፡፡ አንድ ጥናት ከመጀመሩ በፊት የመጀመሪያ ደረጃ ቅኝት ለማድረግ ምልከታ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ በምልከታ ዙሪያ የሚያጋጥሙትን ችግሮች ለማቃለል ይቻል ዘንድ የሚከተሉትን ነጥቦች ማጤን ያስፈልጋል፡፡

- **ትኩረት**
  
  ተጨባጭነት ከሌላቸው ወይም ስሜታዊ ከሆኑ አስተያየቶችና ዳኝነቶችን ከመስጠት ለመቆጠብና ለመከላከል እንዲቻል ምልከታ በአንድ ጉዳይ ላይ መወሰን ይገባዋል፡፡ ለምሣሌ የክፍል ምልከታ ትርጉም ባለው የማስተማር-መማር ሂደት ላይ በማተኮር የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችሉ ጠቃሚ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ማስቻል አለበት፡፡
- **መስፈርቶችን ማዘጋጀት**
  
  ምልከታ ለማድረግ በቅድሚያ ምልከታው በሚያተኩርባቸው ጉዳዮች ላይ መስፈርቶችን ማዘጋጀት ያሻል፡፡

በምልከታ የሚገኝ መረጃ በሁለት ሊከፈል ይችላል፡፡ ይኸውም በስርዓት የተዘጋጀ መረጃና በስርዓት ያልተዘጋጀ መረጃ በሚል ይታወቃሉ፡፡ በስርዓት ያልተደራጀ መረጃን ለመሰብሰብ እምብዛም በዝርዝር ባልተዘጋጀ የምልከታ ስልት ማካሄድ ይቻላል፡፡ ይህ ስልት ምልከታ አድራጊውን ሰው በፈለገው መልክ መረጃውን ለመሰብሰብና ለመመዝገብ እንዲችል ሙሉ ነፃነትና ኃላፊነት ይሰጠዋል፡፡ በአንፃሩ በዝርዝር የተዘጋጀ የምልከታ ስልት ሥርዓት ያለው አቅጣጫ ጠቋሚና ምልከታው በምን ጉዳዮች ላይ እንደሚያነጣጥር ግልጽ አድርጎ የሚያሳይ በመሆኑ አጥኚው ቀደም ብሎ በተዘረዘሩት ገጽታዎች ላይ ብቻ በምልከታ ወቅት እንዲያተኩር ያስችለዋል፡፡

ሌላው የምልከታ ዘዴዎችን ምልከታ አድራጊው/ዋ/ በሚኖረው/ራት/ ሚና ሊወሰን ይችላል፡፡ ይኸውም ምልከታ አድራጊው/ዋ/ በሁኔታው ውስጥ በሚኖረዉ/ራት/ የተሣትፎ መጠን ይወሰናል፡፡ በምልከታው ሂደት የተሣትፎ መጠኑ በሁለት መልክ ይታያል፡፡ ይኸውም አንደኛው ምልከታው የሚደረግባቸው የቡድን አባላትን በመምሰል ሙሉ ለሙሉ ተሣታፊ ሆኖ ምልከታውን ማከናወን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የቡድኑ አባላት ሳያውቁ ፍፁም ተመልካች በመሆን መረጃን መሰብሰብ ሌላው አቅጣጫ ነው፡፡

በርካታ ምልከታ የሚደረግባቸው ዘዴዎች ቢኖሩም የትኛውን ዘዴ መጠቀም እንዳለብን ለመወሰን ግን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማንሣት ተገቢ ይሆናል፡፡

- የምልከታው ዓላማ ምንድነው?
- ምልከታው በምን ጉዳይ ላይ ያተኩራል?

- የትኞቹን ባህሪያት መመልከት ጠቃሚ ነው?
- የትኛው የምልከታ ዘዴ ዓላማውን እጅግ በተሻለ መልክ ተግባራዊ ለማድረግ ያመቻል?
- የተሰበሰበው መረጃ እንዴት ጥቅም ላይ ይውላል? … ወዘተ ናቸው፡፡

የልጆች የተለያዩ የባህሪያት ገጽታዎችን መዳበር ለመከታተል የሚያስችሉ የምልከታ ቅጾች በሞጁሉ የመጨረሻ ክፍል አባሪ ተደርገዋል፡፡

### 1.5 የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ መለማመጃ ጥያቄዎች

**ክፍል አንድ፡ - የእውነት-ሀሰት ጥያቄዎች**

***መመሪያ፡-***የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥንቃቄ ከአነበባችሁ በኋላ ትክክል የሆኑትን **እውነት**፣ትክክል

ያልሆኑትን **ሀሰት** በማለት ከጥያቄዎች በስተግራ በኩል በተሰጠዉ ባዶ ቦታ ላይ ፃፉ።

________1. የሰው ልጅ ባህሪ የሚወሰነዉ በአካባቢያዊ ጉዳዮች እንደሆነ የተለያዩ የስነ-ባህሪ ባለሙያዎች ይገልፃሉ፡፡

________2. ስነ-ባህሪ የልጆችን ስነ-ህይወታዊ፣ ማኅበራዊ፣ አእምሮአዊና ኃይለ-ስሜታዊ ለውጦች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚያጠና የልጆች ስነ-ባህሪ ዘርፍ ነው፡፡

________3. ጥናትና ምርምር ግላዊ ስሜትና ፍላጎትን ማንፀባረቂያ አይደለም፡፡

________4. አሳሽ ጥናት የአንድን ሰው ባህሪ በዝርዝርና በጥልቀት የሚመረምር የጥናት ስልት ነው፡፡

________5. የልጅነት ዘመን ለተከታዮቹ የሰው ልጅ የዕድገት ዘመኖች መሰረት ወሳኝ ነው፡፡

**ክፍል ሁለት፡- የአጭር መልስ ጥያቄዎች**

***መመሪያ፡*** የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዶ ቦታዎች ላይ ተገቢዉን ቃል ወይም ሃረግ በመሙላት

መልሳችሁን ፃፉ።

6. ባህሪንና የአእምሮ አስተሳሰብ ሂደትን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚያጠና ዲስፒሊን ___________ነው፡፡
7. ከአራቱ የስነ-ባህሪ ግቦች የመጀመሪያው ግብ ባህሪን___________ነዉ።

8. የልጆችን ባህሪ ለማጥናት እንደዋነኛ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የሚያገለግለን_____________ነዉ፡፡

9. የሰው የአስተሳሰብ፣ አመለካከትና ድርጊት ውጤት ___________ነው፡፡

10. የስነ-ባህሪ ባለሞያዎች ባህሪንና የአስተሳሰብ ሂደትን የሚያጠኑበት መንገድ __________ነው፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የሰው ልጅ የመዳበር ሂደት

**መግቢያ**

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የምንመለከታቸው ፅንሰ ሃሣቦች የቁልፍ ቃላቶች ትርጓሜ፤ የመዳበር ዘርፎች፤ የመዳበር መርሆዎች፣ የመዳበር መሰረታዊ እውነታዎች እና የሰው ልጅ አብይ የመዳበር ወቅቶች ይሆናሉ፡፡ በምዕራፉ ሰር ያሉ  እርዕሶችን ግልፅ ለማድረግ የተለያዩ ምሳሌዎች ተካተዋል፡፡የመለማመጃ ጥያቄዎችና ተግባራትም ከምዕራፉ ዓላማዎቹ ጋር እንዲተሳሰሩ ተደርገው ቀርበዋል፡፡

**የምዕራፉ አላማዎች**

ሰልጣኞች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የእድገት፣ ብስለት፣ መማርና መዳበርን ትርጉም ይገልፃሉ፡፡
- የመዳበርን ገጽታዎች ያብራራሉ፡፡
- የመዳበርን መሠረታዊ እውነታዎች ይለያሉ፡፡
- የሰው ልጅ አበይት የመዳበር ወቅቶችን ይዘረዝራሉ፡፡

### 1.6 የቁልፍ ቃላቶች ትርጓሜ

እድገት፣ ብስለት፣ መማርና መዳበርን ከራሳችሁ ልምድ በመነሳት ትርጉማቸዉን ግለፁ ፡፡

______________________________________________________________________-

___________________________________________________________________

______________________________________________________________________

**ሀ. እድገት (Growth)**

እድገት በፍጥረታት ላይ የሚታይ የመጠን ለውጥን ሲሆን አንፃራዊ በሆነ መልክ ሲታይ በቀላሉ መለካት ይቻላል፡፡ **ለምሣሌ** የክብደት፣ የቁመትና የስፋት መጨመር በሜትር ወይም በኪሎ ግራም ሊለካ ይችላል፡፡

### ለ. ብስለት (Maturation)

ብስለት ከዘር ውርስ ወይም በተፈጥሮ የሚወሰን አካላዊና አእምሮአዊ ለውጥ ነው፡፡ አንፃራዊ በሆነ መልኩ ከአካባቢ ተፅዕኖ ነፃ ነው፡፡

- ብስለት በዘር ውርስ የሚከናወን የለውጥ ቅደም ተከተልን ያመለክታል፡፡
- ብስለት በእድሜ አማካኝነት የሚመጣ ለውጥን ያመለክታል፡፡

**ለምሣሌ** የሰው ልጅ ባህሪ የሆኑት እንደ መንጋለል፣ መቀመጥ፣ መዳህ፣ ዳዴ ማለት፣ መቆምና መራመድ የመሳሰሉት ቅደም ተከተላዊ ሂደቶች የብስለት ውጤቶች ናቸው፡፡

### ሐ. መማር (Learning)

መማር በአንፃራዊነት ዘለቄታዊነት ያለው የባህሪ ለውጥ ሆኖ ለውጡ በልምምድና በተሞክሮ የሚመጣ ነው፡፡

- መማር ጊዜያዊ የባህሪ ለውጥን አያጠቃልልም፡፡ ስለሆነም በድካም፣ በሕመምና መድሃኒት በመውሰድ የሚመጣ የባህሪ ለውጥ መማር ውስጥ አይካተትም፡፡
- በእድሜ አማካኝነት የሚመጣ የባህሪ ለውጥ በመማር ውስጥ አይጠቃለልም፡፡

መማር ሰዎች ከአካባቢያቸው ጋር በሚያደርጉት መስተጋብር ምክንያት ወይም በልምድና በልምምድ የሚገኝ የባህሪ ለውጥ ነው፡፡ **ለምሣሌ** መፃፍ፣ ማንበብ፣ መኪና ማሽከርከር፣ መዋኘት እና የመሳሰሉት በመማር የሚመጡ የባህሪ ለውጦች ናቹው፡፡

### መ. መዳበር (Development)

መዳበር የአይነትና የመጠንን ለውጥ በአንድ ላይ አካቶ የያዘ ሲሆን ለውጡ ከውህደት እስከ ሕልፈተ ሕይወት ድረስ ይዘልቃል፡፡

- መዳበር የብስለትና የመማር ወይም የልምድ ውጤት ነው፡፡
- መዳበር እድገትን፣ ብስለትንና መማርን ያካትታል፡፡

**ተግባር 3**

በእድገት፣ ብስለት፣ መማርና መዳበር መካከል ያለውን ልዩነትና አንድነት አብራሩ፡፡

### 1.7 የመዳበር ገፅታዎች

የስነ-ባህሪ ባለሙያዎች የሰው ልጅን መዳበር በጥልቀትና በስፋት ለማጥናት እንዲያስችላቸው መዳበርን በተለያየ ገጽታዎች ለይተውታል፡፡ ዋና ዋናዎቹ የመዳበር ገጽታዎች እንደሚከተለው ተብራርተዋል፡፡

**ሀ. የአካል መዳበር (Physical development)**

የሰውነት ክፍሎች ማለትም ጭንቅላት፣ እጅ፣ እግር፣ ጡንቻ፣ አጥንት፣ ልብ፣ ሳንባ፣ ወዘተ በመጠን፣ በቅርጽና በይዘት የሚያሳዩትን ለውጥ ያመለክታል፡፡ ይህም አካላዊ እድገትን፣ ክብደትና ቁመት መጨመርን፣ የሰውነት መጠንከርንና የስሜት ህዋሳት መዳበርን ያካትታል፡፡

**ለ. የእንቅስቃሴ መዳበር (Motor development)**

አንድ ሕፃን በጀርባው ከመንጋለል አንስቶ ጭንቅላቱን ለመቆጣጠር፣ ለመገልበጥ፣ ለመቀመጥ፣ ለመዳህ፣ ዳዴ ለማለት፣ ለመቆም፣ ለመራመድ፣ በእጅ አንዳንድ እቃዎችን ለመያዝ፣ ለመጨበጥ፣ ወዘተ... የሚፈጽማቸውን ልዩ ልዩ ድርጊቶች የእንቅስቃሴ መዳበር ሂደትን ያመለክታል፡፡

**ሐ. አእምሮአዊ መዳበር (Cognitive development)**

የዕውቀት፣ ቋንቋ፣ አስተሳሰብ፣ ትውስታ እና ሌሎች የአእምሮአዊ ሂደቶች መበልፀግን ያሳያል፡፡ የሰው ልጅ ስለአካባቢው ብሎም ስለ ውስብስቡ ዓለም ለማወቅ፣ ለመገንዘብ፣ ችግሮችን ለመፍታትና አዳዲስ ነገሮችን ለማግኘት የሚያደርጋቸውን አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች የአእምሮ መዳበር ዘርፍን ያመለክታል፡፡

**መ. የቋንቋ መዳበር (Language development)**

ድምፅን ለማውጣት፣ ቃላትን ለመናገር፣ ብሎም ዓረፍተ ነገሮችን በመሥራት ሃሣብን ለመግለጽ የሚደረግን ጥረትና ችሎታ ያመለክታል፡፡ ቋንቋ የሰው ልጅ ፍላጎቱን፣ ስሜቱን፣ ሃሣቡን ለመግለጽና አካባቢውን በመረዳት ከሌሎች ጋር ለመግባባት የሚገለገልበት የመዳበር ዘርፍ ነው፡፡ ይህም የማዳመጥን፣ የመናገርን፣ የማንበብንና የመጻፍን ችሎታ ያካትታል፡፡

**ሠ. የኃይለ-ስሜት መዳበር (Emotional development)**

ውስጣዊ ፍላጎትን፣ ፍቅርን፣ ጥላቻን፣ ደስታን፣ ቅናትን፣ ፍርሃትን፣ ወዘተ. የመግለጽ ሂደትን መዳበር የሚያሳይ ነው፡፡

**ረ. የማኅበራዊ መዳበር (Social development)**

ልጆች ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚያደርጉትን ግንኙነት መቼ እንደሚጀምሩ፣ የመተባበርና አብሮ መሥራትና መኖር ክህሎቶችን እንዴት መማር እንደሚችሉ የሚገልጽ ሃሣብ ነው፡፡

እነዚህ ከላይ የተገለፁት የመዳበር ዘርፎች እርስ በርስ የተዛመዱና የሚደጋገፉ ስለሆኑ ለአንዱ የመዳበር ዘርፍ የምናደርገው ድጋፍ ለሌሎቹም የመዳበር ዘርፎች አስተዋጽኦ ሊኖረው ይችላል፡፡ ለምሣሌ የልጁ የማኅበራዊ ግንኙነት እየሰፋ ሲሄድ የአእምሮ፣ የቋንቋ እንዲሁም የኃይለ -ስሜት የመዳበር ዘርፎች እየዳበሩ ይሄዳሉ፡፡

## 1.8 የመዳበር መርሆዎች

የሰው ልጅ የመዳበር ሂደት ሶስት ዋና ዋና የመዳበር መርሆዎች አሉት (Kaplan, 1986) ፡፡ እነዚህ የመዳበር መርሆዎች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**ሀ. ከላይ ወደታች እድገት (Cephalocaudal law)**

በዚህ የእድገት ሕግ መሠረት የአካል አፈጣጠርና ተግባራዊ ብቃት ከጭንቅላት ይጀምርና ፍፃሜው ከእግር ጣቶች ላይ ይሆናል፡፡

**ለ. ጎናዊ እድገት (Proximodistal law)**

በዚህ የእድገት ሕግ መሠረት እድገት ከቅርብ ወደ ሩቅ ማለትም ከመካከለኛ ቋሚ ዘንግ ጀምሮ ወደ ጎን እስከ እጅ ጥፍራችን ያለው ጎናዊ እድገት ያመለክታል፡፡ ተግባራቱንም በሚመለከት ሂደቱ ከአካላዊ አሰራሩ ጥንካሬው ጋር አብሮ የሚሄድ ነው፡፡ **ለምሣሌ** አንድ ሕፃን አሻንጉሊቱን በጣቶቹ ይዞ ለመጫወት ከመቻሉ በፊት ክንዱን ከዚያም የእጁን መዳፍና ጣቶቹ መጠንከር አለባቸው፡፡ አፈጣጠራቸውም ይህንኑ ሂደት የተከተለ ነው፡፡

**ሐ. እድገት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር መቀጠሉን የሚገልፅ ሕግ (Mass to specific law)**

እድገት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ይቀጥላል፡፡ አእምሮአዊና አካላዊ ድርጊቶች በመጀመሪያው የሕይወት ዘመን ማለትም በቅድመ-ልደትና ድህረ ልደት አጠቃላይ ናቸው፡፡ ሕፃናት ለማንኛውም ውጫዊ መንስኤ ምላሽ የሚሰጡት መላ አካላቸውን በማንቀሣቀስ ነው፡፡ ሕፃናት እያደጉ ሲመጡ ግን ለአንድ ውጫዊ ቀስቃሽ ምላሽ የሚሰጡት የተወሰነ የአካል ክፍላቸውን ብቻ በማንቀሣቀስ ይሆናል፡፡ በዚህ የዕድገት ሕግ መሠረት የሰው ልጅ ትላልቅ ጡንቻዎች ከትናንሽ ጡንቻዎች ቀድመው መጎልበታቸውን ያሳያል፡፡

## 1.9 መሰረታዊ የመዳበር እውነታዎች

የመዳበርን ሂደት ለመረዳት መሰረታዊና ሊተነበዩ የሚችሉ የመዳበርን እውነታዎች ማንሳት ተገቢ ይሆናል፡፡ ኤልዛቤት ሐርሎክ የተባሉ የስነ-ባህሪ ባለሙያ ያብራሩዋቸው አስር የመዳበር እውነታዎች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል (Hurlock, 1980) ፡፡

**ሀ. በልጅነት የዕድገት ወቅት የተጣሉ መሰረቶች ወሳኞች ናቸው፡፡**

አንድ ስለመዳበር ያለው መሠረታዊ እውነታ በልጅነት ዕድሜ የሚገነቧቸው አመለካከቶች፣ ልምዶችና ባሕሪያት አንድ ሰው በሕይወቱ እራሱን ከሚኖርበት ኅብረተሰብና አካባቢ ጋር በከፍተኛ

ደረጃና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲለማመድ ያስችሉታል፡፡ በግልም ሆነ ማኀበራዊ ሕይወቱ እራሱን እያለማመደ እንዲኖር ያስችሉታል፡፡

በልጅነት ዕድሜ የተጣሉ መሰረቶች ቋሚ ሲሆኑ ነገር ግን በአንዳንድ ሁኔታዎች ሊለወጡ ይችላሉ፡፡

- በመጀመሪያ ደረጃ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ለውጥ ሊኖር ካስፈለገ ግለሰቡ እርዳታና አመራር ሊኖረው ይገባል፡፡ ለምሳሌ አንድን ሕፃን ከግራው ይልቅ የቀኝ እጅን እንዲጠቀም ለማስቻል የሚሰጥ ስልጠና ሊሆን ይችላል።
- በሁለተኛ ደረጃ ለውጥ ሊኖርባቸው ከሚችሉ መንገዶች አንዱ በጣም አዋቂ የሆኑ ሙያተኞች ሰልጣኞችን በአዲስና በተለየ መንገድ ሲያሰለጥኑ ነው፡፡
- በሶስተኛ ደረጃ ሊጠቀስ የሚችል ለውጥ የማምጫ መንገድ ለውጡን በሚፈልጉ ሰዎች የሚኖር ጠንካራ ተነሣሽነትና መበረታት ሲኖር ነው፡፡

**ለ. መዳበር የብስለትና የመማር የጋራ ውጤት ነው፡፡**

ብስለትና መማር በመቀናጀት ለመዳበር መፈጠር መንስኤ ስለመሆናቸው በሚከተሉት ሁለት ምክንያቶች መረዳት ይቻላል፡፡

- ሰዎች የመማር ችሎታ አላቸው፡፡ ይህ ችሎታቸው ተመሳሳይ ሳይሆን የአንዱ ከሌላው ይለያል፡፡ ስለዚህ በሰዎች መካከል የሚታዩት የስብዕና፣ የአመለካከት፣ የምርጫ ልዩነቶች የብስለት ወይም የመማር ውጤት ብቻ ሣይሆኑ ይልቁንም የሁለቱ መስተጋብር ውጤት መሆናቸውን መረዳት ይገባል።፡
- ብስለት በተለይ በዘር ከቤተሰብ ወደ ልጅ የሚተላለፉት ባህሪያት አንድ ሰው እስከምን ደረጃ እንደሚያድግና የማደጉም እምርታ እስከምን ድረስ እንደሆነ ይወስነዋል፡፡ ምንም ያህል በጣም ምቹ የሆኑ የመማሪያ ቦታዎችና ዘዴዎች ቢሟሉ ወይም በተማሪው በኩል በጣም ጠንካራ የሆነ የመማር ፍላጎትና ተነሣሽነት ቢኖርም ዕድገቱ ከተወሰነለት ውጪ ሊራመድ አይችልም፡፡
- በሌላ መልኩ ለመማር የተወሰነ የጊዜ ሰሌዳን ማሟላትን ይጠይቃል፡፡ ልጆች በአካልም ሆነ በአእምሮ ለመማር የሚያስችላቸው የብስለት ደረጃ እስኪደርሱ ድረስ ዝግጁ አይሆኑም፡፡ ልጆች ትምህርት ለመጀመር ይቻላቸው ዘንድ የተወሰነ "የዕድገት ዝግጁነትን" ማለፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡

**ሐ. መዳበር ግልፅና ሊተነበይ የሚችል ስርዓትን ይከተላል፡፡**

በሰው ልጅ መዳበር ሂደት ውስጥ በቅደም ተከተል የሚከናወኑ ስርዓትን የጠበቀ የአካል፣ የእንቅስቃሴ፣ የንግግርና የአስተሳሰብ ለውጦች ይታያሉ፡፡

**መ. እያንዳንዱ ሰው አንዱ ከሌላው ይለያል፡፡**

ማንኛውም ግለሰብ በስነ-ፍጥረቱና ከዘር በሚወርሳቸው ባሕሪያት አንዱ ከሌላው ልዩ ነው፡፡ መንታዎች (ከአንድ እንቁላል ተከፍለው የሚፈጠሩት) እንኳ ይለያያሉ፡፡ ይህ አንዱ ከሌላው ልዩ የመሆን ባሕሪ ከሕፃንነት ወደ ጎርምስና እያደግን ስንመጣ ከመቀነስ ይልቅ እየጨመረ እንደሚመጣ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ሁለት ሰዎች በሚኖሩበት ተመሳሳይ አካባቢ ለሚገጥማቸው ሁኔታዎች በተመሳሳይ መንገድ ምላሽ አይሰጡም፡፡ በሌላ አነጋገር ሁለቱ ሰዎች አካባቢያቸውን በተመሳሳይ መልኩ ላይረዱ ወይም ላይገነዘቡ ይችላሉ ማለት ነው፡፡

**ሠ. እያንዳንዱ የመዳበር ወቅት የራሱ ባህሪያት አሉት፡፡**

ሰዎች በቀላሉ እራሳቸውን ከሚኖሩበት ማኀበራዊ አካባቢ ጋር ካለመዱ ወይም የሚጠበቅባቸውን ካሟሉ በግልና ማኀበራዊ ሕይወታቸው ጤናማና ጥሩ ኑሮን ይመሰርታሉ፣ ይመራሉ፡፡ ይህም በአካባቢያቸው ፍላጎትና በእነሱ ችሎታ መካከል ሚዛናዊ ግንኙነት ወይም መጣጣም (Equilibrium) ተፈጥሮአል ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ይህ ሁኔታ ሚዛናዊ ካልሆነ (Disequilibrium) ምናልባትም እራሳቸውን ከአካባቢያቸው ጋር የማላመድ ችግር ከገጠማቸው የግልም ሆነ ማኀበራዊ ሕይወታቸው ደካማ ይሆናል፡፡

**ረ. መዳበር በማነቃቂያ ሊፋጠን ይችላል፡፡**

ልጆችን በቀጥታ በማነቃቃትና በማበረታታት ጤናማ ዕድገታቸውን ማፋጠን ይቻላል፡፡ ማነቃቂያ ውጤታማ የሚሆነው በጤናማ መልኩ እያደገ ያለን ክህሎትና ችሎታ ማበረታታት ሲቻል ነው፡፡ ለምሳሌ እናቶች ወይም ሌሎች ተንከባካቢዎች ያለወቅታቸው የተወለዱ ሕፃናትን የተለያዩ የአካል ክፍሎቻቸውን በማንቀሣቀስ፣ በተለያየ አቅጣጫ በማገላበጥና በማነጋገር ማበረታታት ከቻሉ እነዚህ ህጻናት ምንም ዓይነት የማነቃቂያ ድጋፍ ካላገኙ ሌሎች ሕፃናት ፈጣን ዕድገት ያሳያሉ፡፡ ቤተሰብ በአብዛኛው በቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤት ዕድሜ ውስጥ ያሉትን ልጆች ከአነጋገራቸው ልጆቹ ለመናገር ይጥራሉ፣ አስፈላጊው ድጋፍ ስለሚደረግላቸውም ጠንካራ የሆነ ተነሣሽነት ያሳያሉ፡፡

**ሰ. ባሕላዊ ለውጦች በመዳበር ላይ ተፅዕኖ ያደርጋሉ፡፡**

አንድ ልጅ በሚኖርበት ኀብረተሰብ ውስጥ በየጊዜው ዕድገቱ ከኀብረተሰቡ ባሕል፣ አኗኗርና ልምድ ጋር እንዲጣጣም (እንዲያድግ) ለማድረግ ይቻል ዘንድ እየተገራ፣ እየተስተካከለ መሄድና ማደግ ይገባዋል፡፡ በሌላ አገላለጽ የአንድ ኀብረተሰብ ባሕል፣ ወግና ሥርዓቱ እየተለወጠ ሲሄድ የዜጎችም እውቀት፣ ክህሎት፣ አመለካከት፣ ፍላጎት፣ ምርጫና አስተሳሰብ ከባሕሉ ዕድገት አንፃር መቀየርና ማደግ ይገባዋል፡፡

**ሸ. እያንዳንዱ የመዳበር ወቅት ሊያጋጥሙት የሚችሉ ችግሮች መኖራቸው፣**

**ቀ.** **ከእያንዳንዱ የመዳበር ወቅት ህብረተሰቡ በአባላቱ እንዲያከናውኑ የሚጠብቃቸው ተግባራት መኖራቸው፡፡**

**በ.** **ስለእያንዳንዱ የመዳበር ወቅት ሳይንሳዊ ያልሆኑ እምነቶች መኖራቸው ናቸው።**

### 1.10 የሰው ልጅ አብይ የመዳበር ወቅቶች

የሰው ልጅ የመዳበር ሂደትን በሁለት አብይ ወቅቶች ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ እነዚህም፡-

**ሀ.** **የቅድመ-ልደት የመዳበር ወቅት (Prenatal Development)**

ይህ የመዳበር ወቅት ከውሕደት እስከ ልደት ያለውን የመዳበር ግዜ ይሸፍናል፡፡ ይህም በአማካኝ ሁለት መቶ ሰማንያ ቀናት ይሆናል፡፡ ይህ የመዳበር ወቅት በሶስት ንዑሳን የመዳበር ወቅቶች ይከፈላል፡፡

- i. **የውህድ-ህዋስ ወቅት (Germinal stage)**

  ከውህደት/ፅንሰት እስከ ሁለኛው ሳምንት መጨረሻ ያለውን የመዳበር ወቅት ያጠቃልላል፡፡

- ii. **የፅንስ ወቅት (Embryonic stage)**

  ከሁለተኛው ሳምንት መጨረሻ እስከ ሁለተኛው ወር መጨረሻ ያለውን የመዳበር ወቅት ይሸፍናል፡፡

- iii. **የሽል ወቅት** (Fetal stage)

  ከሁለተኛው ወር መጨረሻ እስከ ልድት ያለውን የእርግዝና ግዜ ይሸፍናል፡፡

**ለ.** **የድህረ-ልደት የመዳበር ወቅት** (Postnatal Development)

ይህ የመዳበር ወቅት ከልደት እስከ ህልፈተ ህይወት ያለውን የመዳበር ጊዜ ይሸፍናል፡፡ ይህ የመዳበር ወቅት በተለያዩ ንዑሳን ወቅቶች ይከፈላል፡፡

- i. **የጨቅላነት ወቅት፡-** ከልደት እስከ ሁለተኛው ሳምንት መጨረሻ ያለውን ጊዜ ይሸፍናል፡፡
- ii. **የሕፃንነት ወቅት፡-** ከሁለት ሳምንት እስከ ሁለት ዓመት ያለውን የመዳበር ጊዜ ይሸፍናል፡፡
- iii. **የቀዳማይ የልጅነት ወቅት፡-** ከሁለት እስከ ስድስት ዓመት ያለውን ጊዜ ይሸፍናል፡፡
- iv. **የዳግኅራይ የልጅነት ወቅት፡-** ከስድስት እስከ አስራ ሁለት አመት ያለውን የመዳበር ጊዜ ይሸፍናል፡፡
- v. **የጉርምስና ወቅት፡-** ከአስራ ሁለት እስከ አሥራ ስምንት አመት ያለውን የመዳበር ጊዜ ይሸፍናል፡፡

vi. **የቀዳማይ የጎልማሳነት ወቅት፡-** ከአስራ ስምንት እስከ አርባ አመት ያለውን የመዳበር ጊዜ ይሸፍናል፡፡

vii. **የመካከለኛ የጎልማሳነት ወቅት፡-** ከአርባ እስከ ስልሳ ዓመት ያለውን የመዳበር ጊዜ ያካትታል፡፡

viii. **የእርጅና ወቅት፡-** ከስልሣ አመት እስከ ህልፈተ-ህይወት ያለውን ጊዜ ይሸፍናል፡፡

## 1.11 የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ መለማመጃ ጥያቄዎች

**ክፍል አንድ፡ - የእውነት-ሀሰት ጥያቄዎች**

***መመሪያ፡***የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥንቃቄ ከአነበባችሁ በኃላ ትክክል የሆኑትን **እውነት**፣ትክክል ያልሆኑትን **ሀሰት** በማለት ከጥያቄዎች በስተግራ በኩል በተሰጠዉ ቦታ ላይ ፃፉ።

________1. መማር ከዘር ውርስ ወይም በተፈጥሮ የሚወሰን አካላዊና አእምሮአዊ ለውጥ ነው፡፡

________2. እድገት በፍጥረታት ላይ የሚታይ የአይነት ለውጥን ያመለክታል፡፡

________3. የሰው ልጅ የመዳበር መርህ መዳበር ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሚያመራ መሆኑን ይገልፃል።

________4. የመዳበር ዘርፎች እርስ በርስ የተዛመዱና የሚደጋገፉ ናቸው፡፡

________5. መዳበር ግልፅና ሊተነበይ የሚችል ስርዓትን ይከተላል፡፡

**ክፍል ሁለት ፡ - የምርጫ ጥያቄዎች**

***መመሪያ፡*** የሚከተሉትን የባለ አራት አማራጭ መልስ ጥያቄዎች በጥንቃቄ ከአነበባችሁ በኃላ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመክበብ መልሱ።

6. ከሚከተሉት ውስጥ የአይነትና የመጠን ለውጥን በአንድ ላይ አካቶ የያዘው ቃላት የትኛው ነው?

ሀ) መማር ለ) መዳበር ሐ) ብስለት መ) እድገት

7. የሰው ልጅ ፍላጎቱን፣ ስሜቱንና ሃሣቡን ለመግለጽና አካባቢውን በመረዳት ከሌሎች ጋር ለመግባባት የሚገለገልበት ________ የመዳበር ዘርፍ ነው፡፡

ሀ) የአካል ለ) የእንቅስቃሴ ሐ) የቋንቋ መ) የኃይል-ስሜት

8. መዳበር ከቅርብ ወደ ሩቅ የሚቀጥል መሆኑን የሚገልፀው ህግ________ ነው፡፡

ሀ) ጎናዊ  እድገት

ለ) ከላይ ወደ ታች እድገት

ሐ) ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር እንቅስቃሴ  እድገት

መ) ሁሉም መልስ ናቸው

9. ከሚከተሉት ውስጥ የመዳበር መሰረታዊ እውነታዎች ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ) መዳበር በማነቃቂያ ሊፋጠን ያለመቻሉ፡፡

ለ) መዳበር የብስለትና የመማር የጋራ ውጤት ነው፡፡

ሐ) መዳበር ግልፅና ሊተነበይ የሚችል ስርዓትን ይከተላል፡፡

መ) በመዳበር ወቅት ሊያጋጥሙት የሚችሉ ችግሮች መኖራቸው፡፡

10. ከሚከተሉት የድህረ ልደት የመዳበር ወቅቶች ውስጥ በጣም አጭር ጊዜ የሚሸፍነው የቱ ነው?

ሀ) የሕፃንነት ወቅት

ለ) የደጎራይ የልጅነት ወቅት

ሐ) የቀዳማይ የልጅነት ወቅት

መ) የጨቅላነት  ወቅት

## ምዕራፍ ሶስት

## የቅድመ ልደት የመዳበር ወቅት

**መግቢያ**

የቅድመ-ልደት የመዳበር ወቅት ከውህደት እስከ ውልደት ያለውን የመዳበር ሁኔታ ያጠቃልላል፡፡ ፅንሱ በእናቱ ማህፀን ለዘጠኝ ወራት ይቆያል፡፡ ከሰው ህይወትና ዕድሜ አንፃር ሲታይ ዘጠኝ ወር በጣም ትንሽ ጊዜ ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁንና በዚህ ጊዜ ውስጥ ከውልደት በኋላ ከሚታዩት ከማንኛውም የመዳበር ወቅት ፈጣን የሆነ መዳበር የሚስተዋልበት ነው፡፡ አዲስ ህይወት የሚጀምረው በውህደት ወቅት ሲሆን መሰረቶቹም ከሴት የማዋለጃ አካሎች እንቁላል/እንቁላሎች አኩርተው በመውጣት በወንድ የዘር ፍሬ አማካኝነት ውህደት ሲፈፀም ነው፡፡ ይህ ጊዜ በአንድ ሰው ህይወት ውስጥ ወሳኝ ናቸው ከሚባሉት ወቅቶች አንዱ ነው፡፡ በዚህ ጊዜም በልጁ የወደፊት ህይወት ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ውጤት የሚኖራቸው አራት ጉዳዮች ይወሰናሉ፡፡ እነርሱም ፡-

ሀ. ከዘር ውርስ የሚያገኛቸው ሃብቶች ይወሰናል፡፡

ለ. የሚወለደው ሕፃን ፆታ ይወሰናል፡፡

ሐ. የሚወለደው ወይም የሚወለዱት ሕፃናት ብዛት ይወሰናል፡፡

መ. የልጁ በቤተሰብ ውስጥ ያለው የውልደት ቅደም ተከተል ይወሰናል፡፡

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የቅድመ-ልደት የመዳበር ወቅት ንዑሳን ክፍሎች፤ በቅድመ-ልደት የመዳበር ወቅት ተፅዕኖ የሚያስከትሉ ሁኔታዎች እና የቅድመ-ልደት የመዳበር ወቅትን ማጥናት አስፈላጊነት ተካተዋል፡፡ በምዕራፉ ሰር ያሉ እርዕሶችን ግልፅ ለማድረግ የተለያዩ ምሳሌዎች ተካተዋል፡፡የመለማመጃ ጥያቄዎችና ተግባራትም ከምዕራፉ ዓላማዎች ጋር እንዲተሳሰሩ ተደርገው ቀርበዋል፡፡

**የምዕራፉ ዓላማዎች**

ሰልጣኞች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቁ በኋላ ፡-

- በቅድመ-ልደት የመዳበር ወቅት በየንዑሳን ክፍሉ የሚታዩትን ባህሪያት ይዘረዝራሉ፡፡
- በቅድመ ልደት ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ አደጋዎችን ይገልፃሉ፡፡
- የቅድመ-ልደት የመዳበር ወቅት ማጥናት አስፈላጊነትን ያብራራሉ፡፡

### 1.12 የቅድመ-ልደት የመዳበር ወቅት ንዑሳን ክፍሎች

የፅንስ ዕድገት የእንቁላልና የነባ-ዘር ውህደት ካደረጉበት ጊዜ አንስቶ ያለማቋረጥ ለዘጠኝ ወራት ይቀጥላል፡፡ ከአንድና በአይን ለማየት ከማይቻል ሴል ወደ በርካታ ሴሎች ወዳሉት ሕፃን የሚደረገው እድገት ፈጣን በሆነ መልኩ በዘጠኝ ወራት አካባቢ ሂደት ይከናወናል፡፡ እነዚህ የእርግዝና ወራት በሶስት ንዑሳን ክፍሎች የሚከፈሉ ሲሆን የተለያዩ የእድገት ገፅታዎች ይታዩባቸዋል፡፡ እነሱም እንደሚከተለው ተብራርተው ቀርበዋል።

**ሀ. የውህድ-ህዋስ ወቅት (Germinal stage)**

ይህ ወቅት ውህደት ከተከናወነበት ጊዜ እስከ ሁለተኛው ሳምንት መጨረሻ ያለውን ጊዜ ያጠቃልላል፡፡ የዚህን የቅድመ-ልደት ገጽታ በሚመለከት የተዋሀደው እንቁላል በጉልህ የሚታይ እድገት አያሳይም፡፡ ምክንያቱም ከውጭ የሚያገኘው ምግብ ባለመኖሩ ነው።

የሴሎች ክፍፍልና መራባት በመኖሩ ፈጣን ውስጣዊ እድገት ይታይበታል፡፡ ፅንሱ በማህፀን ግድግዳ ላይ በግምት ከአስረኛው ቀን እስከ አስራ አራተኛው ቀን ባሉት ጊዚያት ይጣበቃል፡፡ ከማህፀን ግድግዳ ላይ ከተጣበቀ በኋላ ፅንሱ የእናትየዋ ጥገኛ ይሆናል፡፡ ምግብና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ከእናትየዋ የሚያገኝ ሲሆን ከፅንሱ የሚወጣው ቆሻሻ ነገርም ወደ እሷ ያስተላልፋል፡፡

**ለ. የፅንስ ወቅት (Embryonic stage)**

እንቁላል ከነባ-ዘር ጋር ውህደት ካገኘበት ሁለተኛው ሳምንት መጨረሻ እስከ ሁለተኛው ወር መጨረሻ ድረስ ያለውን ጊዜ ያካትታል፡፡ በዚህ የፅንስ ወቅት የሚታዩ ጉልህ የዕድገት ገፅታዎችም የሚከተሉት ናቸው።

- ሁሉም የፅንሱ ውስጣዊና ውጫዊ የአካል ክፍሎች እድገታቸውና ተግባራቸው የሚጀምርበት ጊዜ ነው፡፡
- እንደ እንግዴ ልጅ፣ እትብት፣ የእንሽርት ውሃ ከረጢት የመሳሰሉት አካሎች ያድጋሉ፡፡
- በጭንቅላት አካባቢ ያለው አካል እድገት ከተቀረው የሰውነት ክፍል እድገት ጋር ሲነፃፀር በጣም ከፍተኛ ነው፡፡
- ይህ የዕድገት ወቅት በጣም ወሳኝ ወቅት (Critical period) ይባላል፡፡ ምክንያቱም ሁሉም የአካል ክፍሎች የሚመሰረቱበት ወቅት ስለሆነ ነው፡፡

**ሐ. የሽል ወቅት (Fetal Stage)**

ከሁለተኛው ወር መጨረሻ እስከ ውልደት ድረስ ያለውን ጊዜ ያቀፈ ነው፡፡ በዚህ የእርግዝና ወቅት የሚታዩ የፅንሱ እድገትና መዳበር ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የውስጣዊና ውጫዊ የአካል ክፍሎች እድገትና መዳበር በፈጣን ሁኔታ ይቀጥላል፡፡

- ዕድገት የእድገት ህግጋትን አቅጣጫ ተከትሎ ይከናወናል።ይህም ማለት ከላይ ወደ ታችና ከውስጥ ወደ ውጭ ይሆናል፡፡ ውስጣዊ አካሎች በ5ኛው ወር አካባቢ ከአዋቂ ጋር የተቀራረበ አቅጣጫቸውን ይይዛሉ፡፡
- የነርቭ ሴሎች ከ3ኛው ሳምንት ጀምሮ የሚፈጠሩ ሲሆን ከ2ኛ እስከ 4ኛው ወር ቁጥራቸው በጣም ይጨምራል፡፡
- ቢወለድ ሊያድግ የሚችልባቸው 6ኛው ወይም 7ኛው ወር ላይ ይደርሳል፡፡
- የሽል እንቅስቃሴ (ምሣሌ፡- መራገጥ፣ መገላበጥ፣ ወዘተ.) በ2ኛውና በ3ኛው ወር ይጀምራል፡፡

| |
|---|
| **ተግባር 4** |
| *ፆታ በየትኛው የቅድመ-ልደት የመዳበር ንዑስ ክፍል ይወሰናል? እንዴት?* |

### 1.13 በቅድመ-ልደት በፅንሱ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች

እንደሚታወቀው ቅድመ-ልደት ሕፃኑ ከመወለዱ በፊት ያለው የዕድገት ዘመን ነው፡፡ ይህ ዘመን የሰው ዕድገት “ሀ” ብሎ የሚጀመርበትና አካላዊ መዋቅሮች የሚመሠረቱበት ጊዜ ነው፡፡ ሕፃኑ የሚወለደውም ብቻውን ለመኖር የሚያስችሉትን ልዩ ልዩ የሰውነት ክፈሎች ይዞ ነው፡፡ በቅድመ ወሊድ ዘመን ሊከሰቱ በሚችሉ አካበቢያዊ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ምክንያት የሰው ዕድገት ሊደናቀፍና ጉዳት ሊደርስበት ይችላል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ አንዳንድ በሕፃኑ ዕድገት ለይ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ምክንያቶችን በአጭሩ ለመጠቆም ሙከራ ይደረጋል (Tirusew, 1991)፡፡

**ሀ. የነፍሰጡሯ የተመጣጠነ ምግብ አለማግኘት**

ፅንሱ ምግቡን ከእናቱ የደም ቧምቧ ከእንግዴ ልጅ በእትብት በኩል ያገኛል፡፡ ይሁን እንጂ ነፍሰጡሯ በቂና ተመጣጣኝ ምግብ ባታገኝ የማስወረድ፣ ተገቢ ክብደት ይዞ ያለመውለድ የመሳሰሉትን ችግሮች ያስከትላል፡፡

**ለ. የነፍሰጡሯ ጤና**

ነፍሰጡሯ ጤነኛ ሕፃን ለመውለድ ጤናዋ በጥሩ ሁኔታ መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ በመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት ነፍሰጡሯ ለተለያዩ በሽታዎች ለምሣሌ እንደ ኩፍኝ እና አንዳንድ የአባለዘር በሽታ ከተጋለጠች አካል ጉዳተኛ ሕፃን የመውለድ ዕድል ሊያጋጥማት ይችላል፡፡

**ሐ. የነፍሰጡሯ ዕድሜ**

በሴቶች እድሜ ውስጥ ከሃያ እስከ ሰላሳ አምስት ዓመት ያለው ዘመን ለመፀነስና ለመውለድ አመቺ ጊዜ ነው፡፡ ከዚህ ጊዜ ቀድሞ ወይም ዘግይቶ መፀነስ ለነፍሰጡሯም ሆነ ለፅንሱ አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ በአካል አለመበርታትና አቅም ማጣት

የተነሣ በወሊድ ጊዜ ከፍተኛ ችግር ሊያጋጥም ይችላል፡፡ ይህም በነፍሰጡሯም ሆነ በሕፃኑ ላይ የአካል ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡

**መ. የነፍሰጡሯ የስሜት ሁኔታ**

በተለያዩ ምክንያቶች አንዳንድ ነፍሰጡሮች በእርግዝናቸው ደስተኞች አይሆኑም፡፡ የእርግዝና ጊዜአቸውን ብዙውን ጊዜ በሃዘን፣ በትካዜ፣ በጭንቀት፣ ወ.ዘ.ተ. ያሳልፉታል፡፡ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ለዚህ ዓይነት ስሜት መንስኤዎች ከግለሰብ ግለሰብ ቢለያዩም ሕጋዊ ያልሆነ ፅንስ፣ የኢኮኖሚ ጉዳይ፣ ከባል ወይም ከጓደኛ ጋር አለመስማማት፣ የጤና መታወክ ወይም የአካባቢ አለመመቻቸት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ነፍሰጡሯ የስጋት፣ የጭንቀትና የመሣሰሉትን ስሜቶች በቅድመ - ወሊድ ዘመን በተደጋጋሚ የምታሳይ ከሆነ በሰውነቷ ውስጥ ያሉ ውስጣዊ ዕጢዎች ፈሳሽ ንጥረ ነገሮችን ይለቃሉ፡፡ እነዚህ ንጥረ ነገሮች በእናቱ ደም በኩል ወደ ፅንሱ በመድረስ ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ የዚህ አይነቱ ችግር ካጋጠሟቸው ነፍሰጡሮች የሚወለዱ ሕፃናት አልቃሾች፣ ቅብጥብጦችና ብስጩዎች የመሆን አዝማሚያ ከማሳየታቸውም በላይ የአካል ጉዳትም ሊያጋጥማቸው ይችላል፡፡

**ሠ. የስራ ጫና**

በተለይም ከበድ ያለ የጉልበት ስራ በነፍሰጡሯ ላይም ሆነ በፅንሱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ስለሚኖረው መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው፡፡ በተለይም የመውለጃዋ ቀን እየደረሰ ሲሄድ መወገድ ይኖርበታል፡፡

**ረ. የተለያዩ ዕፆችን መጠቀም፣ አልኮል መውሰድና ሲጋራ ማጨስ**

እነዚህ ነገሮች ወደ ፅንሱ በመሸጋገር የፅንሱን የዕድገት ሂደት በማዛባት ሕፃኑ በሚወለድበት ጊዜ የቅብጥብጥነት ስሜትና የአካል ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ምክንያቶች ከግንዛቤ በማስገባት ችግሩን ለመከላከል ተገቢውን እንክብካቤና ድጋፍ ከወዲሁ ለእናቶች መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡

**ሸ. አባትነትና የቅድመ-ልደት መዳበር**

አባትየውም በተፀነሰው ሽል ላይ እንከን በማስተላለፍ የራሱ የሆነ ድርሻ አለው፡፡ ለምሣሌ አባትየው በጣም ሲጋራ የሚያጨስ፣ በጣም የአልኮል መጠጦችን የሚጠጣ፣ ወይም ለጨረር የተጋለጠ ከሆነ እንከን ያለበት የነባ-ዘር ሴል ሊያመነጭ ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ እንከን ያለበት ልጅ እንዲፀነስ የማድረግ ዕድሉ ሰፊ ነው፡፡ አባትየው የቫይታሚን ሲ እጥረት ያለባቸውን ምግቦች ከተመገበ ወይም የሚመገበው ምግብ የዚህ ቫይታሚን ዕጥረት ካለበት የሚወለደው ልጅ እንከን ያለበትና በካንሰር የመጠቃት ዕድሉ ከፍተኛ ነው፡፡ አባቶቻቸው በትላልቅ ፋብሪካዎች ውስጥ የሚሰሩ ልጆች በአእምሮ እጢ የመጠቃታቸው እድል በነኝህ

ቦታዎች ከማይሰሩት ወንዶች አብራክ ከተወለዱት ከፍ ያለ መሆኑን ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ ስለሆነም እነዚህ ችግሮች እንዳይከሰቱ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 1.14 የቅድመ-ልደት የመዳበር ወቅትን ማጥናት አስፈላጊነት

የቅድመ-ልደት የመዳበር ወቅትን ማጥናት ለምን አስፈለገ?

____________________________________________________________________

- የቅድመ-ልደት ወቅት ፈጣን ዕድገት የሚታይበት ሲሆን ዕድገቱም የአካል ክፍሎች መመስረትንና ተግበራዊ እንቅስቃሴ የማድረግ ዕድገት ነው፡፡
- ምሁራን የቅድመ-ልደት መዳበር ለድህረ-ልደት መዳበር ሞዴል (ምስል) ነው ብለው ያስባሉ፡፡ አንዳንድ የቅድመ-ልደት የመዳበር መርሆዎች ድህረ-ልደትም ላይ የሚተገበሩ ናቸው፡፡
- ዋናው የቅድመ-ልደት መጠናት ተግባራዊ ምክንያት በማደግ ላይ ያለው ፅንስ ጤና በመልካም ወይም በጎጂ መልኩ ይሁን ከእናትየዋ የዕርግዝና ወቅት ሁኔታ ጋር የተያያዘ መሆኑ ነው፡፡ እነዚህም ጉዳዮች የእናቲቱ የተመጣጠነ ምግብ ማግኘት፣ የእናቲቱ የጤንነት ሁኔታ፣ የእናቲቱ ልምዶች እና ከአንዳንድ ጎጂ ጉዳዮች መራቅ የመሳሰሉት ናቸው፡፡ በመሆኑም ብዙ ተመራማሪዎችና የስነ-ባህሪ ባለሙያዎች የተረገዘውን ህፃን ጤንነት ለማሻሻልና ከአደጋ ለመከላከል በሰፊው ጥናት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡
- የሰውን ልጅ ከጽንስ ጀምሮ ያለውን እድገት ማጥናት አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት በጽንስ ጊዜ የሚፈጠሩ የተለያዩ ችግሮችና አደጋዎች ከውልደት በኋላ በሕፃኑ እድገት ላይ የሚኖራቸው ተፅዕኖ ከፍተኛ ስለሆነ ምናልባትም እነዚህን ችግሮችና አደጋዎች ከወዲሁ የሚወገዱበት ሁኔታ ማመቻቸት በጣም ወሣኝ ነው፡፡ በአጠቃላይ ጤናማ አስተዳደግ ለማምጣት ምን ሁኔታዎች ከጽንሱም ሆነ ከእናቲቱ አኳያ መደረግ ስላለበት ሁናቴ የሚኖረው እንደምታ ከፍተኛ ነው፡፡

**1.15 የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ መለማመጃ ጥያቄዎች**

**ክፍል አንድ ፡ - የእውነት-ሀሰት ጥያቄዎች**

***መመሪያ*** ፡የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥንቃቄ ከአነበባችሁ በኃላ ትክክል የሆኑትን **እውነት**፣ትክክል ያልሆኑትን **ሀሰት** በማለት ከጥያቄዎች በስተግራ በኩል በተሰጠዉ ቦታ ላይ ፃፉ።

________1. የቅድመ-ልደት የመዳበር ወቅት የተዋሃደው እንቁላል እራሱን ከማህፀን ግርግዳ ጋር ከአጣበቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ልደት/ውልደት ያለውን የመዳበር ሂደት ያጠቃልላል፡፡

________2. አባት በተፀነሰው ሽል ላይ እንከን የማስተላለፍ የራሱ የሆነ ድርሻ አለው፡፡

________3. የሽል ወቅት ከሁለተኛው ወር መጀመሪያ እስከ ውልደት ድረስ ያለውን ጊዜ ያቀፈ ነው፡፡

________4. የቅድመ-ልደት ወቅት ፈጣን ዕድገት የሚታይበት ሲሆን ዕድገቱም የአካል ክፍሎች መመስረትንና ተግባራዊ እንቅስቃሴ የማድረግ ዕድገት ነው፡፡

________5. በቅድመ ወሊድ ዘመን ሊከሰቱ በሚችሉ አካባቢያዊ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ምክንያት የሰው ዕድገት ጉዳት ሊደርስበት ይችላል፡፡

**ክፍል ሁለት ፡- የአጭር መልስ ጥያቄዎች**

***መመሪያ*** ፡ የሚከተሉት ጥያቄዎች ባዶ ቦታዎች ላይ ተገቢዉን ቃል ወይም ሃረግ በመሙላት መልሳችሁን ፃፉ።

6. ለመፀነስና ለመውለድ አመቺ ጊዜ የሚባለው የሴቶች እድሜ ከ_________ እስከ________አመት ነው፡፡

7. ከቅድመ-ልደት የመዳበር ወቅት ሶስት ንዑሳን ክፍሎች ውስጥ ለእድገት ወሳኝ ወቅት (critical period) የሚባለው __________ ወቅት ነው፡፡

8. የሰው ልጅ ፆታ በየትኛው የቅድመ-ልደት የመዳበር ንዑስ ክፍል ይወሰናል? __________

9. ፈጣን የሴሎች ክፍፍልና መራባት የሚታይበት የተዋሃደው እንቁላል በእናቲቱ ላይ ጥገኝነት ያልጀመረበት የቅድመ-ልደት የመዳበር ንዑስ ክፍል ___________ወቅት ነው፡፡

10. ፅንሱ በእናቲቱ ማህፀን ውስጥ በአማካኝ ለ_____________ ወራት ይቆያል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የድህረ-ልደት የመዳበር ወቅት

**መግቢያ**

የድህረ ልደት የመዳበር ዘመን ከልደት እስከ ህልፈተ - ህይወት ያለውን የሰው ልጅ መዳበር ሂደት የሚያካትት ቢሆንም በዚህ ምዕራፍ የሚዳሰሰው እስከ ቀዳማይ የልጅነት ወቅት መጨረሻ ብቻ ይሆናል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የምንቃኛቸው ይዘቶች የጨቅላነት የመዳበር ወቅት፣ የህፃንነት የመዳበር ወቅትና የቀዳማይ የልጅነት የመዳበር ወቅት ይሆናሉ.ል፡፡በምዕራፉ ሰር ያሉ እርዕሶችን ግልፅ ለማድረግ የተለያዩ ምሳሌዎች ተካተዋል፡፡የመለማመጃ ጥያቄዎችና ተግባራትም ከምዕራፉ ዓላማዎቹ ጋር እንዲተሳሰሩ ተደርገው ቀርበዋል፡፡

**የምዕራፉ ዓላማዎች**

ሰልጣኞች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቁ በኋላ ፡-

- የጨቅላነት ወቅት ባህሪያትን ይገልፃሉ፡፡
- የሕፃንነት የመዳበር ዘመን ዋና ዋና ባህሪያትን ይለያሉ፡፡
- የሕፃንነት ወቅትን የአካል፣ የአእምሮ፣ የቋንቋ፣ የኃይለ-ስሜትና ማኅበራዊ መዳበር ያብራራሉ፡፡
- የቀዳማይ የልጅነት ወቅት ባህሪያትን ይዘረዝራሉ፡፡
- የቀዳማይ የልጅነት ወቅትን አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ እንቅስቃሴያዊ፣ ኃይለ - ስሜታዊና ማኅበራዊ መዳበሮችን አንዱን ከሌላው ይለያሉ፡፡
- በቀዳማይ የልጅነት ወቅት የሚጎለብቱ ባህሪያት ለትምህርት ያላቸውን እንደምታ ያብራራሉ፡፡
- ልጆች መልካም ስነ-ምግባር እንዲያጎለብቱ የሚያስችሉ ስልቶችን ይገልፃሉ ፡፡
- በልጅነት ወቅት ሊጎለብቱ የሚችሉ ተገቢ ያልሆኑ ባህሪያትን በመለየት እንዴት ሊሻሻሉ እንደሚችሉ ያብራራሉ ፡፡
- የልጆች ትኩረት ወደ ትምህርቱ እንዲሆን ከቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤት መምህር ምን እንደሚጠበቅ ይዘረዝራሉ፡፡

**1.16 የጨቅላነት ወቅት**

የጨቅላነት ወቅት ከልደት ወይም ውልደት እስከ ሁለት ሳምንት ያለውን ጊዜ ይሸፍናል፡፡ ይህ ወቅት የድህረ - ልደት የመዳበር ወቅት የመጀመሪያው ንዑስ ክፍል ሲሆን በስሩም ሁለት ንዑሳን ክፍሎች አሉት፡፡ እነርሱም እንደሚከተለው ተብራርተው ቀርበዋል።

**ሀ.** **የውልደት ጊዜ** (Period of partunate)፡- ጨቅላው ከማህፀን ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ እትብቱ እስከተቆረጠበት ጊዜ ድረስ ያለውን አጭር ጊዜ ያካትታል፡፡

**ለ.** **የአዲስ ጨቅላነት ወቅት** (Period of neonate) ፡- ጨቅላው እትብቱ ከተቆረጠበትና ከተቋጠረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሁለት ሣምንት ያለውን ጊዜ ያካትታል፡፡ ይህ በአብዛኛው ጨቅላው ከአዲሱ አለም ጋር እራሱን ለማስማማት ጥረት የሚያደርግበት ፈታኝ ጊዜ ነው ማለት ይቻላል፡፡

**የጨቅላነት ወቅት መላመድ**

አዲስ የተወለዱ ጨቅላዎች ራሳቸውን ከአራት ጉዳዮች ጋር ማስማማት ይኖርባቸዋል (Hurlock, 1980) ። እነርሱም፡-

i. **ከሙቀት ለውጥ ጋር መላመድ**

በእናቱ ማህፀን ውስጥ ባለው የፅንስ ከረጢት ውስጥ የሙቀት ሁኔታ በቋሚነት $100^0$F ነው፡፡ በውጫዊው አለም ግን የሙቀት መጠን $60^0$F እስከ $70^0$F ይሆናል፡፡ ስለዚህ ጨቅላው ይህን ለውጥ መቀበልና ራሱን ማስማማት ይጠበቅበታል፡፡

ii. **ከአተነፋፈስ ስርዓት ጋር መላመድ**

ከልደት በፊት ባሉት ወራት ሽሉ ንፁህ አየር ማለትም ኦክስጅን የሚያገኘው ከእናቱ በእትብት አማካኝነት ነበር፡፡ በልደት ጊዜ እትብቱ ስለሚቆረጥ በራሱ የአተነፋፈስ ስርዓት አየር ማስገባትና ማስወጣት ይኖርበታል፡፡ የውልደት ልቅሶ የሚከተለው አዲሱ ጨቅላ አየር ወደ ሳንባው ለማስገባት እንቅስቃሴ እንዲያደርግ ለማበረታታት ሲሆን ለቅሶው የሚጀምረው ጨቅላው በራሱ ሳንባ መተንፈስ ሲጀምር ነው፡፡

iii. **የእናትን ጡት መጥባትና መዋጥን መላመድ**

በቅድመ-ልደት ወቅት ሽሉ ምግብ ከእናቱ በእትብት አማካኝነት ይደርሰዋል፡፡ በልደት ጊዜ እትብት ስለሚቆረጥ የእናቱን ጡት መጥባትና መዋጥን መላመድ ይጠበቅበታል፡፡ ጨቅላው የአመጋገብ ለውጡን ተቀብሎ መመገብ ካልቻለ ህይወቱ አደጋ ላይ ትወድቃለች፡፡

iv. **ከሰውነት የሚወጡ ቆሻሻዎችን ማስወገድ መላመድ**

ጨቅላው ከተወለደ ከጥቂት ደቂቃዎችና ሰዓታት በኋላ የቆሻሻ አስወጋጅ አካላት ስራቸውን ይጀምራሉ፡፡ በቅድመ-ልደት ወቅት ግን እነዚህ የሰውነት ቆሻሻዎች ይወገዱ የነበሩት በእትብትና በእንግዴ ልጅ አማካኝነት ወደ እናቲቱ ከሄዱ በኋላ ከእሷ ከሚወጡ ቆሻሻዎች ጋር አብረው ነበር፡፡

እንደ ኤልዛቤት ሐርሎክ እምነት እነዚህን ለውጦች ተቋቁሞ ራሱን ከሁኔታዎች ጋር አስማምቶ ሕይወትን ለቀጣዩ ጉዞ ማመቻቸት አዲስ ለተወለደ ጨቅላ በጣም አስቸጋሪና ጊዜ የሚወስድ እንደሆነ ገልጻለች (Hurlock, 1980) ፡፡ የጨቅላነት ዘመን ከፍተኛና ውስብስብ ራስን የማስማማት ወቅት ነው፡፡ በዚህ ጊዜም በጨቅላዎች ላይ ተለዋዋጭ ባህሪያት፣ የክብደት መቀነስና ከዚህ በከፋ ሁኔታ ደግሞ የጨቅላዎች ሞት ይስተዋላል፡፡

በሌላ በኩል የስነ-ባህሪና የህክምና ጥናቶች እንደሚያስረዱት ልደትና ከውልደት ጋር ግንኙነት ያላቸው ጉዳዮች ጨቅላው እራሱን ከአዲሱ አካባቢ ጋር በማላመድ ሂደቱ ላይ እና በአጠቃላይ በድህረ-ልደት ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ አለ፡፡ የሚከተሉት ምክንያቶች ዋነኞቹ ናቸው፡፡

- የውልደት ዓይነቶች፤
- የቅድመ-ልደት ከባቢያዊ ሁኔታ፤
- የወራት-ፅንስ ርዝመት፤
- ድህረ-ልደት ክብካቤ፤
- የቤተሰብ አመለካከቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

### 1.17 የሕፃንነት ዕድሜ ወቅት

የሕፃንነት ዕድሜ ከጨቅላ ዕድሜ ሁለተኛው ሳምንት ማብቂያ እስከ ሁለተኛ ዓመት መጨረሻ ያለውን ጊዜ ያካትታል፡፡

#### 1.17.1 የሕፃንነት የመዳበር ወቅት ዋና ዋና ባህሪያት

ሀ. **ሕፃንነት እውነተኛ መሰረት የሚጣልበት ዕድሜ ነው፡፡**

በሕፃንነት ዕድሜ ብዙ የባህሪ ዓይነቶች፣ የአመለካከት ስርዓትና የስሜት መገለጫ ዓይነቶች መሰረት የሚጣልበት ነው፡፡

ለ. **ሕፃንነት ፈጣን ዕድገትና ለውጥ የሚታይበት ዕድሜ ነው፡፡**

ሕፃናት በአካልም በስነ-ባህሪ ፈጣን ዕድገት ያሳያሉ፡፡ በዚህ ፈጣን ዕድገት የሚመጣው ለውጥ የገጽታ ብቻ ሳይሆን በችሎታም ጭምር ነው፡፡ የሕፃንነት ወቅት ከመጠናቀቁ በፊት

ሕፃናት ብዙ ነገሮችን መረዳት ይችላሉ፣ ፍላጎታቸውንና ስሜታቸውን ሌሎች እንዲረዱ በሚችሉበት ሁኔታ ያስተላልፋሉ፡፡

**ሐ. ሕፃንነት ጥገኝነትን የሚቀንስበት ዕድሜ ነው፡፡**

ሕፃናት በሌሎች ላይ ጥገኛ መሆንን እየቀነሱ የሚመጡት ፈጣን የሆነ አካልን የመቆጣጠርና በዚህም ምክንያት መቀመጥ፣ መቆምና መራመድ በመቻላቸው ነው፡፡ ሕፃናት ማናቸውንም ነገር በነፃነት እራሳቸው ለመስራት እንጂ ሌሎች እንዲሰሩላቸው አይፈልጉም፡፡ ሌሎች እንዲሰሩላቸው ስሞክሩም ይቃወማሉ፣ አሉታዊ ባሕሪን ያዳብራሉ፡፡ ተቃውሞአቸውንም የሚገልፁት በንዴት፣ በማልቀስና የተቃርኖ ስሜትን በመፍጠር ነው፡፡

**መ. ሕፃንነት ግለኝነትን የማጠናከሪያ ዕድሜ ነው፡፡**

የነፃነት መጨመር ሕፃናት በራሣቸው የግል ምርጫና ፍላጎት ማደግ እንዲችሉ ይፈቅድላቸዋል፡፡ ግለኝነት በተክለ ሰውነትና (ገፅታ) በተለያዩ ባህሪዎች ይንፀባረቃሉ፡፡ መንታ ወይም ከሁለትና ሶስት በላይ በአንድ ጊዜ የተወለዱ ህጻናት ቢሆኑም እንኳ ግለኝነትን ያንፀባርቃሉ፡፡

**ሠ. ሕፃንነት የማኀበራዊ ሕይወት መጀመሪያ ዕድሜ ነው፡፡**

በእራስ ስሜትና አስተሳሰብ ብቻ ይመራ የነበረ ሕፃን ፈጣን በሆነ መልኩ የማኀበራዊ ቡድን አባል ለመሆን ጥረት ሲያደርግ ይስተዋላል፡፡ በሕፃንነት ዕድሜ ማኀበራዊ ሕይወትና ትስስር የሚገለፅበት መንገድ በ”Attachement Behavior” ነው፡፡ ይኸውም ሕፃናት ከእናቶቻቸው ጋር ጠንካራ ስሜታዊ ትስስር የሕፃንነት ዕድሜ (ወቅት) ከመጠናቀቁ በፊት የሚፈጥሩበት ነው፡፡ ህጻኑ የሚፈጥረው የማኀበራዊ ግንኙነት/ትስስር እድገት ከእናቱ በመጀመር ከቤተሰቡ አባላትና ጎረቤቶች ጋር በማጠናከር ይቀጥላል፡፡

**ረ. ሕፃንነት የፆታዊ ሚና መለየት የሚጀመርበት ወቅት ነው፡፡**

ሕፃናት ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ ወንዶች እንደወንድ ሴቶች ደግሞ እንደሴት እንደሚስተናገዱ ግልጽ ነው፡፡ ለምሣሌ ወንዶች ከሴቶች የተለየ አለባበስ እንዲለብሱ ይደረጋል፡፡ አሻንጉሊቶችን ሲመርጡ ለወንድ ወይም ለሴት ምቹ የሆኑ በሚል ነው፡፡ ተረት ሲነገራቸው ስለወንድ ታሪክ ነው፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ፆታን የሚለይ ልማዶችና ስርዓቶች ለሴቶችም አሉ፡፡

**ሰ. ሕፃንነት ተፈጥሮአዊ ችሎታቸውን/ተሰጦአቸውን የሚጀምሩበት ወቅት ነው፡፡**

በሕፃንነት ዕድሜ ልጆች ያላቸውን ተፈጥሮአዊ ተሰጥኦ በመጠቀም አካባቢያቸውን ይቃኛሉ፣ ሙከራዎች ያደርጋሉ። በመሆኑም ከሰውም ይሁን ከእቃ ምላሽ ይጠብቃሉ፡፡

**ሸ. ሕፃንነት ለዕይታ የሚስብ ወቅት ነው፡፡**

ሕፃናት ባላቸው ተክለ-ሰውነት ማለትም ትልቅ ጭንቅላት፣ የተወጠረ ወጣ ያለ ሆድ፣ አጭርና ቀጭን እጅና እግር የተነሳ ለዕይታ የሚማርኩ ናቸው፡፡

**ቀ. ሕፃንነት አደጋ የሚያጋጥምበት እድሜ ጭምር ነው፡፡**

በሕፃንነት ወቅት የሚያጋጥሙት አደጋዎች አካላዊ ወይም ስነ-ባህሪያዊ ናቸው፡፡ አካላዊ ከሆኑት ውስጥ ሕመምና አደጋ ዋናዎቹ ሲሆኑ ለዘላቂ የአካል ጉዳተኛነትና ሞት ሊያደርሱ ይችላሉ፡፡ በሌላ መልኩ ሕፃንነት ስነ-ባህሪያዊ የሆኑ ውስጣዊ ባህሪያት (ምርጫ፣ ፍላጎት፣ ተነሳሽነት፣ አመለካከት) የሚመሠረትበት ዕድሜ በመሆኑ እነዚህ ባህሪያት በደካማ መሠረት ላይ ከተቀረቀሩ በሂደት ሕፃናቱ የከፋ የስነ-ባህሪ ችግር ሊከሰትባቸው ይችላል፡፡

### 1.17.2 የህፃንነት ወቅት የአካል መዳበር

የሕፃናት የአካል መዳበር በመጀመሪያዎቹ ሁለት አመታት ውስጥ በጣም ፈጣን ነው፡፡ ክብደትና ቁመት በመጀመሪያዎቹ ወራት አካባቢ ከመቼውም ግዜ በበለጠ ይጨምራሉ፡፡

- የአጥንት እድገት በመጀመሪየው ዓመት ላይ በጣም ፈጣን ነው፡፡
- የሕፃናት ክብደት መጨመር መንስኤው የጡንቻዎችና የስብ ቲሹ መጨመር ነው፡፡
- ሕፃናት የመጀመሪያዎቹን የወተት ጥርስ (Temporary teeth) ከ5ኛው ወራቸው እስከ 9ኛው ወራቸው ያበቅላሉ፡፡ በአንደኛ አመታቸው አካባቢ ከ6 እስከ 8 የወተት ጥርሶች ሊያበቅሉ ይችላሉ፡፡ ከ2 - 2½ ዕድሜአቸው ወደ 20 ጥርሶች ያበቅላሉ፡፡
- የስሜት ሕዋሳት በሕፃንነት ወቅት ከፍተኛ ዕድገት ያሳያሉ፡፡
- የነርቭ-ስርዓት ዕድገት በሕፃንነት ወቅት ፈጣን ነው፡፡ የዕድገቱ መሠረት የነርቭ ሴሎች በቁጥርና መጠን መጨመር ነው፡፡

### 1.17.3 የህፃንነት ወቅት የእንቅስቃሴ መዳበር

መገላበጥ፣ መቀመጥ፣ መዳህ፣ ዳዴ ማለት፣ መቆምና መራመድ በህፃንነት ወቅት የሚታዩ የእንቅስቃሴ መጎልበት ሂደቶች ናቸው፡፡

ትላልቅና መለስተኛ የጡንቻዎችን እንቅስቃሴ ክህሎቶች ያዳብራሉ፡፡

- ከ3-13 ወራት አንገትን ቀና ከማድረግ ጀምሮ ያለምንም ድጋፍ በራሣቸው ይራመዳሉ፡፡
- ከ13-18 ወራት የተንጠለጠለ አሻንጉሊት ይስባሉ፣ ደረጃዎችን ይወጣሉ፣ መውረድም ይጀምራሉ፡፡
- ከ18-24 ወራት ፈጥነው ይራመዳሉ፡፡

### 1.17.4 የሕፃንነት ወቅት አእምሮአዊ መዳበር

ጄን-ፒያጄት የተባለው ምሁር  በሕፃንነት ዕድሜ የሚኖረው አእምሮአዊ መዳበር በአብዛኛው የስሜት ሕዋሳትንና አካላዊ እንቅስቃሴዎችን በማከል የሚከናወን አስተሳሰብ እንደሆነና ይህንንም በሚከተሉት ስድስት ደረጃዎች (Six stage of sensorimotor development) ማየት እንደሚቻል አብራርቷል፡፡

| ወቅት | መገለጫው | ምሳሌ |
|---|---|---|
| I. ከውልደት -1 ወር | ተፈጥሮአዊ ምላሾች መጥባት፣ መያዝ፣ ማፍጠጥ፣ ማዳመጥ ናቸው፡፡ የደስታው የግንኙነት ምንጭ በአብዛኛው የራሣቸው አካል ነው፡፡ | አውራጣትን መጥባት፣<br>እግርን መምታት፣<br>እጅ ላይ ማፍጠጥ፣ |
| II. ከ1 ወር - 4ኛ ወር | የመጀመሪያው አካባቢያቸውን የተላመዱበት ጊዜ ነው ፤ወይም ምላሾቻቸው እንደአካባቢያቸው ሁነው የማጣጣም ችሎታን የሚያዳብሩበት ወቅት ነው፡፡<br>- ብቃት ያለው ጡት መጥባት ጡቱን መጭመቅ መሆኑን መረዳት ይጀምራሉ፤<br>- እራብን የሚያስታግሱ ነገሮችን ከማያስታግሱ ይለያሉ፤<br>- "የእንጀራናት ጡትን" በራባቸው ጊዜ ሲሰጡ ይተፉታል፡፡<br>- ዕቃ በዓይን እስካልታየ ድረስ አለ የሚለውን ነገር አያውቁም (Lack of object permanence) | "ጡትንና ጡጦን" መጥባት የምግብ ፍላጎትን ማርካት እንደሆነ ይገነዘባሉ፡፡<br>"እጅንና የእንጀራናትን" መጥባት ለእርካታና ደስታ ብቻ መሆኑን ይለያሉ፡፡ |
| III. ከ4—8ኛ ወራት | - ለሰዎችም ሆነ ለእቃዎች መልስ የሚሰጡበት ወቅት ነው፡፡<br>- ሰውንና እቃን የሚለዩበት ወቅት ነው፡፡<br>- ሕፃናት አንድ ውስን ነገር ሲያከናውኑ ከሰውም ሆነ ከእቃው ምላሽ ይጠብቃሉ፡፡ በመሆኑም ደጋግመው ነገሩን ያከናውናሉ፡፡  ምላሽም እንደሚኖር እንደገና ተስፋ ያደርጋሉ፡፡ | አሻንጉሊትን ድንገት ሲነኩት ድምጽ ከሰጣቸው ደግመው በመጭመቅ ምላሽ (ድምጽ መስማት) ይጠብቃሉ፡፡  ይህም ደስታ ይሰጣቸዋል፡፡ |
| IV. ከ8—12ኛ ወራት | - ሕፃናት በተሻለ እራሣቸውን እየለወጡ አካባቢያቸውን የሚረዱበት፣ የሚለማመዱበት፣ ዓላማ ያለው መስተጋብር የሚፈጥሩበት ወቅት ነው፡፡<br>- አንድ እቃ ከዓይናቸው ቢሰወር እንኳ እንዳለ እንደሚኖር በትክክል ይረዳሉ፡፡ (Object permanence)፡፡ | - ነገሮች በዓይን ባይታዩም እንደሚኖሩ መረዳት ይችላሉ፤<br>- ነገሮችን ከወዲሁ ይገምታሉ፣ እናታቸው ነጠላ ገና ስትለብስ ልትወጣ ነው በሚል ማልቀስ ይጀምራሉ፣ |
| V. ከ12—18ኛ ወራት | አካባቢያቸውን በአዲስ ሰመልክ የሚቃኙበት፣ ሙከራዎችን የሚያከናውኑበት፣ የፈጠራ ችሎታቸውን የሚያንፀባርቁበት ወቅት ነው፡፡ | "አሻንጉሊት ከበሮን" በእንጨት፣ በእርሳስ፣ በመዶሻ ወዘተ በመምታት  የተለያየ ድምጽ |

| ወቅት | መገለጫው | ምሳሌ |
|---|---|---|
| | "ትንሹ ሣይንቲስት" የሚባሉበት ወቅት ነው፡፡<br>- መሠረታዊ ጥያቄዎችን ያነሣሉ፣ ምን ነገር ላደርግበት እችላለሁ? ከጡጦው ላይ ጫፉን ባነሳው ምን ይሆናል? ድመቷ ላይ ውሃ ባፈስባት ምን ትሆናለች? በሚል ይጠይቃሉ። የሚጠቀሙት "ሣይንሣዊ ዘዴ" መሞከር - መሣሣት - መሞከር - መሣሣት ወዘተ. ነው፡፡ (Action before thinking) | ማውጣቱን ይለያሉ፡፡<br>የሸክላ ጭቃን በተለያየ መልክ በመጭመቅ ቅርፁን ያያሉ፡፡ |
| VI. ከ18—24ኛ ወራት | አእምሮአዊ ውህድ በመፍጠር ቀላል ችግሮችን ከፊቱ በኋላ ወደተግባር ይሄዳሉ፡፡ በመጀመሪያ ችግሩን እንዴት እንደሚፈታ በዓይነ ሕሊናቸው ካሰላሰሉ በኋላ ወደ ተግባር ይገባሉ፡፡ (Thinking before action) | በአእምሮአቸው ችግሩ የሚፈታበትን የተለያዩ ሙከራዎችና መፍትሔዎች ካጤኑ በኋላ ወደ ተግባር ይሄዳሉ፡፡ |

### 1.17.5 የሕፃንነት ወቅት የቋንቋ መዳበር

ቋንቋና ንግግርን ብዙ ሰዎች አለዋውጠው ሲገለገሉባቸው ይታያል፡፡ ሆኖም እነዚህ ሁለት ቃላት የተለያዩ ትርጉም አላቸው፡፡ ቋንቋ ማንኛውንም የግንኙነት ዘዴ የሚያቅፍ ሲሆን ሃሣብን ወይም ውስጣዊ ፍላጎትን ለሌላው ለማጋራት የምንጠቀምበት መንገድ ነው፡፡ ይህም የተለያዩ የግንኙነት መንገዶች ማለትም በጽሁፍ፣ በንግግር፣ የምልክት ቋንቋ፣ የፊት ገለፃ፣ አካላዊ እንቅስቃሴ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ንግግር (speech) የቋንቋ አካል ሲሆን ትርጉም ያለው ግንኙነት ለማድረግ ይቻል ዘንድ ድምፅን ወይንም ቃላትን የምንጠቀምበት መንገድ ነው፡፡ ይህ ውጤታማ የግንኙነት መንገድ ጠቃሚና ብዙውን ጊዜ የምንገለገልበት ነው፡፡ ንግግር የአካላዊ እንቅስቃሴና የአእምሮ ክህሎት ውጤት ነው፡፡ የነርቭና ጡንቻዎች እድገት ግልጽ፣ የተቆጠቡ፣ ልዩ ድምፆች እንዲያፈልቁ ይረዷቸዋል፡፡ የንግግር ክህሎት መማር ረጅምና ውስብስብ ሂደት ያለው ጉዳይ ነው፡፡ ሕፃናትን ለንግግር የሚያስችለው አካላዊ ክፍል እስከሚያድግ ድረስ ተፈጥሮ የተለያዩ የሃሣብ መግለጫ መንገዶች ቀይሳላቸዋለች፡፡ በዚህም ምክንያት ቅድመ-ንግግር (pre-speech) የመገናኛ መንገዶችን በመጠቀም ሃሣባቸውን ማስተላለፍ ግድ ነው፡፡ ከ1-2 ዓመት ባለው ጊዜ ለንግግር የሚያስፈልጓቸውን ቃላት እስከሚማሩ ድረስ ሕፃናት አራት ቅድመ-ንግግር የግንኙነት ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡ እነርሱም፡-

ሀ. **ማልቀስ (Crying)**

ለቅሶ ሕፃናት ከአለም ጋር የሚገናኙበት የመጀመሪያው ድምጽ ነው፡፡ ሆኖም የተለያዩ ሁኔታዎችን (ለምሣሌ፡- መራባቸውን፣ መፍራታቸውን፣ መቆጣታቸውንና መተኛት መፈለጋቸውን) የሚገልፁት በለቅሷቸው የተለያየ የድምፅ ቅላፄ (Tonal quality) በማውጣት

ነው፡፡ በቤተሰብ ምክርና ማበረታታት ሕፃናት ለቅሶን እንደ ግንኙነት መንገድ መጠቀማቸው ቀስ በቀስ በመዋዕለ ሕፃናት ጊዜአቸውና በመጀመሪያው የመደበኛ ትምህርት ቤት ዕድሜያቸው ወቅት እየቀነሰ እንዲመጣ ያደርጋቸዋል፡፡ በዚህ ዕድሜያቸው መሻሻል ካልታየባቸው በግልና ማኀበራዊ ሕይወታቸው ውህደት ላይ ችግር ያስከትልባቸዋል፡፡

**ለ. በሂደት ወደ ድምፅ ቅላፄነት የሚቀየር ድምጽ** (Babbling)

የአየር እንቅስቃሴን በድምፅ መፍጠሪያ ቦታ አካባቢ መቆጣጠር ሲችሉ ሕፃናት አንዳንድ ድምፆችን በትክክል መድገም ይችላሉ፡፡ ማላዘን የድምፅ ጅምናስቲክ ሲሆን በሕፃናት ፍላጎት የሚደረጉ ሆነው ነገር ግን ትክክለኛ ትርጉም ለሕፃኑ የማይሰጡ ናቸው፡፡ ማላዘን አንዳንድ ሕፃናት ገና በተወለዱ ከ2ኛው ወራቸው የሚጀምሩ ሲሆን ከፍተኛ የሆነ እድገት ላይ ከ6 — 8 ወራቸው ይደርሳሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ማላዘን በቃላት መጠቀምን የሚያስከትል ይሆናል፡፡

**ሐ. የአካላዊ እንቅስቃሴ ግንኙነት** (Gestures)

አካላዊ እንቅስቃሴ የቅድመ-ንግግር የግንኙነት መንገድ ሲሆን አካልን በማንቀሣቀስ ንግግርን በመተካት ወይም በማገዝ ሃሣብን የመግለጫ ዘዴ ነው፡፡ አብዛኞቹ በሕፃናት የሚደረጉ አካላዊ እንቅስቃሴዎች በቀላሉ መረዳት የሚቻሉ ናቸው፡፡ በዚህም የተነሣ ሕፃናት ቃላትን በማውጣት ሀሣባቸውን መግለጽ እስከቻሉ ድረስ የንግግር ፍላጎታቸውን የሚያረኩበት መንገድ ነው፡፡

**ለምሣሌ**

| **የአካላዊ እንቅስቃሴ ግንኙነት** | | **ትርጉማቸው** |
|---|---|---|
| ምግብን ከአፍ ማውጣት ......................................... | - | መጥገብን |
| ዕቃን ከፊታቸው  መግፋት .................................... | - | አለመፈለግን |
| ፈገግ ማለትና እጆችን መዘርጋት ............................ | - | ለመታቀፍ መፈለግን |
| ጡትን በምላስ ገፍቶ ከአፍ ማውጣት ....................... | - | መጥገብን |
| ከንፈርን ወደፊት መለጠጥ ..................................... | - | ቅሬታ መግለጽን |
| ከንፈርን መምጠጥ ወይም ምላስን መጎልጎል  ........... | - | መራብን |

**መ. ኃይለ-ስሜታዊ አገላለፆች** (Emotional expressions)

አራተኛው የቅድመ-ንግግር የግንኙነት መንገድ ሐይለ ስሜታዊ አገላለፅ ነው፡፡  ይህም በአካል ለውጥና በፊት ሁኔታ ሃሣብን መግለፅ ነው፡፡  ደስተኛ ሁኔታዎች በአስደሳች ድምፅና ሳቅ የሚታገዙ ሲሆን የማያስደስቱ ኃይለ-ስሜቶች ደግሞ በሚንቀጠቀጥ ድምፅና ለቅሶ ይደገፋሉ፡፡  ህፃናት ደስ ሲላቸው ሰውነታቸው ይዘናል፡፡  እግርና እጃቸውን ያወናጭፉሉ፡፡ ፈገግታም በፊታቸው ላይ ይታያል፡፡  ይህም አስደሳች በሆነ ድምፅ ይደገፋል፡፡  በተቃራኒው

ቁጣቸው የሚገለፀው ሰውነታቸውን በማስቆጣት የእጅና እግር እንቅስቃሴአቸውን አለማዋሃድ፣ በተወጠረ የፊት ገፅታና በቁጣ ለቅሶ ነው፡፡

ሕፃናት ውስጣዊ ሁኔታቸውን መደበቅ ስላልተማሩ ሰዎች ስለ እነርሱና ስለሁኔታዎች ሕፃናት ያደረባቸውን ስሜት በቀላሉ መረዳት ይችላሉ፡፡ እያደጉ ሲመጡ ግን ፍላጎታቸውንና ስሜታቸውን መደበቅ ስለሚማሩ ይህ የግንኙነት መንገድ ጥቅም አይኖረውም፡፡

ሌላው ኃይለ-ስሜታዊ ገለፃ ለሕፃናት ያለው ጠቀሜታ የወላጆቻቸውን የፊትና የድምፅ ቅላጼ ለውጥ ቶሎ እንዲረዱ ማድረጉ ነው፡፡ የሚናገሩትን ቃላት መረዳት ባይችሉም የቤተሰቦቻቸውን መጥፎና መልካም ሁኔታ ይገነዘባሉ፡፡

ልክ እንደአካላዊ እንቅስቃሴ ሁሉ ኃይለ-ስሜታዊ ገለፃ ሕፃናት መናገር ከጀመሩ በኋላም በቀጣይነት ይታያል፡፡ ውስጣዊ ስሜትን መደበቅ መቻል በጣም አስቸጋሪ በመሆኑ ከአካላዊ እንቅስቃሴ ይልቅ ለረጅም ጊዜ ይቆያል፡፡

* ሕፃናት ከ12 — 18 ወራት ባሉት ጊዜያት አንድ ቃል ብቻ ያለው አረፍተ ነገር መሰል መሥራት ይጀምራሉ፡፡

  **ለምሣሌ** *ስጠኝ ብሎ ወደ አሻንጉሊት ሲያመላክት አሻንጉሊቱን ስጠኝ ማለቱ ነው፡፡* በአንድ ቃልና በአካላዊ እንቅስቃሴ ታግዞ የተመሰረተ ዓረፍተ ነገር ይሆናል፡፡

* ሕፃናት ከ18 እስከ 24 ወራት ከበፊቱ መለስተኛ ለውጥ በማድረግ ያልተሟሉና በሁለት ቃላት የተገነቡ ዓረፍተ ነገሮች መሥራት ይጀምራሉ፡፡

  **ለምሣሌ**

  *ባባ የት?*................ - *አባባ የት ሄደ? ለማለት ሲፈልግ ነው፡፡*

  *ማማ ጫማ* ........... - *የእማማ ጫማ ነው ለማለት ሲፈልግ ነው፡፡*

### 1.17.6 የሕፃንነት ወቅት የኃይለ-ስሜት መዳበር

ኤልዛቤት ሐርሎክ የተባለችው ታዋቂ የልጆች ስነ-ባህሪ ባለሙያ እንደገለፀችው በሕፃንነት ዕድሜ የሚስተዋሉ የስሜት ዓይነትና መገለጫዎቹ እንደሚከተለው ማቅረብ ይቻላል (Hurlock, 1980)፡፡

- **ቁጣ/ንዴት** (Anger)፡-ሕፃናት የሚናደዱት ማድረግ የሚፈልጉትን እንዳያደርጉ ሲከለከሉ፣ ለመንቀሳቀስ ሲፈልጉ ጣልቃ ገብቶ የሚያግዳቸው ነገር ሲፈጠር፣ ወዘተ ናቸው፡፡ የንዴት መገለጫዎችም ጩኸት፣ የራስ እግርን መምታት፣ ክንድን ማወናጨፍ፣ በቅርብ ያለ ነገርን መምታት ናቸው፡፡

- **ፍርሃት** (Fear)፡- ድንገተኛናያልተጠበቀ ነገር ሲያጋጥማቸው ወይም ሕፃናቱ ከዚህ ቀደም የማያውቁት ሲገጥማቸው ፍርሀት ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ ፍርሀት ለፈጠረባቸው ሁኔታ ሕፃናት የሚከተሉትን ምላሾች ይሰጣሉ፡፡
    - ፍርቱን ከፈጠረው ሰው ወይም ነገር እራስን ማግለል፣
    - አነስተኛና ደካማ ድምጽን ማሰማት፣
    - ማልቀስ፣
    - ለጊዜውም ቢሆን ትንፋሽን መያዝ (መዋጥ)፣
    - ፀጥ ብሎ የነገሩን እንቅስቃሴ መቆጣጠር

አብዛኛውን ጊዜ ፍርሐትን በሕፃናት ላይ የሚፈጥሩት አነቃቂ ነገሮች

- ከፍተኛ ፍንዳታ /ድምፅ/፣
- እንግዳ ሰው፣
- ያልተለመዱ እቃዎችና ነባራዊ ሁኔታዎች፣
- ጨለማ ክፍሎች፣
- ከፍታ ቦታዎች፣
- እንስሳት ወዘተ ናቸው፡፡

- **ለማወቅ ያለ ጉጉት** (Curiosity)፡- ማንኛውም አዲስ የሆነ ነገርና ያልተለመዱ ተግባራት በሕፃናት ላይ የማወቅ ጉጉትን ይጭሩባቸዋል፡፡ ሕፃናት ጉጉታቸውን የሚገልፁት፡-
    - በፊታቸው በሚያንፀባርቁት፤
    - በጡንቻዎቻቸው በሚያደርጉት እንቅስቃሴ፣
    - አፋቸውን በመክፈት ሲሆን የኋላ ኋላ ግን ሕፃናቱ ለማወቅ ያላቸውን ጉጉት የሚገልፁት፣ እቃውን በመያዝ፣ በማወዛወዝ፣ በማገላበጥ፣ በመጥባትና በመሳሰሉት ነው፡፡
- **ደስታ** (Joy): ሕፃናት ደስተኛ የሚሆኑት በሚያገኙት አካላዊ ደህንነት (በቂ ምግብና እንቅልፍ፣ ፍቅርና እንክብካቤ) ነው፡፡ መገለጫውም ፈገግታ፣ ሣቅ፣ እጅና እግርን ማንቀሣቀስ ናቸው፡፡
- **መውደድ** (Affection):- ማንኛውም ሰው ከህጻናቱ ጋር የሚጫወት፣ አካላዊ ፍላጎታቸውን የሚያሟላላቸው፣ ፍቅር የሚሰጣቸው ሁሉ በእነርሱ ዘንድ ይወደዳል፡፡ አሻንጉሊቶች፣ ድመት፣ ውሻ ወዘተ… የሚወዷቸውና የሚያፈቅሯቸው ይሆናሉ፡፡ መውደዳቸውን የሚገልፁት
    - ወደ እራሣቸው አስጠግተው በማቀፍ፣
    - በእጃቸው ደጋግመው በመዳሰስና በማሻሸት፣
    - የሚወዱትን ሰው ወይም እቃ በመሳምና በመሳሰሉት ናቸው፡፡

**ተግባር 5**

**ሕፃናት ከ8ኛ ወራቸው አካባቢ ጀምረው ያዩትን ነገር አይጠፌነት ይረዳሉ ሲባል ምን ማለት ነው? በምሳሌ በማስደገፍ ግለፁ፡፡**

### 1.17.7 የሕፃንነት ወቅት ማኅበራዊ መዳበር

ማኅበራዊ መዳበር ማለት የአንድን ኅብሰተሰብ ልማድና ባህል ከእራስ ስብዕና ጋር የማዋሀድ ሂደት ነው፡፡ ሕፃናትን ወደ ማኅበራዊ ግንኙነት እንዲያመሩ ግፊት የሚያደርጉባቸው ነገሮች፡

- እንደሌሎች ለመሆን ያለ ፍላጎት (ሌሎችን መቅዳት)፣
- የሌሎችን ፍቅርና መወደድ የማትረፍ ፍላጎትና ስሜት፣
- ቅጣትን የመከላከል ፍላጎት ወዘተ... ናቸው፡፡

የሕፃናት ማኅበራዊ ዕድገት ደረጃዎችን/ሂደቶችን እንደሚከተለው ማቅረብ ይቻላል።

1. ከ 4 - 5 ወራት፡- ሕፃናት ለተለያዩ ሰዎች የተለያዩ ምላሾችን ይሰጣሉ፡፡ ከእናታቸው ጋር ከፍተኛ የሆነ ግንኙነትና ትስስር አላቸው፡፡
2. ከ 6 - 8 ወራት፡- ሕፃናት በዚህ ወቅት የሚኖራቸው ግንኙነት ከዕቃዎችና ከመጫወቻ መጫሪያዎች ጋር ነው፡፡ ከልጆች ጋር አይገናኙም፤ ይዘነጓቸዋል፡፡
3. ከ 9 - 13 ወራት፡ ለሚጫወቱባቸው እቃዎች ትኩረት ያደርጋሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ በመጫወቻ እቃዎች ላይ ከሌሎች ጋር ሲጣሉ ይስተዋላሉ፡፡
4. ከ 14 - 18 ወራት፡ ትኩረታቸው ከመጫወቻ እቃዎች ወደ ቢጤዎቻቸው ይዞራል፡፡

### 4.2.8 የሕፃንነት ወቅት የስነ-ምግባር መዳበር

ህፃናት ክፉውን ከደጉ ወይም መጥፎውን ከጥሩ መለያውን መስፈርት ያላወቁ ናቸው፡፡ ለዚህም ነው ህፃናት ስነ-ምግባራዊ ናቸው ወይም ስነ-ምግባር የጎደላቸው (ኢ-ስነምግባራዊ) ናቸው የምንለው፤ ይልቁንም ደግሞ ስነ-ምግባርን ያላወቁ ናቸው የምንለው፡፡ ህፃናት አንድን ድርጊት ትክክል ወይም ስህተት ነው የሚሉት ከሚያስከትለው ነገር ተነስተው ነው፡፡ ይህም ማለት ድርጊቱ ቅጣት ካስከተለ ስህተት ነው፤ ካላስከተለ ትክክል ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ይህም የሆነው ህፃናት የግንዛቤያቸው የመዳበር ደረጃ ውሱን በመሆኑ ውሳኔያቸው በምክንያት የተደገፈ ስላልሆነ ነው።፡፡

## 1.18 ቀዳማይ የልጅነት ወቅት

የቀዳማይ የልጅነት ዘመን ከሁለት ዓመት መጨረሻ እስከ ስድስት ዓመት ያለውን የልጆች የመዳበር ወቅት ያካትታል፡፡ በዚህ ወቅት ወጣት ልጆች እራሳቸውን ለመቻልና ለራሳቸው ጥንቃቄ ለማድረግ ጥረት ያደርጋሉ፣ ለትምህርት ቤት ዝግጁ የሚያደርጋቸውን ክህሎት ያዳብራሉ፡፡ ብዙውን ጊዜአቸውን በጨዋታ ያሳልፋሉ፡፡

### 1.18.1 የቀዳማይ የልጅነት ወቅት ባህሪያት

በዚህ የመዳበር ወቅት የሚገኙ ልጆች ባህሪያትን ለመግለጽ ወላጆች፣ የትምህርት ባለሙያዎችና የስነ-ባህሪ ባለሙያዎች የተለያየ ስያሜዎችን ተጠቅመዋል፡፡

1. **ወላጆች ለቀዳማይ የልጅነት ዘመን የሰጡት ስያሜ፡-**

አብዛኛዎቹ ወላጆች እንደሚገምቱት የቀዳማይ የልጅነት ወቅትን **የችግር እድሜ** **/Problem age/** ወይም **አስቸጋሪ እድሜ** **/Troublesome age/** ነው ይሉታል፡፡ በእነዚህ እድሜ ክልል ያሉ ልጆች ልዩ የሆነ ስብዕና ይዘው ለማደግ ጥረት የሚያደርጉ ሲሆን ነፃነትም ይሻሉ፡፡ በዚህም የተነሳ የተለያዩ የባህሪ ችግሮች ይታዩባቸዋል፡፡ እነዚህ ለጋ ልጆች አብዛኛውን ጊዜ ጨቅጫቃዎች፣ የማይታዘዙ፣ ሁሉነገራቸው ግራ የሆነ፣ ነጭናጮች ናቸው፡፡ በየጊዜው ከረር ያለ ለቅሶና መሬት ላይ እየተንደፋደፉ በማላዘን ያለቅሳሉ፡፡ ብዙውን ጊዜ በምሽት ህልማቸው መጥፎ ነገር የሚያዩ ሲሆን ቀንም ተጨባጭነት የሌላቸውና አስፈሪ ያልሆኑ ነገሮች ፍርሐት ይለቁባቸዋል፤ ይህም ያስጨንቃቸዋል፡፡

የተወሰኑ ወላጆች ደግሞ የቀዳማይ የልጅነት ወቅትን **የአሻንጉሊት እድሜ** ወይም **የእቃ እቃ ጨዋታ**/Toy age/ይሉታል፡፡ ምክንያቱም ልጆች ከእንቅልፍ ሰዓታቸው ውጪ ያለውን ጊዜአቸውን በሙሉ የሚያሳልፉት ከአሻንጉሊቶቻቸው ጋር በመጫወት መሆኑን በማየት ነው፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የአሻንጉሊት ጨዋታ ከፍተኛ ደረጃ የሚደርሰው በቀዳማይ የልጅነት እድሜ ወቅት እንደሆነና ልጆች ወደ ትምህርት ቤት መግባት ሲጀምሩ የአሻንጉሊት ጨዋታ ቀስ በቀስ እየቀነሰ በመምጣት በሌሎች የጨዋታ ዓይነቶችና በትምህርት ቤት ሥራዎች እንደሚዋጥ ነው፡፡

**የትምህርት ባለሙያዎች ለቀዳማይ የልጅነት እድሜ የሰጡት ስያሜ፡-**

የትምህርት ባለሙያዎች የቀዳማይ የልጅነት ወቅትን **የቅድመ-ትምህርት ቤት እድሜ** /Pre-school age/ ይሉታል፡፡ ይህን ስያሜ የሚጠቁመው የመደበኛውን የትምህርት ቤት እድሜ ከቅድመ-ትምህርት ቤት ዘመን ጋር ለመለየትና በዚህ የእድሜ ክልል ያሉ ልጆች በአካልም ሆነ በአእምሮ መደበኛ ትምህርት ለመቀበል ያልደረሱ መሆናቸውን ለመግለጽ ነው፡፡ ሆኖም በዚህ የእድሜ ክልል ያሉ ልጆች በተለይም ከ 4-6 ዓመት ባለው ጊዜ ለመደበኛ ትምህርት ቅድመ-ዝግጅት በሚደረግባቸው የቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤት የሚገኙ ናቸው። ትምህርቱ በአብዛኛው በመረጃ መሣሪያዎች የሚደገፍ ሲሆን በርካታ ጠቃሚ እውቀቶች የሚተላለፉት በጨዋታ መልክ ነው። ጨዋታው አላማና ግብ ያለው፣ በመሣሪያዎች አቅርቦት የተሟላ ሲሆን የሚካሄደውም ስርዓት አስጠባቂ አዋቂ ባለበት ሁኔታ ነው

2. **የስነ-ባህሪ ምሁራን የሚጠቀሙባቸው ስሞች፡-**

የስነ-ባህሪ ምሁራን የቀዳማይ የልጅነት ዘመንን በሚመለከት የተለያዩ ስሞች በመጠቀም ይጠሯቸዋል፡፡

- **የቅድመ ጓድ ምስረታ እድሜ** /Pre-gang age/፡- ይህ እድሜ ለልጆች ማኅበራዊ ህይወት አስፈላጊ የሆነውን ማኅበራዊ ባህሪ መማሪያ ዘመን ነው፡፡
- **የአሰሳ እድሜ** /Exploring age/፡- ልጆች አካባቢያቸው ምን እንደሆነ፣ እንዴት እንደሚሰራ፣ እንዴት እንደሚዳስሱት፣ እና እነርሱም የአካባቢያቸው አካል እንዴት ሊሆኑ እንደቻሉ ለመረዳት የሚጥሩበት ዘመን በመሆኑ ነው፡፡ አንድ ወሣኝ የሆነ አካባቢን የመረጃ መንገድ ጥያቄ መጠየቅ ነው፡፡
- በዚህ እድሜ ያሉ ልጆች ስለተለያዩ ነገሮች ጥያቄ ይጠይቃሉ፡፡ በዚህ የተነሣ ይህ እድሜ **የመጠይቅ እድሜ** /Questioning age/ በመባል ይታወቃል፡፡
- **የመቅዳት እድሜ** /Imitative age/፡- ይህ ጊዜ ልጆች የአዋቂዎችን አነጋገርና ድርጊት ለመቅዳት ጥረት የሚያደርጉበት ነው፡፡
- ልጆች በጨዋታ አማካኝነት በርካታ የፈጠራ ተግባራት ያከናውናሉ፡፡ በዚህም ምክያት የቀዳማይ የልጅነት ዘመን **የፈጠራ እድሜ** /Creative age/ ይባላል፡፡

### 1.18.2 የቀዳማይ የልጅነት ወቅት አካላዊ መዳበር

አካላዊ እድገት በርካታ ጉዳዮችን የሚያካትት ነው፡፡ እነርሱም፡-

**ሀ.** **የቁመት ለውጥ፡-** ዓመታዊ የቁመት የመጨመሩ መጠን 3 ኢንች ወይም 7.62 ሴንቲ ሜትር ሲሆን በቀዳማይ የልጅነት ዘመን መጨረሻ ላይ ልጆች 46.6 ኢንች ወይም 118.4 ሴንቲ ሜትር ርዝመት ይኖራቸዋል፡፡

ለ. **ክብደት፡-** ዓመታዊ የክብደት መጠን ጭመራው 3.75 ፓውንድ ወይም 1.69 ኪሎግራም ይሆናል፡፡ የቀዳማይ የልጅነት ዘመናቸውን ሲያጠናቅቁ ማለትም በ6 ዓመታቸው ልጆች በውልደት ወቅት የነበራቸው ክብደት በ7 እጥፍ ያድጋል፡፡ በአማካይ ሴቶች 48.5 ፓውንድ ወይም 21.8 ኬሎግራም ያህል ሲመዝኑ ወንዶች ልጆች በአማካይ ከሴቶች በለጥ ያለ 49 ፓውንድ ወይም 22.05 ኪሎግራም ይመዝናሉ፡፡

ሐ. **አካላዊ ሚዛናዊነት፡-** የህፃንነት መልክ ይጠፋል፣ የፊታቸው ክፍል ትንሽ ይሆናል፣ አገጫቸው በጣም ይጎላና ትልቅ ይሆናል፣ አንገታቸው ረጅም ይሆናል፣ ሆዳቸው ጠፍጣፋ ይሆናል፡፡ የእጃቸው ክንድና የእግራቸው ቅልጥም ረጃጅም ይሆናል፡፡ እጃቸውና እግራቸው ከፍተኛ እድገት ይታይበታል፡፡

መ. **አካል አገነባብ፡-** ለመጀመሪያ ጊዜ የልጆች ተክለ-ሰውነት ወይም የአካል አገነባብ ልዩነት ይታይበታል። በዚህም የተነሳ ሶስት ጎልተው የሚታዩ አካላዊ አገነባብ መኖራቸው ተደርሶበታል፡፡

1. **ወፍራም አካላዊ አገነባብ ያላቸው፡-** በስጋ የተሞሉ፣ ድንቡሽቡሽ፣ ክብ ቅርጽ ያላቸው፣ የስብ መጠናቸው ከጡንቻዎች የበለጠ ይሆናል፡፡
2. **በጠንካራ ጡንቻ የተገነባ አካል፡-** ሸንቃጣ ግን ጠንካራ የሆኑና የጡንቻ መጠናቸው ከስብ የበለጠ ነው፡፡
3. **ቀጫጫ ሰውነት ያላቸው፡-** ቆዳቸው ከአጥንታቸው ጋር የተጣበቀ፣ ከሲታዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ልጆች ደግሞ የስብም ሆነ የጡንቻቸው መጠን አነስተኛ የሆነ ነው፡፡

ሠ. **አጥንቶችና ጡንቻዎች፡-** የሰው አጥንት የእድገት አቅጣጫን ተከትሎ በተለያየ መጠንና ቦታ ይጠነክራል /ossify/፡፡ የአጥንት መጠንከር በአብዛኛው በታይሮይድ እጢ የምንጨታ መጠን ይወሰናል፡፡ በዚህም በቀዳማይ የልጅነት ዘመን የልጆች ጡንቻዎች ረጃጅም፣ ጠንካራ እና ከባድ በመሆናቸው የተነሣ ልጆቹ ቀጫጫዎች መስለው ቢታዩም ቅሉ ክብደታቸው ከፍተኛ ነው፡፡ አማካይ አካላዊ ሁኔታ ባለው ሰው ከውልደት እስከ በሳል እድሜ ድረስ የጡንቻዎች ክብደት በ40 እጥፍ ይጨምራል፡፡ እስከ 5 ዓመት እድሜ የጡንቻዎች እድገት ከአካላዊ ክብደት መጨመር ጋር በተዛመደ መጠን ይሆናል፡፡ ከዚያም ከ5-6 ዓመታት ባለው ጊዜ ከፍተኛና ቅጽበታዊ የጡንቻዎች እድገት የሚከሰት ሲሆን 75% የሚሆነው የልጆች የክብደት መጠን መጨመር የሚመጣው ከጡንቻዎች እድገት የተነሳ ነው፡፡ ከዚህ ዕድሜ በኋላ ያለው የደጎራይ የልጅነት ዘመን አልፎ በትልቅነት ዘመን እንደገና የጡንቻዎች እድገት ከፍተኛ ይሆናል፡፡

ረ. **ስብ፡-** ወፍራም አካላዊ አገነባብ ያላቸው ልጆች ከጡንቻ ይልቅ ከፍተኛ የሆነ የስብ ቲሹ ይኖራቸዋል፡፡ በሌላ መልኩ ጠንካራ አካላዊ አገነባብ ያላቸው ልጆች የጡንቻ ቲሹ ከስብ

ቲሹዎቻቸው በጣም የበለጡ ናቸው፡፡ በመጨረሻም ቀጫጫ አካላዊ አገነባብ ያላቸው ልጆች የስብም ሆነ የጡንቻ ቲሹዎቻቸው አነስተኛ ነው፡፡

ሰ. **ጥርስ፡-** ከ2 ዓመት ከአራት ወራት እስከ 2 ዓመት ከስድስት ወራት ባሉት ጊዜ ውስጥ የመጨረሻዎቹ 4 ምስሬ (ወተት) ጥርሶች ይበቅላሉ፡፡ እነርሱም ድሂር-መንጋጋ /back molars/ ይባላሉ፡፡ ከ5 ዓመት ተኩል ጀምሮ የልጆች ምስሬ (ወተቴ) ጥርሶች በቋሚ ጥርሶች መተካት ይጀምራሉ፡፡ ቀድመው የሚወልቁትም ሆነ የሚተኩት የፊት ጥርሶች ናቸው፡፡ በቀዳማይ የልጅነት ዘመን መጨረሻ ላይ ልጆች በአብዛኛው አንድ ወይም ሁለት ቋሚ (ዘላቂ) ጥርሶች ፊት ለፊት እና ለቋሚ ጥርስ መብቀያ የሚሆኑ ባዶ ቦታዎች ይኖራቸዋል፡፡

### 1.18.3 የቀዳማይ የልጅነት ወቅት የእንቅስቃሴ መዳበር

ቀዳማይ የልጅነት ዘመን ክህሎቶችን የመማሪያ ምቹ ወቅት ነው፡፡ ምክንያቱም፡-

1. ለጋ ልጆች ነገሮችን መደጋገም የሚወዱና ትክክለኛውን ነገር እስካላደረጉ ድረስ መደጋገም የማይሰለቹ በመሆናቸው፣
2. ልጆች አዲስ ነገር የማድረግ ፍላጎት ያላቸው ከመሆናቸውም በላይ በጓደኞቻቸው መሸሚጠጥ ወይም ችግር ይደርስብናል የሚል ፍርሃት ስለሌለባቸው፣
3. ልጆች በቀላሉ በፍጥነት ክህሎትን መማር መቻላቸው ናቸው፡፡ ለዚህም የአካላቸው እንደልብ መተጣጠፍ ወይም መታዘዝ እና ቀደም ባለው የህይወት ዘመናቸው ያካበቱት ክህሎት ውሱን ከመሆኑም የተነሳ አዲስ በሚማሩት ላይ የሚኖረው አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነት አነስተኛ ስለሚሆን ነው፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ሶስት ምክንያቶች የተነሳ የቀዳማይ ልጅነት ዘመን የክህሎት ማስተማሪየ ወቅት ሊባል ይችላል፡፡ ዋና ዋናዎቹን የቀዳማይ ልጅነት ዘመን ክህሎቶችን በሁለት መክፈል እንችላለን፡፡

ሀ. **የእጅ ክህሎት**

- ራስን መመገብና ማልበስ
- ፀጉርን መታጠብና ማበጠር
- ኳስ መወርወርና መያዝ
- ስዕሎችን መቀባት
- የሰውና እንስሳት ስዕል መሳል

ለ. **የእግር ክህሎት**

- በአንድ እግር መዝለል
- በፍጥነት መራመድ
- ተንሸራታች ነገሮችን መንዳት
- ዛፍና መሰል ነገሮችን መውጣትና መውረድ

- በእጅ እየታገዙ መዋኘትና ሳይክል መጋለብ

የእግር ክህሎቶች በተባሉት ውስጥ እጅ በተወሰነ ደረጃ አስተዋፅኦ ያለው ቢሆንም አብዛኛው ሥራ የእግር በመሆኑ በዚሁ መሠረት ተመድበዋል፡፡

### 1.18.4 በቀዳማይ የልጅነት ወቅት አእምሮአዊ መዳበር

**እንደ ጂን ፒያገ** (Hurlock, 1980; Berger, 1986; Dacey and Travers, 2004) **አገላለጽ የቀዳማይ የልጅነት ወቅት ልጆች በሁለተኛው የአእምሮአዊ መዳበር ደረጃ ማለትም አመክንዮታዊ** (በቅድመ-ስሌታዊ) **ነገሮችን የመረዳት ደረጃ** (Preoperational stage of cognitive development) **ላይ ይገኛሉ ፡፡**

በዚህ የአእምሮአዊ መዳበር ደረጃ ላይ የሚገኙ ልጆች የሚከተሉትን ባህሪያት ያሳያሉ፡፡

- ቋንቋንና ምልክቶችን በመጠቀም አንዳንድ ችግሮችን ለመፍታት ጥረት ያደርጋሉ፡፡
- አካባቢያቸውን ለመረዳት ከፍተኛ ፍላጎት ያሳያሉ፡፡
- አካባቢያቸውን ለመረዳት ብዙ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ፡፡
- የእቃዎችን ምስል በአእምሮአቸው በመቅረጽ በወቅቱ በአካባቢያቸው በሌሉና በማይታዩ ነገሮች ላይ ማሰብ ይችላል፡፡
- የሌሎችን አስተያየት የማይቀበሉበት (Egocentrism) ሁኔታ ይታያል፡፡ ምክንያቶችም ሌሎች ሰዎች እንደነሱ የሚያስቡ ስለማይመስላቸውና በዚህ አለም ያለ አስተሳሰብ የነሱ ብቻ ስለሚመስላቸው ነው፡፡
- ነጠላ አትኩሮት (Centration) ይታያል፡፡
- የምክንያትና ውጤት ግንኙነትን ያለመረዳት ይታያል፡፡
- በቡድን የተመደቡ እቃዎች በምን መሠረትነት እንደተመደቡ ለመረዳት መቸገር ይታያል፡፡ እንዲመድቡም ሲጠየቁ በውጪያዊ ገጽታቸው ብቻ መመደብ ይታያል፡፡ **ለምሣሌ** እቃዎችን ማለትም ኳስ፣ ብርቱካን፣ ሙዝ፣ አሎሎ አንድ ላይ አድርገን በሁለት እንዲከፍሉ ብናዝዛቸው ውጫዊ ሁኔታቸውን ማለትም ድቡልቡልነታቸውን ብቻ በማየት ኳስ፣ ብርቱካንና አሉሎን በአንድ ወገን ሙዝን ለብቻው በሌላ ወገን ያስቀምጡልናል፡፡
- ሁሉም ነገር በሰው የተሰራ ነው ብሎ ማሰብ ይታያል።
- አንድ አይነት መጠን ያለውን ፈሳሽ የተለያየ መጠን ባለው እቃ ውስጥ ብናስቀምጠው የፈሳሹ መጠን እንደማይለወጥ ያለመረዳት ሁኔታ ይታያል።
- ህይወት ካላቸው ነገሮች ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ግን ሕይወት የሌላቸውን ነነገሮች ሕይወት እንዳላቸው አድርጎ የመቁጠር ሁኔታ (Animism)ይታያል። ፡፡ **ለምሳሌ** ጨረቃና አሻንጉሊት በቀዳማይ የልጅነት ዘመን ልጅ ላይ በተደረገ ጥናታዊ ቃለ ምልልስ ጨረቃ ሕይወት አላት ወይ? አዎ፡፡ እንዴት አወቅክ? እኔ ስሄድ ትሄዳለች ስቆም ትቆማለች፡፡ ለምን ይመስልሃል የምትሄደው? የምናገረውን ለመስማት ነዋ ብሏል፡፡

**በቀዳማይ የልጅነት ዘመን በአንዳንድ ወሣኝ በሆኑ ፅንሰ-ሃሳቦች ላይ ልጆች ያላቸው አመለካከት**

- **ሕይወት፡-** በዚህ የልጅነት ዘመን አሻንጉሊቶችና ፀጉራም የእንስሳት ምስሎች በሙሉ ሕይወት እንዳላቸው ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ልጆች ሕይወት ያላቸውንና የሌላቸውን ነገሮች መረዳት ይሳናቸዋል፡፡
- **ሞት፡-**ከእነርሱ የራቀ ወይም የተለየን ነገር በሙሉ እንደ ሞተ ይቆጥሩታል፡፡ የሞትን ተፈጻሚነት አይገነዘቡትም፡፡
- **ቦታ፡-** ቅርብ ቦታን እንጅ ሩቅን መረዳት አይችሉም፡፡ ሆኖም ግራና ቀኛቸውን በትክክል ያውቃሉ፡፡
- **ክብደት፡-** በትምህርት ቤት ሕይወታቸው የተለያዩ የክብደት መለኪያዎችንና የክብደት ምንጭ እስከሚማሩ ድረስ የክብደት መለኪያቸው መጠን ነው፡፡ በእነርሱ ግምት ትልቅ እቃ ከፍተኛ ክብደት ሲኖረው መጠኑ አነስተኛ የሆነ ግን ትንሽ ክብደት ይኖረዋል፡፡ ሆኖም ይህ የመጠን መስፈሪያነት ተጨባጭና ትክክለኛ አይደለም፡፡ የዚህ ምክንያትም ትልቅ እቃ ትንሽ ክብደት፣ ትንሽ እቃ ደግሞ ከፍተኛ ክብደት ሊኖረው ስለሚችል ነው። በዚህ ዕድሜ ክልል ላሉ ልጆች ፒያጀት ያቀረቡት ጥያቄ ከአንድ ኪሎ ጥጥና ከአንድ ኪሎ ጨው የቱ ይከብዳል? የሚል ሲሆን የልጆቹ ምላሽ ጥጥ ይከብዳል የሚል ነበር፡፡ ነገር ግን ሁለቱም እኩል ናቸው፡፡
- **ጊዜ፡-** ልጆች የአንድን ሰዓት ርዝመት ወይም በአንድ ሰዓት ምን ያህል ተግባራት ማከናወን እንደሚችሉ አያውቁም፡፡ አብዛኛዎቹ የ4 እና 5 ዓመት ልጆች የሳምንቱን ቀናት በትክክል መጥራትና ማወቅ ሲችሉ የ6 ዓመት ልጆች ደግሞ ወራቶችን፣ ወቅቶችንና ዓመትን በትክክል መረዳት ይችላሉ፡፡

### 1.18.5 የቀዳማይ የልጅነት ወቅት የቋንቋ መዳበር

በቀዳማይ የልጅነት ዘመን ልጆች የንግግር ችሎታቸውን ለማዳበር ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ ይስተዋላል፡፡ ምክንያቶቹም፡-

1. የንግግር ችሎታ ለማኀበራዊ ህይወት መሳካት ጠቃሚ መሳሪያ በመሆኑ ሲሆን ያላቸው ማኀበራዊ ተቀባይነት የንግግር ችሎታ ከሌላቸው ይልቅ ያማረ ነው፡፡
2. የንግግር ችሎታ አንፃራዊ በሆነ መልኩም ቢሆን ከቤተሰብ ተፅዕኖ ነፃ እንዲሆኑ የሚረዳ መሳሪያ ነው፡፡ ሀሳባቸውንና ፍላጎታቸውን በንግግር አማካይነት ለሌሎች መግለጽ የማይችሉ ልጆች ሁልጊዜ እንደጨቅላ ወይም ያልበሰሉ ልጆች ስለሚቆጠሩ ቤተሰብ ልጆች የሚፈልጉትን በነፃነት መንቀሳቀስንና ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር አብረው መጫወትን አይፈቅዱላቸውም፡፡ በተቃራኒው ግን ልጆች ሀሳባቸውን የመግለጽ ችሎታው ካላቸው እንደአደጉና እንደበሰሉ በመገመት በተወሰነ ደረጃ የመንቀሣቀስ ነፃነት ይሰጣቸዋል፡፡

#### 1.18.5.1 በቋንቋ መማር ሂደት ውስጥ ያሉ ጠቃሚ ደረጃዎች

በንግግር ሂደት ውስጥ የቋነቋ ትምህርት ሶስት ደረጃዎችን ተከትሎ የሚያድግ ነው፡፡ እነርሱም፡-

1. **ቃላትን በአግባቡ ማንበብ፡-** በአደጉ ሀገሮች ልጆች ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ለሊጋ ልጆች አስቸጋሪ የሆኑ ድምፆች /sounds/ ወይም ድርብ ድምፆች /sound combinations/ እንዳሉ ተደርሶበታል፡፡ እነዚህም በአብዛኛው የተናባቢ ፊደላት ድምፆች ሲሆኑ እንደ ዜድ /Z/፣ ደብሊው /W/፣ ዲ /D/፣ ኤስ /S/፣ እና ኪው /Q/ ናቸው፡፡ ድርብ ድርብርብ ድምፆችን በሚመለከት ደግሞ እንደ ኤስቲ /St/፣ ኤስቲአር /Str/፣ ዲአር /Dr/ እና ቲኤል /tl/ የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ማዳመጥ ብሎም ወላጆች እነዚህን ስህተቶች ለማረም የሚያደርጉት ጥረት ችግሩን በወቅቱ ሊቀርፈው እንደሚችል ይታመናል፡፡
2. **ቃላት ምሥረታ፡-** አዳዲስ ቃላትን በየጊዜው ስለሚማሩ የልጆች ቃላት ክምችት ከጊዜ ወደ ጊዜ በፈጣን ሁኔታ እድገት ያሳያል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ልጆች የሚማሯቸው ቃላት አጠቃላይ ባህሪ ያላቸው እንደሆኑና እያደጉ ሲመጡ ግን የቃላቱ ሁኔታም ሆነ አጠቃቀማቸው ለውጥ እንደሚኖረው ተገልጿል፡፡ በዚህ እድሜ ክልል የሚነገሩ ቃላት እንደ አባባ፣ እማማ፣ ስጠኝ፣ እንካ፣ ጥሩ፣ መጥፎ፣ የመሳሰሉት ናቸው፡፡
3. **የዓረፍተ-ነገሮች ምስረታ፡-** ከሁለት ዓመት እድሜ ጀምሮ ልጆች ሁለት ቃላትን በማጣመር አረፍተ ነገር በመሥራት ሃሣባቸውን መግለጽ ይጀምራሉ፡፡ የአረፍተ-ነገሮቹ ይዘት ሲታይ ስምና ግስ ብቻ ያላቸው የፆታ ደረጃን የማይገልፁ ናቸው፡፡ ለምሳሌ አባባ መጣ ካለ እማማ መጣ ብሎ ይናገራል፡፡ በቀዳማይ የልጅነት ዘመን መጨረሻ ላይ ልጆች ከ 6-8 ቃላትን ያቀፉና ሁሉንም የንግግር ክፍሎች ያካተቱ ዓረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡ ዓረፍተ ነገር ምሥረታ ለልጆች በጣም አስቸጋሪና ብዙውን ጊዜ ስህተቶች የሚስተዋሉበት የንግግር ትምህርት ደረጃ ነው፡፡ ሆኖም ከ5 ዓመት በኋላ ዓረፍተ ነገሮቹ እየተስተካከሉ ይመጣሉ፡፡ ልጆች ከሚመሰርቷቸው ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በአብዛኛው የሚቀርቡት በጥያቄ መልክ ነው፡፡ በማንኛውም እድሜ ያሉ ልጆች የሚመሰርቷቸው ዓረፍተ ነገሮች ርዝመትና ይዘቱ ከልጅ ልጅ የተለያየ ነው፡፡ ብሩህ አእምሮ ያላቸውና ከፍተኛ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ካላቸው ቤተሰብ የመጡ ልጆች ረጅምና ውስብስብ /complex/ ወይም በርካታ ቃላትን ያጣመረ ዓረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡ ልጆችን የውጭ ቋንቋ ማስተማሪያ ወሣኝ እድሜ ቀዳማይ የልጅነት ዘመን ነው፡፡ ምክንያቱም ቃላትን በትክክል ለማንበብና ለማወቅ የሚችሉት በዚህ ጊዜ በመሆኑ ነው፡፡

#### 1.18.5.2 ለንግግር አስፈላጊ ነገሮች

1. **አካላዊ ዝግጅት፡-** የንግግር ችሎታ ለንግግር አስፈላጊ በሆኑ አካላዊ ክፍሎች ብስለት ይወሰናል፡፡ በውልደት ወቅት የድምፅ ቱቦ አጭር ሲሆን ላንቃ /Plate/ ጠፍጣፋ ነው፡፡ እንዲሁም ምላስ ከድምፅ ቱቦ ጋር ሲነፃፀር በጣም ትልቅ ነው፡፡ ለንግግር የሚያስፈልጉ

ነርቮችና ጡንቻዎች እስኪበለፅጉ ድረስ ድምፅ ማውጣት አስቸጋሪ ነው፡፡ ስለዚህ ለንግግር አስፈላጊ የሆኑ የአካል ክፍሎች እድገት ለንግግር ወሣኝነት አለው።፡

2. **ለንግግር የሚያስችል የአእምሮ ዝግጅት፡-** ንግግር በአእምሮ ብስለት ይወሰናል፡፡ በተለይም አንዳኝ የአእምሮ ቦታ /Association area of brain/የሚባለው የአእምሮ ክፍል ብስለት በጣም አስፈላጊ ነው። የአእምሮ ለንግግር ዝግጅት ከ12-18 ወራት ከውልደት በኋላ ባለው ጊዜ የሚጀምር ሲሆን ይህም ንግግር የማስተማሪያ ወቅት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
3. **ጥሩ የንግግር ምሣሌ የሚሆን ሰው ማግኘት፡-** ልጆች ቃላትን በትክክል እንዲያነቡ በኋላም በትክክለኛ ቃላት ምሥረታ እንዲያገናኙአቸው በቅድሚያ ጥሩ ተምሣሌት የሚሆን የተቀነባበረ ንግግር መስማት ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህ የመልካም ወይም የተስተካከለ ንግግር አርአያ ወላጆች፣ በአካባቢያቸው ያሉ ሰዎች፣ የሬዲዮና ቴሌቪዥን ዜና አንባቢዎችና የተለያዩ መርሃ-ግብር አዘጋጆች ወይም በመድረክ ላይ የሚሰሩ ተዋንያኖች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ተገቢ አርአያ ማጣት ያልተስተካከለ ሃሣብ የመግለጽ ልምድ መከሰተንና የንግግር ችሎታ ማነስን ያስከትላል፡፡
4. **የልምምድ እድል መኖር፡-** ሃሣቦችን የመግለጽ ልምምድ እንዲያደርጉ የተገደቡ ልጆች ብስጩና ቁጡ ይሆናሉ፡፡ ይህም ንግግርን ለመማር በሚኖራቸው ጉጉት ላይ ጫና ያሣድራል፡፡
5. **መነቃቃት፡-** ልጆች ፍላጎታቸውን ሳይናገሩ የሚሟላላቸው ከሆነ ለቅሶ ብሎም አካላዊ እንቅስቃሴ የንግግርን ቦታ ከተካ ለንግግር የሚኖራቸው መነቃቃት አነስተኛ ይሆናል፡፡
6. **ምክር፡-** የንግግር ችሎታን በምክር ማሣደግ ይቻላል፡፡ እነዚህ የምክር ዓይነቶች፡-
   ሀ. ተገቢ ምሣሌ/አርአያ ማቅረብ፣
   ለ. ቃላትን በዝግታና በግልጽ በመናገር ልጆች እንዲረዱቸው ማድረግ፣ እና
   ሐ. ምሣሌውን/አርአያውን በመከተል እንዲናገሩ ማድረግና ስህተቶችን በየጊዜው ማረም ናቸው፡፡

የቋንቋ መዳበር ሂደትን የሚያሣይ ሰንጠረዥ (Morgan et.al, 1986)

| ተ.ቁ. | ደረጃዎች | የእድገቱ ባህሪ ወይም ገጽታ | የንግግር ናሙናዎች |
|---|---|---|---|
| 1 | አረፍተ ነገር መሰል ቃላት መመስረት /Sentence like word/ ከ12 - 18 ወራት ዕድሜ | ቃላትን ከድምጽ አልባ አካላዊ እንቅስቃሴ ጋር በማዋሀድ ሃሣብን መግለጽ | - “እማማ”<br>- “እማማ?” |
| 2 | መለስተኛ ለውጥ ማድረግ /Modification/ ከ18 ወራት እስከ 2 ዓመት | በዋነኞቹ ቃላት ላይ መጠነኛ ለውጥ በማድረግ የተለያዩ ዓረፍተ ነገሮችን መመስረት፣ እንደ አድናቆታዊ፣ ጥያቄአዊ፣ አጋኖአዊ አፍራሽ የመሳሰሉትን | ያልተሟሉና በሁለት ቃላት የተገነቡ ዓረፍተ ነገሮች መሥራት ምሣሌ፡- -<br>- ቆንጆ ልጅ<br>- አባባ የት? |
| 3 | ማቀነባበር ከ2 - 3 ዓመታት | የሚመሰርቷቸው ዓረፍተ ነገሮች ባለቤትና ተሣቢ ያላቸው ናቸው፡፡ | አባቴ የት ነው?<br>ተጨማሪ ወተት |

| ተ.ቁ. | ደረጃዎች | የእድገቱ ባህሪ ወይም ገጽታ | የንግግር ናሙናዎች |
|---|---|---|---|
| | | | እፈልጋለሁ |
| 4 | የዓረፍተ ነገር አገባብ ለውጥ/Operational change/ ከ2½-4 ዓመታት | በሚመሰርቱት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ አንዳንድ ነገሮችን መጨመር፣ በተለያየ መልኩ ማቀነባበር የሚታይበት ደረጃ | - እኔ መጫዎት አልችልም<br>- አንብበው የእኔ መጽሐፍ ነው፡፡ |
| 5 | የተለያዩ የአረፍተ-ነገር ክፍሎችን በተለያየ መልኩ ማከፋፈል /Categorization/ 3½ - 7 ዓመታት | የቃላት ክፍሎች (ስም፣ ግሶች እና መስተፃምሮች) በተለያየ መልኩ መከፋፈል | - ጥቂት ወተት እፈልጋለሁ<br>- ወደ መጋዘን ውሰደኝ |
| 6 | ውስብስብ ቅንብር /Complex structure/ ከ5 - 10 ዓመታት | በውስብስብ ቅንብሮች መካከል ያሉትን ልዩነቶች መገንዘብ መቻል | - ሰዓት ስንት እንደሆነ መጠየቅ<br>- እሷን ለመርዳት ቃል ገብቷል፡፡ |

#### 1.18.5.3 ንግግርን ለመማር በሚደረገው ሂደት ልዩነት የሚፈጥሩ ሁኔታዎች

ቀጥሎ በምንገልፃቸው በርካታ ምክንያቶች የተነሣ ሁሉም ልጆች ያላቸው የንግግር ችሎታ እኩል አይደለም፡፡ እነዚህን ምክንያቶች በመያዝ በነባራዊው ዓለም ያለውን የቋንቋ ችሎታ መለያየት መገመት እንደሚቻል ይታመናል፡፡

1. **ጤና፡-** የማኅበረሰቡ አካል ለመሆን ባላቸው ከፍተኛ ጉጉት የተነሳ ጤናማ ግንኙነት በንግግር አማካኝነት ለመመስረት ሲሉ ጤናማ ልጆች ንግግርን ቶሎ ይማራሉ፡፡ ጤናማ ያልሆኑት ግን ንግግርን የሚማሩት ዘግይተው ነው፡፡
2. **የአእምሮ ችሎታ፡-** ብሩህ አእምሮ ያላቸው ልጆች ቀድመው የንግግር ክህሎቶችን የሚማሩ ሲሆን ደካማ የአእምሮ ችሎታ ካላቸው በጣም የበለጠ የቋንቋ እድገት ያሳያሉ፡፡
3. **የቤተሰብ የገቢ ምንጭ፡-** ከፍተኛ የገቢ ምንጭ ካላቸው ቤተሰቦች የመጡ ልጆች ቀድመው መናገርን ይማራሉ፣ ሃሳባቸውን በተሻለ ሁኔታ መግለጽ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ልጆች ዝቅተኛ የገቢ ምንጭ ደረጃ ካላቸው ቤተሰብ ከሚመጡ ልጆች የበለጠ ይናገራሉ፡፡ ይህም የሚሆነው ከከፍተኛ የገቢ ምንጭ ካላቸው ቤተሰብ የሚመጡ ልጆች ከፍተኛ የሆነ ማበረታታትና ምክር ከወላጆቻቸው ስለሚለገሳቸው ነው፡፡
4. **ጾታ፡-** ወንዶች በአማካይ በንግግር ችሎታቸው ከሴቶች ወደኋላ የቀሩ ናቸው፡፡ በማንኛውም ዕድሜ የወንዶች ልጆች ዓረፍተ-ነገሮች አጫጭሮችና ሰዋሰዋዊ ትክክለኛነታቸውም ዝቅተኛ ነው፡፡ በተጨማሪም የቃላት ክምችታቸው አነስተኛ ከመሆኑም በላይ በትክክል የማንበብ ሁኔታ ከልጃገረዶች ጋር ሲነፃፀር ያልተስተካከለ ነው፡፡

5. **የግንኙነት ፍላጎት፡-** ልጆች ከሌሎች ጋር የመወያየት ፍላጎታቸው ከፍተኛ ከሆነ ንግግርን ለመማር ያላቸው መገፋፋትም ያንኑ ያህል ከፍተኛ ይሆናል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ በተዘዋዋሪ ልጆች ያላቸውን ጊዜና ጥረት በማስተባበር ንግግርን እንዲማሩ ያደርጋቸዋል፡፡
6. **መበረታታት፡-** ልጆች እንዲናገሩ የሚበረታቱ ከሆነ ማለትም ከእነሱ ጋር በመናገርና ምላሽ እንዲሰጡ ጥረት የሚደረግ ከሆነ ልጆቹ በቶሎ መናገር እንዲችሉ የሚያደርግ ሲሆን የንግግር ችሎታቸውም የተስተካከለ ይሆናል፡፡
7. **የቤተሰብ መጠን፡-** የቤተሰቡ ብቸኛ ልጅ ወይም አነስተኛ የቤተሰብ አባላት ካሉት ቤተሰብ የመጡ ልጆች አብዛኛውን ጊዜ ቀድመው የመናገር ችሎታ ያዳብራሉ፡፡ ይህም የሚሆነው ቤተሰቡ ጊዜአቸውን መስዋዕት በማድረግ ንግግርን ስለሚያስተምሯቸው ሲሆን በርካታ የቤተሰብ አባላት ከአሉ ግን የቤተሰቡ አባላት የየራሣቸውን ቡድን በመፍጠር ስለሚጫወቱ ህፃናት እስከመኖራቸውም ሊዘነጉ ይችላሉ፡፡ ይህም በንግግር ችሎታቸው ላይ ችግር ያስከትላል፡፡
8. **የውልደት ቅደም ተከተል፡-** በአንድ ዓይነት የእድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ ልጆች ሲነፃፀሩ የመጀመሪያ ልጆች ከእነሱ ቀጥለው ከተወለዱት የተሻለ የንግግር ችሎታ ይኖራቸዋል፡፡ ምክንያቱም ወላጆች በርካታ ጊዜያቸውን የመጀመሪያ ልጃቸውን ንግግር ለማስተማር ስለሚያውሉና ስለሚያበረታቷቸው ነው፡፡
9. **የልጆች አስተዳደግ ስርዓት፡-** አምባገነናዊ የልጆች አስተዳደግ የሚከተሉ ወላጆች እንደሚያምኑት “ልጆች መታየት እንጅ መስማት የለባቸውም” /Children should be seen but not heard/ የሚሉ ስለሆነ ልጆቻቸውን ንግግር እንዲያስተምሩ አመለካከታቸው ይገድባቸዋል፡፡ በተቃራኒው ወላጆች ለቀቅ ያለና ዲሞክራሲያዊ የልጆች አስተዳደግ የሚከተሉ ከሆነ ልጆቻቸውን ንግግር ለማስተማር የሚያስችላቸው ሁኔታ አለ፡፡ በዚህም የተነሣ የልጆቻቸው የቋንቋ ችሎታ ከፍተኛ ነው፡፡
10. **ብዙሃ ውልደት፡-** በአንድ ጊዜ የተወለዱ በርካታ ህፃናት በእድገታቸው ወቅት የእርስ በርስ ግንኙነታቸው የጎላ ስለሚሆን የንግግር እድገታቸው ከነጠላ ሕፃናት ጋር ሲነፃፀር ኋላ ቀር ነው፡፡
11. **ከእድሜ አቻዎቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት፡-** ልጆች ከእድሜ አቻዎቻቸው ጋር ያላቸዉ ግንኙነት ከፍተኛ ከሆነ ተቀባይነት እንዲኖራቸውም ጭንቀታቸው ከፍተኛ ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ የንግግር ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ያነቃቃቸዋል፡፡
12. **ስብዕና /Personality/:-** የተስተካከለ ስብዕና መሠረት ያላቸው ልጆች የስብዕና ችግር ካለባቸው ልጆች ይልቅ በጥራቱም ሆነ በመጠኑ የተሻለ ንግግር ያደርጋሉ፡፡ ንግግር በመሠረቱ የአእምሮ ጤንነት ምልክት እንደሆነ ይታመናል፡፡

13. **ሁለት ቋንቋ መናገር** /Bilingualism/፡- በቤተሰብ ውስጥ የሚነገረው ቋንቋ ኅብረተሰቡ ከሚናገረው የተለየ ከሆነ ልጆች ከእድሜ አቻዎቻቸውና ከአዋቂዎች ጋር ከቤታቸው ውጪ በአግባቡ መናገር ይሳናቸዋል፡፡ ይህም የሚሆነው የሁለቱ ቋንቋዎች ቃላት ግጭት በመፍጠር ስለሚያስቸግሯቸው ነው፡፡

### 1.18.6 የቀዳማይ የልጅነት ወቅት ኃይለ ስሜት መዳበር

በዚህ ዕድሜ ያሉ ልጆች ከወላጆቻቸው ትኩረት ውጭ እየሆኑ ስለሚመጡ፣ኃይለ-ስሜታቸው አሉታዊ ከመሆኑም በላይ የባህሪ ችግሮች ይታይባቸዋል፡፡ እነዚህን ልጆች መምራት፣ መምከርም ሆነ አብሮ መሆን አስቸጋሪ ነው፡፡ በዚህ እድሜ ዘመን ጎልተው የሚታዩ ኃይለ-ስሜቶች የሚከተሉት ሲሆኑ ለአቀራረብ ያመች ዘንድ በሰንጠረዥ መልክ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

| ተ.ቁ | የኃይለ-ስሜቶች ዓይነት | መንስኤው | የኃይለ-ስሜቶች መግለጫ |
|---|---|---|---|
| 1 | ቁጣ /Anger/ | በጨዋታ መጫሪያዎች የተነሣ ከሌሎች ልጆች ጋር መጣላት፣ የፍላጎት መገደብ ወ.ዘ.ተ | እያለቀሱ መሬት ላይ መንፈራፈር፣ ማጉረምረም፣ መምታት፣ ወደ ላይ መዝለልና መውደቅ፣ እጅና እግራቸውን ማወናጨፍ ወዘተ.. |
| 2 | ፍርሃት /Fear/ | የአስፈሪ ነገሮች ልምዶች /Conditioned fear/፣ የሌሎችን ፍርሃት መቅዳት፣ አስደሳች ያልሆኑ ነገሮችን ማስታወስ፣ አስፈሪ ታሪኮች፣ ስዕሎች፣ በሬዲዮና ቴሌቪዥን የተላለፉ አስፈሪ ፕሮግራሞች ወ.ዘ.ተ. | በመጀመሪያ ልጆች ለአስፈሪ ነገሮች የሚሰጡት ምላሽ ጭንቀት ወይም መረበሽ ነው፡፡ ቀስ በቀስ ግን ለአስፈሪው ነገር ተመጣጣኝና ተመሳሳይ ምላሽ እንደ መሮጥ፣ መደበቅ፣ ማልቀስ፣ የሚያስፈራውን ነገር ለማስወገድ መጣር ይታይባቸዋል፡፡ |
| 3 | ቅናት /Jealousy/ | ተከታዩ አዲስ ህፃን መወለድ የቅናት ዋነኛው መንስኤ ሲሆን ምክንያቱም የቤተሰቡን ፍቅርና ይደረግለት የነበረውን እንክብካቤ ሁሉ የሚሻማው መሆኑን በመረዳት ይሆናል፡፡ | በግልጽ ቅናታቸውን የሚገልፁ ሲሆን መገለጫ መንገዳቸው<br>- እንደ ህፃን በማልቀስ<br>- አልጋቸው ላይ መሽናት<br>- የታመሙ ማስመሰል፣ አለመታዘዝ ወይም ሕግጋትን መጣስ ናቸው፡፡ |
| 4 | መደነቅ /curiosity | አዲስ ነገሮችን ማየት፣ የራሣቸውንና የሌሎችን የሰውነት አሰራር መቃኘት | በመጀመሪያ የሚያስደንቃቸውን ነገር ይዘው ይደሰታሉ፤ እያደጉ ሲመጡ በኅብረተሰቡ ግፊትና በሚሰነዘርባቸው ቅጣት የተነሳ መደነቃቸውን በተለያዩ ጥያቄዎች ይገልፃሉ፡፡ |
| 5 | ምቀኝነት /Envy/ | የሌሎች ችሎታ ከእነሱ ተሽሎ መገኘትና እነሱ የሌላቸው ነገር ሌሎች ልጆች ኖሮአቸው ማየት | - ለምን እኔ የለኝም በማለት ፍላጎታቸውን ለወላጆቻቸው መጠየቅ<br>- የሌላቸው ነገር ተከፍሎ እንዲሰጣቸው ማመልከት |
| 6 | መደሰት /Joy/ | - የአካላዊ ደህንነታቸው መጠበቅ<br>- አስቸጋሪ ወይም ከባድ የመሰላቸውን ተግባር ማከናወን<br>- ከእድሜ አቻዎቻቸው በልጠው | - ፈገግታና ሳቅ<br>- ማጨብጨብ<br>- ወደ ላይ መዝለል<br>- ያስደሰታቸውን ሰውም ሆነ |

| ተ.ቁ | የኃይል-ስሜቶች ዓይነት | መንስኤው | የኃይል-ስሜቶች መግለጫ |
|---|---|---|---|
| | | መገናት | እንስሳትን ማቀፍ |
| 7 | ሃዘን /Grief/ | የሚወዱትንና ለእነሱ ጠቃሚ የሆነን ሰውም ሆነ መጨወቻ ማጣት | - ለቅሶ<br>- በመደበኛ እንቅስቃሴአቸው ላይ ፍላጎት ማጣት<br>- የምግብ ፍላጎት ማጣት፣ የእንቅልፍ ጊዜአቸው ማነስ ወዘተ |
| 8 | ማፍቀር /መዉደድ | ሰዎችንና መጫወቻቸውን ይወዷቸዋል | - በቃላት የሚወዱትን ነገር መግለጽ<br>- መሳም |

### 1.18.7 የቀደማይ ልጅነት ወቅት ማኅበራዊ መዳበር

ማኅበራዊ መዳበር እርስ በርሳቸው የተደጋገፉ ሶስት ሂደቶችን የሚያካትት ነው፡፡ እነርሱም፡-

1. **ኅብረተሰቡ እንደሚቀበለው ማድረግ መማር፡-** እያንዳንዱ ኅበረተሰብ አባላቱ እንዲያደርጉ የሚጠበቅባቸውን ተግባራት መለኪያ መስፈርት አለው፡፡ በዚህም ምክንያት ልጆች እነዚህን ኅብረተሰቡ የተቀበላቸውን ነገሮች እንዲያውቁ ብቻ ሳይሆን ባህሪያቸውንም ከእነዚህ መስፈርቶች አኳያ እንዲቀርቡ ይጠብቅባቸዋል፡፡
2. **ተቀባይነት ያላቸውን ማኅበራዊ ሚናዎች መጫወት፡-** በማንኛውም ማኅበረሰብ በጥንቃቄ የተቀረፁና አባላቱ እንዲያከናውኗቸው የሚጠበቁ ባህላዊ ባህርያት አሉ፡፡ ለወላጆች፣ ለልጆች፣ ለመምህራን፣ ለተማሪዎች ወ.ዘ.ተ. የተሰጡ ተቀባይነት ያላቸው ሚናዎችም እንዳሉ ይታመናል፡፡ ልጆች ድርሻቸውን እንዲወጡ ይጠበቃሉ፡፡
3. **የማኅበረሰባዊ አመለካከት እድገት፡-** ለማኅበራዊነት ወሣኙ ጉዳይ ልጆች ሰዎችንና ማኅበራዊ እንቅስቃሴን መውደድ ይሆናል፡፡ ጥሩ ማኅበራዊ ውህደት እና ተቀባይነት ካላቸው በመረጡት ቡድን ዘንድ አባል መሆን አይሳናቸውም፡፡

ከሁለት ዓመታቸው በኋላ የቀዳማይ ልጅነት ዘመን ልጆች አንዳንድ ቀላል ተግባራትን ከአዋቂዎች ጋር ተባብረው መሥራት ይሞክራሉ፡፡ ለምሣሌ እንደመታጠብና ልብስ መልበስ ያሉ ተግባራት ይገኙበታል፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ ልጆች ከተራ የማኅበረሰቡ አባልነት ወደንቁ አባልነት ይዘዋወራሉ፡፡ ማኅበራዊ ግንኙነት ጀማሪም ይሆናሉ፡፡ እናም ለሰዎች ከፍተኛ ፍቅር ያሳያሉ፣ ፍቅሩም ያድርባቸዋል፡፡

በዚህ የልጅነት ዘመን ልጆች ማኅበራዊ ግንኙነትን እንዴት መመስረት እንደሚችሉ ከቤተሰቦቻቸው ውጪ ካሉ ሰዎች በተለይ ከእድሜ አቻዎቻቸው ጋር እንዴት አድርገው መኖር እንደሚችሉ ይማራሉ፡፡ ልጆች ራሣቸውን ከሌሎች ጋር እንዴት ማስማማት እንደሚችሉና በጨዋታ ወቅት ሊኖራቸው ስለሚችል ኅብረት ሁሉ ይማራሉ፡፡ በቡድን በተደራጁ ልጆች ላይ የተደረጉ የክትትል

ጥናቶች እንዳመለከቱት በቀዳማይ የልጅነት ወቅት የተገነቡ ማኅበራዊ አመለካከቶችና ባህርያት ከመጠነኛ ለውጥ በስተቀር ዘላቂ ቆይታ ይኖራቸዋል፡፡ የቀዳማይ የልጅነት ዘመን የቅድመ ጓድ ምስረታ እድሜ /pre-gang age/ ነው፡፡ በዚህ ወቅት ልጆች ከሌሎች ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት የማኅበራዊ እድገታቸውን ይወስነዋል፡፡ በቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤት ውስጥ ያለፉ ልጆች በዚህ ሂደት ካላለፉት ይልቅ የተሻለ ማኅበራዊ ግንኙነት ከእድሜ አቻዎቻቸው ጋር ይኖራቸዋል፡፡ የቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤቶች ያላቸው ዋና ጠቀሜታ ልጆች በባለሙያ መምህራን እየተረዱ ማኅበራዊ ልምድ እንዲያካብቱ ማድረግ ነው፡፡ በዚህም የተነሣ በአጠቃላይ ልጆች-ለልጆች ያላቸው አፍራሽ አመለካከት ይወገዳል፡፡

### 1.18.7.1 የልጆች ከአዋቂዎች ጋር ግንኙነት

ልጆች እያደጉ ሲመጡ ከአዋቂዎች ጋር የሚያሳልፉት ጊዜ እያነሰ ይመጣል፡፡ ከአዋቂዎች ጋር በመሆናቸው የሚያገኙት ደስታም ይቀንስና ትኩረታቸው ከጓደኞቻቸው ጋር ይሆናል፡፡

- ነፃ የመሆን ፍላጎታቸው እያደገ ስለሚመጣ የአዋቂዎችን ስልጣን ይቃወማሉ፡፡
- ነፃ ከመሆን ፍላጎት የተነሳ ትኩረትና ማበረታቻ ከአዋቂዎች ለማግኘት ይሻሉ፡፡
- በህፃንነት ጊዜአቸው በነበረው ቤተሰባዊ ግንኙነታቸው የሚያገኙት እርካታ ከፍተኛ ከሆነ ከአዋቂዎች ጋር የሚኖራቸውም ግንኙነት ያማረ ይሆናል፡፡

ምንም እንኳ ከእድሜ እኩዮቻቸው ጋር ያለው ግንኙነት ጠንካራ ቢሆንም ቅሉ ወላጆችና መምህራን ለልጆች ተገቢ የሆነ ማኅበራዊ አመለካከት አርአያ/ምሣሌ የማቅረብ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

### 1.18.7.2 ልጆች ከሌሎች ልጆች ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት

ከሁለት ዓመት እድሜአቸው በፊት ህፃናት በብቻ ወይም ትይዩ ጨዋታ /solitary or parallel play/ ይሳተፋሉ፡፡ ምንም እንኳ በአንድ ክፍል ውስጥ ሁለት ወይም ሦስት ልጆች በየራሣቸው መጫዎቻዎች ቢጫወቱም ቅሉ በመካከላቸው ምንም ግንኙነት አይኖርም፡፡ የሚኖራቸው ግንኙነት ቢኖር አንዱ የሌላውን ድርጊት መቅዳት ወይም መመልከት እና አንዱ የሌላውን የመጫዎቻ እቃ ለመውሰድ መጣር ነው፡፡ በሶስት ወይም በአራት ዓመት ወቅት ልጆች በቡድን ሆነው በጋራ መጫወት ይጀምራሉ፡፡ አብረው ማውራትና ከማን ጋር እንደሚጫወቱ የመምረጥ ባህርያት ይታዩባቸዋል፡፡ ሌሎች ባህሪያት እርስ በርስ መተያየትና ምክር መለዋወጥ ናቸው፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤት ዘመን ልጆች እድሜአቸው እየጨመረ በመጣ ቁጥር የጓደኝነት ፍቅራቸው እየጨመረና በመካከላቸው ያለው ጥላቻ እየቀነሰ እንደሚመጣ ነው፡፡ በአንድ ዓይነት እድሜ ከሚገኙ ልጆች ውስጥ ወንዶች ከፍተኛ የጓደኝነት እና ከፍተኛ የመጠላላት ግንኙነት ለሌሎች ልጆች ያሳያሉ፡፡

### 1.18.7.3 የጨዋታ እድገት በቀዳማይ የልጅነት ወቅት

ጨዋታ ለልጆች የማኅበራዊ ግንኙነት መሠረት ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ልጆች ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር በጨዋታ አማካኝነት ግንኙነት የሚፈጥሩት በተለያየ መንገድ ነው፡፡ እነዚህን መንገዶች የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መልኩ ቢያስቀምጧቸውም ሞርጋን እና ኪንግ ግን በሦስት ከፍለውታል፡፡

1. **የብቻ ጨዋታ /Solitary Play/፡-** ልጆች ሌሎች ልጆች ሲጫወቱ አጠገባቸው ሆነው የሚያደርጉትን የማየት ፍላጎት ማሳደርና የራሳቸውን ጨዋታ ግን በግላቸው ማካሄድ፡፡ የብቻ ጨዋታ በሂደት ወደ ትይዩ ጨዋታ /parallel play/ ይለወጣል፡፡
2. **ትይዩ ጨዋታ /Parallel Play/፡-** ልጆች ተመሳሳይ የጨዋታ መሣሪያ በመያዝ በተመሳሳይ ጨዋታ ላይ መሳተፍ ሲሆን በዚህም ወቅት አጠገብ ለአጠገብ ሆነው የሚጫወቱ ትግን ለየብቻቸው ነው። በምንም ዓይነት የርስ በርስ መስተጋብር አያደርጉም፡፡
3. **የሕብረት ጨዋታ /Co-operative Play/፡-** ቀጥተኛ የሆነ የልጅ ለልጅ መስተጋብር የሚያካትት እና ሌሎች ተጨማሪ ሚናዎችን የሚያቅፍ የጨዋታ ዓይነት ነው፡፡ ልጆች በሶስት ዓመታቸው የሕብረት ጨዋታን ይጀምራሉ፡፡ በዚህ ጨዋታም የአዋቂዎችን ሚና አስመስለው ለመጫወት ይሞክራሉ፡፡ ለምሣሌ አባትና እናት፣ ባልና ሚስት፣ ሐኪምና ታማሚ፣ ወ.ዘ.ተ. ከላይ የተጠቀሱት የጨዋታ ዓይነቶች የልጆችን ማኅበራዊ መጎልበት ያመለክታሉ (Morgan and King, 1986)፡፡

### 1.18.7.4 የቀዳማይ የልጅነት ወቅት የጨዋታ ይዘት

በቀዳማይ የልጅነት ዘመን ጨዋታ የልጆች ዋነኛ ተግባር እንደሆነ ይታመናል፡፡ በዚህም የተነሳ በርካታ ጊዜአቸውን ከአሻንጉሊቶች ጋር በመጫወት ስለሚያሳልፉ እድሜው ራሱ የአሻንጉሊት እድሜ /Toy age/ በሚል ተሰይሟል፡፡ የጨዋታቸውን ይዘት በሦስት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

1. **የአሻንጉሊት ጨዋታ /Toy play/፡-** በመጀመሪያዎቹ ጥቂት የቀዳማይ የልጅነት ዘመን የአሻንጉሊት ጨዋታ ዋነኛው የልጆች የጨዋታ ዓይነት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን እያደጉ ሲመጡ አሻንጉሊቶች ህይወት እንደሌላቸው እየተረዱ ለእነሱም የነበራቸው ፍቅር ይቀንሳል፡፡ በተጨማሪም የኅብረት (የቡድን ጨዋታ) ፍላጎታቸው እያደገ ሲመጣ የአሻንጉሊት ጨዋታ በብቻ ጨዋታ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ እየጠሉት ይሄዳሉ፡፡
2. **ድራማ /Dramatization/፡-** ልጆች በአካባቢያቸው የሚያዩትንና የሚሰሙትን የሕይወት ልምድ በድራማ መልክ ያቀርቡታል፡፡ ከጓደኞቻቸው ጋርም ይጫወቱታል፡፡ በዚህም ደስታን ያገኛሉ፡፡ በአቅራቢያቸው ሆኖ ለሚያያቸውና ለሚሰማቸውም መንፈስን ያዝናናሉ፡፡
3. **ግንባታ /Construction/፡-** ልጆች በአካባቢያቸው የሚያገኟቸውን እንደ ጭቃ፣ አሸዋ፣ አገዳ፣ ወ.ዘ.ተ. በመጠቀም አስደናቂ ነገሮችን ይሰራሉ፡፡ ግንባታዎቻቸው የሚያተኩሩት የአሊታዊ

ኑሮን ቅጅ፣ ወይም በቴሌቪዥንና ፊልሞች ያዩአቸውን ነገሮች አስመስሎ በመስራት ላይ ነው፡፡ በቀዳማይ የልጅነት ዘመን ማብቂያ ገደማ የልጆች የፈጠራ ችሎታን የሚያሳዩ የግንባታ ጨዋታዎች ይከናወናሉ፡፡

> **ተግባር 6**
>
> 1. የቀዳማይ የልጅነት ወቅት ዋና ዋና የግንዛቤ መጎልበትንና የግንዛቤ ውስንነትን አብራሩ፡፡
> 2. የልጆች የቋንቋ ችሎታን ለማዳበር ከወላጆችና ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ምን ይጠበቃል?
> 3. ጨዋታ ለልጆች የአካል፣ የእንቅስቃሴ፣ የግንዛቤ፣ የቋንቋና የማኅበራዊ ሕይወት መጎልበት ያለውን አስተዋጽኦ አብራሩ ፡፡

### 1.18.8 የቀዳማይ የልጅነት ወቅት የስነ-ምግባር መዳበር

በቀዳማይ የልጅነት ወቅት ያሉ ልጆች የስነ-ምግባር የመዳበር ደረጃቸው ዝቅተኛ ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ የመዳበር ወቅት የሚገኙ ልጆች የአእምሮ መዳበር ደረጃ ገና ትክክለኛውን ጉዳይ ስህተት ከሆነው የሚለዩበት ረቂቅ መርህ የሚረዱበት ደረጃ ላይ ስላልደረሱ ነው፡፡ ይህንን ብቃት በሂደት ከወላጆቻቸው፣ ከመምህራኖቻቸውና ከሕብረተሰቡ ጋር በሚፈጥሩት መስተጋብር እያጎለበቱት ይሄዳሉ፡፡ የስነ-ምግባር መዳበርን በሰፊው ያጠናው የስነ-ባህሪ ምሁር ኮኸልበርግ ነው፡፡ በኮኸልበርግ ጥናት መሰረት የስነ-ምግባር መዳበር ሶስት እርከኖች ሲኖሩት እያንዳንዱ እርከን ሁለት ደረጃዎች አሉት፡፡ እንደ ኮኸልበርግ አገላለጽ የቀዳማይ የልጅነት ወቅት ልጆች በቅድመ ስምምነት የስነ-ምግባር እርከን ላይ (Preconventional level of moral development) ይገኛሉ፡፡ ይህ የስነ-ምግባር እርከን በስነ-ምግባር ምክንያታዊ መሆን አይታይበትም፡፡ በዚህ እርከን ስነ-ምግባር በውጪያዊ ሁኔታዎች ቁጥጥር ስር ያለ እንጂ ከውስጥ የመነጨ አይደለም፡፡ ይህ እርከን ሁለት ደረጃዎች አሉት፡፡ እነሱም፡-

i. ቅጣትና ታዛዥነት ማወቅ (Punishment and Obedience orientation)። ልጆች ሕግጋትን የሚያከብሩት ቅጣትን ለማስወገድ ሲሉ ነው፡፡ ምክንያቱም ሕግጋቱን አለማክበር ቅጣት እንደሚያስከትል ስለሚያውቁ ነው፡፡

ii. ግላዊ ሽልማትን ማወቅ (Personal reward orientation)፡፡ ልጆች ነገሮችን የሚያከናውኑት ከሚያገኙት ጥቅምና ሽልማት አኳያ በመሆኑ ነው፡፡

### 1.18.8.1 የልጆች ስነ-ምግባር መገንቢያ ዘዴዎች

የልጆች ስነ-ምግባር እንዴት ይገነባል?

____________________________________________________

____________________________________________________

የልጆችን ባህሪ በመልካም ስነ-ምግባር ለማነጽ፣ ደንብና ስርዓትን ለማስጠበቅ፣ ተገቢ ያልሆነ ባህሪን ለማስተካከል ወላጆችና መምህራን የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ የሚከተሉት አዎንታዊ የስነ-ምግባር መገንቢያ ስልቶችን ያመለክታሉ፡፡

**ሀ. የደንቦች ግልጽነት**

ደንቦችን፣ መከበር የሚገባቸውን መመሪያዎችን፣ መከናወን የሚገባቸው ተግባራትን ግልጽነትና አዎንታዊ ይዘት ባለው መንፈስ ተቀርፀው ልጆች በቀላሉ እንዲገነዘቡ ማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡ ሁኔታውን ለልጆቹ በምናስረዳበት ጊዜ የሚከተሉትን ነጥቦች ልብ ልንል ይገባል፡፡

- መከበር ስለሚገባቸው ስርዓቶች ለልጆቹ በምንነግርበት ጊዜ ኃይለ ቃልና ማስፈራራት ከአንደበታችን እንዳይወጣና የድምፃችንን ቃና ለማለስለስ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል፤
- ልጆች በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ፣ ጥያቄ እንዲያቀርቡና ሃሣብ እንዲሰጡበት መገፋፋት፤
- ደንቦችን በላይ በላዩ በማከታተል ከመስጠት/ከመናገር መቆጠብና አንድ ደንብ በአንድ ጊዜ ለማስተላለፍ መሞከር፤
- ልጆች አንድ ተግባር እንዲያከናውኑ ሲፈለግ ተግባሩ ሊፈጅ ወይም መውሰድ ያለበትን ጊዜ አበክሮ መንገር፡፡ **ለምሣሌ** የክፍል ስራ ተሰጥቷቸው ወድያውኑ "ሰዓቱ አልቋል አቁሙ" ወይም "በልታችሁ አልጨረሳችሁም በቃ መሄዳችን ነው" ከማለት ይልቅ ከወዲሁ የጊዜውን ገደብ ማሣወቅ ሊደርስ የሚችለውን ያለመግባባት ችግር ያስወግዳል፡፡ በእርግጥ የሚሰጠው የጊዜ ገደብና ተግባሩም የተመጣጠነ መሆኑ መጤን ይኖርበታል፡፡
- ሁኔታው እስከፈቀደ ድረስ ልጆች የተሰጣቸውን ሥራ የተለያዩ መንገዶችን ተጠቅመው እንዲሰሩ መፍቀድ ወይም መገፋፋት ጠቃሚ ይሆናል፡፡

**ለ. መልካም ስነ-ምግባርን ማበረታታት**

ብዙውን ጊዜ ስለ ዲሲፕሊን ወይም ስነ-ምግባር ሲነሳ ትዝ የሚለን ስለ አጥፊነት፣ በጥባጭነት፣ ጠበኝነት፣ ባጠቃላይ የስነ-ምግባር ብልሹነት ነው፡፡ ነገር ግን የስነ-ምግባር ዋነኛ ዓላማ በጥሩ ስነ-ምግባር የታነፁ ልጆችን ማፍራት ስለሆነ መልካም ስነ-ምግባርና ባህሪ ለተላበሱት ልጆች ተገቢ እውቅናና ማበረታቻ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ለእነዚህ ልጆች ተገቢውን ትኩረት አለመስጠትና ችላ ማለት ውጤቱ አስከፊ ሊሆን ይችላል፡፡ **ለምሣሌ** አንድ ልጅ ንጽሕናዋን በሚገባ ስትጠብቅ፣ ስራዋን በሚገባ ስታከናውን፣ ከሌሎች ጋር አብሮ የመሥራትንና የመተጋገዝን ባህሪ ስታሳይ፣ በዕቅድ

የመሥራትን ባህሪ ስታሳይ፣ በእቅድ የመሥራት ልምድ ስታዳብር ወዘተ. ተገቢውን አድናቆትና ማበረታቻ ሊሰጣት ይገባል፡፡ ይህ ዘዴ በልጆችና በአዋቂዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ከማለስለሱም በላይ መልካሙን ስነ-ምግባር ይበልጥ እንዲገፉበትና ለሌሎቹ አርአያ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ልጆች በሚያከናውኑት ተግባራት ላይ አዋቂዎች ተሣትፎና ፍላጎት ማሳየት ከአድናቆትና ከሙገሣ በላይ ጠቀሜታ እንዳለው ጥናቶች ይዘግባሉ፡፡ ቀረብ ብሎ ልጆች የሚሠሩትን ሥራ መልከት መልከት ማድረግና በተግባሩ ላይ ፍላጎት እንዳለ መግለጽ ጥሩ ማነቃቂያና ማበረታቻ ነው፡፡ ለምሣሌ "አንቺ ጎበዝ ልጅ ነሽ" ከማለት ፋንታ "ምን እየሰራሽ ነው?" "ለማየት እችላለሁ?" "ከየት ተማርሽው?" "ማን አሳዬሽ?" እና የመሳሰሉት መጠይቆችን በማቅረብ ልጅቷን ማነጋገር እጅግ በጣም ያስደስታታል፡፡ ይህን የመሰለው አቀራረብ በልጆቹ ሥራ ላይ ፍላጎትና ትኩረት እንዲሁም ክብር መስጠታችንን ያመለክታል፡፡ ስነ-ምግባር መገንባት መጥፎ ባህሪን መግራት ወይም ማስወገድ ብቻ አርጎ መውሰዱ ተገቢ አለመሆኑን በመገንዘብ መልካም ባህሪ ለሚያሳዩት ያላሰለሰ ድጋፍና ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ የልጆቹን ባህሪ ፈር ለማስያዝ ቀን ተቀን ከልጆቹ ጋር በሚኖረው መስተጋብራዊ ግንኙነት የሚከተሉትን ነጥቦች ልብ ማለት ተገቢ ነው፡፡

- ልጆቹ በሚያከናውኑት ተግባር ላይ ፍላጎት ማሳየት፡፡ (ጥያቄዎችን በመጠየቅና የሚከናወኑትን ተግባራት መልከት መልከት በማድረግ)
- በሚከናወኑት ተግባራት ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ፡፡ (ማገዝ ወይም የማሻሻያ ምክር መስጠት)
- ማመስገንና ማድነቅ፡፡ (ጠንካራ ጎኖቹን በማጉላት)
- ሞቅ ያለ የፍቅር ስሜት ማሳየት፡፡ (በሳቅ፣ በፈገግታ፣ ዳበስ ዳበስ በማድረግ ወዘተ.)

**ሐ. ምክንያቶችን በግልጽ ማስረዳት**

ለምን ደንቦች እንዳስፈለጉ፣ ደንቦች ወይም ሥርዓቶች ቢጣሱ የሚያስከትሉትን ችግር ወይም አደጋ በረጋ መንፈስ ለልጆቹ ግልጽ ማድረግ፣ ይህ በልጆቹ ዘንድ ተቀባይነት አገኘ ማለት ደግሞ ለሚፈለገው የባሕሪ ለውጥ መሠረት ተጣለ ማለት ነው፡፡ እርምጃዎቻቸውም በውሣኔ ላይ የተመሠረቱ፣ ግብታዊነትና ግንፍልተኝነት ያላጠቃቸው እንዲሆኑ ይረዳል፡፡ ብዙውን ጊዜ ለደንቦችም ሆነ ለሚከናወኑት ድርጊቶች የሚሰጡት ምክንያቶች ከሞላ ጎደል በሶስት መልክ ይጠቃለላሉ፡፡ እነሱም፡-

- ባሕሪው ወይም ድርጊቱ ልጆቹን ለአደጋ ያጋልጣል ወይም ይጥላል ተብሎ የሚገመት ከሆነ፣ ለምሣሌ መኪና የሚበዛበት አካባቢ እግር ኳስ መጫወት፣ ንጽሕናን አለመጠበቅ፣ ለትምህርት ትኩረት አለመስጠት ወዘተ… ሊሆኑ ይችላሉ።

- ባህሪው ወይም ድርጊቱ ሌሎች ሰዎችን ሊጎዳ ይችላል ተብሎ የሚገመት ከሆነ፣ ለምሳሌ የሌሎች ልጆችን መጫወቻ መንጠቅ፣ መስረቅ፣ መስበር ወይም ማበላሸት፣ ሌሎችን መደብደብ፣ መተናኮል፣ መመቅኘት፣ ለአደጋ መዳረግ ወዘተ.. ናቸው፡፡
- ባህሪው ወይም ድርጊቱ በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤትና በማኅበረሰቡ ተቀባይነት የሌለው ከሆነ፣ ለምሳሌ ታላላቆችን የማዋረድ፣ የመናቅ፣ የትዕቢተኝነትና የግድየለሽነት ስሜት መኖር ወዘተ… ናቸው፡፡

ደንቦችና ስርዓቶች በአግባቡ ተግባራዊ እንዲሆኑ ከተፈለገ ወላጆችም ሆኑ መምህራን ያላሰለሰ ጥረትና ክትትል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ጉዳዩን ያዝ ለቀቅና ችላ ማለት ወይም በየጊዜው የመለዋወጥ ሁኔታ ካለ "አድሮ ቃርያ" ወይም ከንቱ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ደንቦች አለመጣሳቸውንና ሥርዓቶች መጠበቃቸውን በየጊዜው መገምገም፣ ተግባራዊ ያደረጉትን እውቂያ መስጠት፣ ማበረታታትና የጣሱትን በጊዜ እርማት እንዲያደርጉ መምከር ተገቢ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ አዎንታዊ የሥነ-ምግባር መገንቢያ ዘዴ ቀላል አለመሆኑንና ከወላጆችም ሆነ ከመምህራን ከፍተኛ ትዕግስትን፣ መቻቻልንና ልምድን የሚጠይቅ፣ አንዳንዴም ተፈታታኝ ሊሆን እንደሚችል ከወዲሁ መገንዘቡ አስፈላጊ ነው፡፡ ተፈታታኝ ሲባል ጠንከር ያሉ ጥያቄዎችና ከረር ያሉ ክርክሮች በልጆቹ በኩል ሊነሱ እንደሚችሉና ወላጆችም ሆኑ መምህራን በቂ ስነ-ባህሪያዊና አእምሮአዊ ዝግጅት አበክረው ማድረግ እንደሚገባቸው ለማሳሰብና የነበረውን ዘይቤ ለውጦ በሌላ ለመተካት ከባድና አስቸጋሪ መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡ ሆኖም ለልጆቹ ሁለንተናዊ ጤንነትና ደህንነት እንዲሁም ለቤተሰብና ለኅበረተሰብ እድገት ሲባል ይህን በስፋት ተቀባየይት ያለውን ዘዴ ከአሁኑ መጀመር ያስፈልጋል።

**መ. የአዎንታዊ ዘዴ ውጤቶች**

ዲስፕሊን ዙሮ ዙሮ ዲስፕሊን የሚያስፈልገው የልጁን ብሎም የኅብረተሰቡን ደህንነት ለመጠበቅና ለመንከባከብ ስለሆነ ወላጆችም ሆኑ መምህራን ይህን ዓላማ ግብ ለማድረስ አዎንታዊውን የሥነ-ምግባር መገንቢያ ዘዴ መጠቀም አለባቸው፡፡ ይህ ዘዴ ሲተገበር በልጆቹ ሰብዕና ላይ የሚያስከትለውን ዋና ዋና ተፅዕኖዎች እንመልከት፡፡

- ፍራቻና ጭንቀት በልጆቹ ላይ አያሳድርም፡፡ ይህም ልጆች ሃሣባቸውን ካለምንም ስጋትና ድንጋጤ ለወላጆችም ሆነ ለመምህራን ለመሰንዘር ያስችላቸዋል፡፡ አእምሮአቸውን በሚገባ ይጠቀሙበታል፣ ቀለም የመቀበልና የግንዛቤ አድማሳቸውንም ለማስፋት ይረዳቸዋል፡፡
- በእራስ የመተማመን ስሜትን ይገነባል፡፡ ይህ ልጆች በአላቸው ክህሎት ምን ምን ሊሰሩ፣ ሊማሩ፣ ሊሞክሩና ሊንከባከቡ እንደሚችሉ ያላቸውን ግንዛቤ ያሳያል፡፡ ስለእራስ በጎ አመለካከት በልጅነት ዘመን ጀምሮ መቅረጽ ወደፊት ተደቅኖ የሚጠብቃቸውን የትምህርት ፣ የሥራና የማኅበራዊ ኑሮ ውጣ ውረድ በድል አድራጊነት እንዲወጡት ያግዛቸዋል፡፡

- → የልጆቹን የማስተዋል፣ የግንዛቤንና የአስተሳሰብን አድማስ ያሰፋል፡፡ ግልብ የሆነን ባህሪ በማስወገድ ጉዳዮችን በሚገባ ጠለቅ ብሎ በመመልከት፣ በማመሳሰል፣ ልዩነታቸውን ለቅሞ በማውጣትና ከተለያዩ ሁኔታዎች ጋር በማያያዝ፣ መንስኤዎችንና ውጤቶችን በማዛመድ ስለአካባቢያቸው ያላቸውን እውቀት እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል፡፡
- → ለሌሎች ሰዎች የመቆርቆርን ስሜትን ይቀሰቅሳል፡፡ ሌሎችን ማጥቃት፣ የሌሎችን ንብረት እቃ መዝረፍና በሌሎች ላይ ጉዳት ማድረስ ተገቢ አለመሆኑን እንዲገነዘቡ ያስችላል። በአንፃሩ አብሮ የመሥራትንና የመረዳዳትን መንፈስን ያሳድራል፡፡
- → እራስን የመቆጣጠር ባህሪ ያዳብራል፡፡ የግልፍተኝነት ባህሪ ያስወግዳል፡፡ በምትኩም የአስተዋይነትን ባህሪ ያስተምራል፡፡ ሥራን በዕቅድና በቅደም ተከተል የመሥራት ልምድን ያዳብራል፡፡
- → የኀላፊነትን ስሜት ያሳድራል፡፡በቤት ውስጥም ሆነ በትምህርት ቤት ሃሣባቸውን እንዲያካፍሉና አንዳንድ ተግባራትን ኃላፊነት ወስደው እንዲያከናውኑ ማድረግ ለራሣቸው ክብርና ተቀባይነት ስሜት ከመስጠቱም በላይ የበለጠ ኃላፊነት እንዲያድርባቸው ያደርጋቸዋል፡፡
- → የብቃት ወይም የብቁነት ፍላጎት ይቀሰቅሣል። በዚህ ዘዴ የሚያድጉ ልጆች በራሣቸው የሚተማመኑና የኃላፊነት ስሜት የተጣለባቸው ስለሚሆኑ የበለጠ አካላዊ፣ አእምሮአዊና ማኅበራዊ ብቃት ለማዳበር ሳይታክቱ ሌት ከቀን እንዲሰሩ ይገፋፋቸዋል፡፡

### 1.18.8.2 የልጆች አስተዳደግ ዘይቤዎች

የልጆች አስተዳደግ ዘይቤ ጽንሰ ሃሳብን ግለፁ?

______________________________________________

______________________________________________

ወላጆችና መምህራን ዕለት ከዕለት ከልጆች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት ምክንያት በልጅ ባህሪ ላይ በተለያዩ መንገዶች ከፍተኛ ተፅዕኖ ያደርጋሉ፡፡ ተፅዕኖዎቹም አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ወይም የሁለቱም ቅልቅል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በአለም አቀፍ ደረጃ ስለልጆች አስተዳደግ ዘይቤ ጥናቶች የሚዘግቡትን ባጭሩ ሲዳሰስ ወላጆችም ሆነ መምህራን በልጆች አስተዳደግና አያያዝ ዘዴ የልጆቹን ስነ-ባህሪ ለመገንባት ሶስት ዓይነት ስልቶችን ይጠቀማሉ(Tirusew, 1991) ። እነዚህ ስልቶች እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

### ሀ. የአምባገነናዊ አስተዳደግ ዘይቤ

ይህ አምባገነናዊ ዘይቤ የወላጅ ወይም የመምህሩ ቃል እንደ ሕግ የሚከበርበት፣ ጥያቄ የማይቀርብበት፣ ማስረጃ ወይም ማብራሪያ የማይጠየቅበትሲሆን

"ይህን ማድረግ አለብህ!" "ዝም ብለህ ተቀመጥ!"

"እኔ የምልህን ብቻ ስማ!" "አፍህን ዝጋ!" በማለት የልጆቹን ባህሪ ለመቆጣጠር፣ አቅጣጫ ለማስያዝ ብሎም ለመግራት የሚገለገሉበት ስልት ነው፡፡ ልጆቹ በፍርሃትና በጭንቀት ይዋጣሉ፡፡ ወደዱም ጠሉም የታዘዙትን ተግባራዊ ለማድረግ ይገደዳሉ፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ሀይለ ቃል፣ ስድብ፣ ቁጣና ዱላ ይከተላል፡፡ በዚህ መልክና ሁኔታ የሚከናወን የአስተዳደግ ተግባር በልጆቹ ላይ የሚጠበቀውን ዘላቂነት ያለው የባህሪ ለውጥ የማምጣት ችሎታው እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ በአንፃሩ ልጆቹን ታዛዥና የራሣቸውን ውሣኔ መስጠት የሚሳናቸው ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ ጥሩና መጥፎውን ዕርምጃ ከመውሰድ ይልቅ የአዋቂዎችን ፊትና ውሣኔ መጠበቅን ይመርጣሉ፡፡ ለእነሱም ውሣኔ ተገዥ ይሆናሉ፡፡

ይህን የመሰለው ያስተዳደግ ስልት ተፈላጊውን የባህሪ ለውጥ ማምጣት ይቅርና የልጆቹን ሁለንተናዊ ዕድገት በተለይም የአስተሳሰብንና ራስን የመቆጣጠር ችሎታን ያዳክመዋል የሚል ግምት አለ፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ያደጉ ልጆችም ለወደፊቱ በራስ የመወሰንና ራስን የመቆጣጠር ችግር የሚታይባቸው ከመሆናቸውም በላይ የጠበኝነትና የተደባዳቢነት ባህሪ ሊያዳብሩ ይችላሉ፡፡

### ለ. የግዴለሽነት አስተዳደግ ስልት

ይህ ስልት የአምባገነናዊ አስተዳደግ ስልት ተፃራሪ ሆኖ ይገኛል፡፡ የግድየለሽነት አስተዳደግ ስልትን የሚገለገሉ ወላጆችም ሆኑ መምህራን ራሳቸውን የሁሉም የበላይ አርገው ከማየት ይልቅ፣ የልጆቹን መልካም ተፈጥሮና ስሜት እንዲሁም ችሎታና ሙሉ ተሣትፎ እንደመመሪያ አድርጎ መውሰድ ዓይነተኛ መርሃቸው ነው፡፡ ልጆቹን ሃሣብ እንዲሰጡና በራሣቸው ውሣኔ ላይ እንዲደርሱ ይጋብዛሉ፡፡ ለምሣሌ ልጆች፡-

"ምን ማድረግ እንዳለባቸው!"

"ምን መሥራት እንደሚፈልጉ!"

"የራሣቸውን ውሣኔ እንዲሰጡ!" ያደርጋሉ፡፡

በዚህ መልክ በልጆቹ ላይ ሙሉ የኃላፊነት እምነት በመጣል ልጆችን ለሁሉም ነገር አድራጊ ፈጣሪ የማድረግ አዝማሚያ ይታይባቸዋል ይህ ስልት ምንም እንኳን በልጆች ጥሩ ተፈጥሮአዊ ስሜትና ችሎታ እንዲሁም ተሣትፎ ላይ እምነት መጣሉ በጎ ጎኑ ቢሆንም ብቻውን ካለአዋቂዎች ሙሉ

ተማትሮና ክትትል  የሚፈለገውን የባህሪ ለውጥ ወይም ስነ-ምግባር ለማምጣት አያስችልም፡፡ ለዚህም የሚከተሉት ምክንያቶች ዋነኞቹ ናቸው፡፡

- ልጆች ደንብና ስርዓትን ለመከተልና አካባቢያቸውን በሚገባ ለማወቅ፣ ብሎም እራሳቸውን የመቆጣጠር ልምድ ለማዳበር ከአዋቂዎች ድጋፍ ማግኘት ስለሚገባቸው፣
- ልጆች በየዕድገት ደረጃው ለማከናወን የሚሞክሩትን አካላዊ፣ አእምሮአዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ በመከታተል ተገቢውን እውቅና፣ ድጋፍና ማበረታቻ ከአዋቂዎች ማግኘት አስፈላጊ በመሆኑ፣
- ልጆች ተገቢውን የመወሰን ልምድ የመማር ዕድል ሳያገኙ ገና በለጋ ዘመናቸው ውሜኔ የመወሰን ስልጣን መስጠቱ ችግር ውስጥ ስለሚጥላቸውና ምናልባትም ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊበልጥ ይችላል የሚል ስጋት በመኖሩ ነው።

በዚህ ሁኔታ ያደጉ ልጆች አላማ የሌላቸውና ራስን የመቀስቀስ ስሜታቸው ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል፡፡ ልጆችን ልቅ የሚተው ወላጅ ወይም መምህራን በልጆች ላይ ከመጠን ያለፈ ቁጥጥር እንደሚያደርግ ወላጅ ወይም መምህር በልጆቹ ስነ-ምግባር ላይ ተመሳሳይ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚያስከትል ጥናቶች ይዘግባሉ፡፡ በአጠቃላይ ልጆች በራሣቸው ጥረት ብቻ ከአዋቂዎች እርዳታና አመራር ውጭ ስለአካባቢያቸዉ የተሟላ ግንዛቤና ተፈላጊውን ስነ-ምግባር ያዳብራሉ የሚለው አመለካከት ተቀባይነት የለውም፡፡  ልጆች የራሳቸውን እምቅ የተፈጥሮ ሃብት በሚገባ ሊጠቀሙና ሊያንቀሳቅሱ የሚችሉት ከአዋቂዎች ጋር የተቀናበረና የተደጋገፈ ግንኙነት በሚኖርበት ጊዜ ነው፡፡

### ሐ. ምክንያታዊና ግልጽነት የተሞላበት የአስተዳደግ ዘይቤ

ይህ ስልት አዋቂዎች ለልጆች ደንቦችንና መጠበቅ ያለባቸውን ስርዓቶች እስከነ ምክንያቶቻቸው ግልጽ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ያመለክታል፡፡  በዚህ ዘዴ የወላጅ ወይም የመምህራን የበላይነት ተገቢ እውቅና አለው፡፡ይህም እውቅና  በአምባገነናዊነት መልክ የሚተገበር ሳይሆን ልጆችን በመምራት፣ አቅጣጫ በማስያዝ፣ፈር በማስጨበጥና የግንዛቤ አድማሳቸውንና የማኅበራዊ ግንኙነታቸውን በማስፋትና በመከባበር ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

እንግዲህ ይህ ስልት የልጆችን ፍላጎት የሚያካትት፣ መከበር የሚገባቸውን ደንቦችንና ግዴታዎች በግልጽና በቀላል መንገድ አበክሮ የሚገልጽ፣ ከደንቦችና ከግዴታዎች በስተጀርባ ያሉትን ምክንያቶች የሚያብራራና ለውይይት ክፍት የሚያደርግ ዘዴ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በዚህ ስልት ልጆች የመጠየቅ፣ ማስረጃ የማግኘትና ገንቢ ሃሣብ የመስጠት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡  በዚህ ስልት፡

“ያን መሥራት አለብህ”

“ይህን መሥራት የለብህም”

የሚሉትና የመሣሰሉት አባባሎች በምክንያቶች ተደግፈው በጥሞና ከበቂ ማብራሪያ ጋር መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡"እኔ ስላልኩ" የሚለው አምባገነናዊ ያስተዳደግ ስልት እዚህ ተቀባይነት የለውም፡፡ ምናልባት ስምምነት ላይ ባይደረስ እንኳን ኃይለ-ቃል ወይም ዱላ አይከተልም፡፡ ሁኔታውን ለማስረዳት፣ ለማብራራትና በቂ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ካለመታከት ጥረት ይደረጋል፡፡ ይህን የመሰለ ሁኔታ በልጆችና በወላጆች እንዲሁም በተማሪዎችና በመምህራን መካከል ያለውን ግንኙነት ከማቀራረቡም በላይ በመካከላቸው የመከባበርና የመተማመን መንፈስን ያሳድራል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ወላጆችም ሆኑ መምህራን በግብታዊነት ከሚሰጧቸው ትእዛዞችና እርምጃዎች ለምሣሌ አላግባብ ከሚሰነዘሩ ትዕዛዞች፣ ትችቶች፣ ኃይለ-ቃሎች እንዲሁም አካላዊ ቅጣቶች እንዲቆጠቡ ያደርጋል፡፡

በአገራችን በቤትም ሆነ በትምህርት ቤት አካባቢ ገኖ የሚታየው የልጆች አስተዳደግና አያያዝ ስልት ከሞላ ጎደል አምባገነናዊነት ገጽታ ይታይበታል፡፡ ቀደም ሲል በዝርዝር ለማየት እንደተሞከረው ይህ ሁኔታ ለልጆቹም ሁለንተናዊ እድገት ሆነ ለትምህርት ስኬታማነት ከጠቀሜታው ይልቅ ጉዳቱ ስለሚበልጥ ከወዲሁ ወላጆችም ሆኑ መምህራን ተገቢውን ግንዛቤ በመውሰድ ይህን ዘዴ በተቻለ መጠን ለማስወገድ ሙከራ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

### 1.18.9 በልጅነት ዘመን የሚከሰቱ የባህሪ ችግሮች ገፅታና የማሻሻያ ዘዴዎች

በልጅነት ዘመን የሚከሰቱ ዋና ዋና የባህሪ ችግሮችን ግለፁ?

________________________________________

________________________________________

የልጆች ሁለንተናዊ ዕድገት የሚወሰነው ውስጣዊ የሆኑ ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች ከአካባቢው ጋር በሚያደርጉት የተወሳሰበ ግንኙነትና ቅንጅት ነው፡፡ የግንኙነቱና የቅንብሩ ዓይነትና መጠን ከሞላ ጎደል በመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ እንደተገለፀው፡- የልጆቹን የቋንቋ፣ የማኀበራዊ፣ የስሜትና የአእምሮ እድገት ሂደቶችን ይወስናል፡፡ የባህሪ ችግሮችም የሚመነጩት በአብዛኛው ከማኀበራዊ ግንኙነት መዛባት ነው፡፡ ለዚህም ቤተሰብ፣ ትምህርት ቤት፣ ጓደኛና በአጠቃላይ አካባቢ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያደርጋሉ፡፡ የልጆቹ አካባቢ ማለትም ከወላጆቻቸው፣ ከመምህራኖቻቸውና ከጓደኞቻቸው ጋር ያለው ግንኙነት በበጎ አመለካከት፣ በመተማመን፣ በመከባበርና በመግባባት ላይ ከተመሰረተ የተለያዩ የባህሪ ችግሮችን ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ የማይቻልበት ምክንያት የለም፡፡ በአንፃሩ ልጆች ከወላጆቻቸው፣ ከመምህራን፣ ከጓደኞቻቸውና ከአካባቢያቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት የተበላሸ ከሆነ ማለትም መግባባትና መተሳሰብ የሌለበት፣ በመናናቅና በጥላቻ ከተሞላ፣ ቤትም ሆነ ትምህርት ቤት

የተለያዩ የባህሪ ችግሮች መፈልፈያ ቦታ ይሆናሉ፡፡ ችግሩም ከልጁ፣ ከቤትና ከትምህርት ቤት አልፎ የማኅበራዊ ግንኙነት ጠንቅና የእድገት ደንቃራ ሊሆን ይችላል፡፡

የልጆችን የባህሪ ችግር በምንመረምርበት ጊዜ ምርመራችን ልጁ ላይ ብቻ ማተኮር የለበትም፡፡ ችግሩ ልጁ ከአካባቢው ጋር በሚያደርገው ግንኙነት የሚመነጭ ነው የሚል ግንዛቤ ስላለ፣ የልጁ አካባቢም አብሮ መመርመር ይኖርበታል፡፡ መፍትሄውም በተመሳሳይ ሁኔታ መፈለግ አለበት፡፡ በተጨማሪም የልጆችና የወላጆች ግንኙነት በልጆችና በወላጆች የስነ-ባህሪ ዝንባሌ መጣጣምና አለመጣጣም ላይ ሊመሰረት ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ የዳተኝነት ባህሪ የሚያሳዩ እናቶች ወይም አሳዳጊዎች ልጆቹ እንደነሱ የዳተኝነት ባህሪ እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ፡፡ ነገር ግን እንዳጋጣሚ ልጆቻቸው ችኩሎችና ፈጣኖች ከሆኑ በመካከላቸው የሚኖረው ግንኙነትና መግባባት ጥሩ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለዚህ በአሳዳጊዎችና በልጆች መካከል ያለውን የግንኙነት ይዘት ከሁለቱም አቅጣጫ ማጤንና መመርመር የችግሩን መንስኤ ለመረዳትና መፍትሄ ለመፈለግ አመች ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

**በልጅነት ዘመን የሚከሰቱ የባህሪ ችግሮችን በሁለት ከፍሎ ጠቅለል ባለ መልኩ እንደሚከተለው ማየት ይቻላል፡፡**

ሀ. ልጁ ከሚጠበቅበት የባህሪ ደረጃ በታች ሆኖ ሲገኝ፡-**ለምሣሌ** የጥገኝነት፣ የዓይነአፋርነት የዳተኝነት ባህሪ ማሳየት፣

ለ. ልጁ ከሚጠበቅበት የባህሪ ደረጃ በላይ ሆኖ ሲገኝ፡- **ለምሣሌ** የጠበኝነት፣ የእምቢተኝነት፣ የዕረፍተ ቢስነት ባህሪ ማሳየት ናቸው።

እነዚህ ባህሪያት በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤት፣ ከጓደኛ ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ወቅትና በሌሎች ሁኔታዎች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ **ለምሣሌ** በጨዋታ ጊዜ፣ ዘመድ ጥየቃ በተሄደበት ወይም ጎረቤት ሲላኩ ሊታዩ ይችላሉ፡፡ ይህ ጽሁፍ የሚያተኩረው **በቅድመ-መደበኛ ትምህርት** ቤትና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አካባቢ በተደጋጋሚ የሚከሰቱትንና ልዩ ክትትል ያስፈልጋቸዋል ተብለው በሚገመቱ የባህሪ ችግሮች ላይ ነው፡፡ አንዳንዶቹ የባህሪ ችግሮች እርስ በርሳቸው የተያያዙና የተቆላለፉ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ **ለምሣሌ** የእረፍተቢስነት ባህሪ ወደ ጠበኝነትና አጥፊነት ሊያመራ ይችላል፡፡

እነዚህም የባህሪ ችግሮች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡፡ **ዓይነአፋርነት/ገለልተኝነት፣ ጥገኝነት፣ ዕረፍተቢስነት/ቅብጥብጥነት እና ጠበኝነት/አዋኪነት** ናቸው፡፡

እነዚህ ባህሪያት በተወሰነ ደረጃ በማንኛውም ልጅ የእድገት ሂደት ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ ሆኖም እንደ ችግር የሚወሰዱት ረዘም ላለ ጊዜ በተለያዩ ቦታዎች ሲከሰቱ ብቻ ነው፡፡

በሚከተሉት ንዑስ ክፍሎች የእነዚህን የባህሪ ችግሮች፣ ገጽታዎች፣ መንስኤዎችና የማስወገጃ ዘዴዎች ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡ ችግሮችን ለመቅረፍ ይረዳሉ ተብለው የተጠቀሱት ሃሳቦች በቤትም ሆነ

**በትምህርት ቤት ውስጥ ምን ማድረግ እንደሚቻል ያመለክታሉ፡፡** ችግሩም ዕውቅና እያገኘ ጎልቶ መታየት የሚጀምረው ከሌሎች ልጆች ጋር በሚደረገው ግንኙነትና በትምህርት ወቅት በሚታየው ተሣትፎ ነው፡፡ ሆኖም ወላጆች ከራሣቸው ልጆችና ከጎረቤት ልጆች ዕድገትና ባህሪ ጋር በማወዳደር ልዩነቶችን ለመገንዘብ ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡ እነሱም በበኩላቸው ሁኔታዎችን በመከታተልና በማመቻቸት የራሣቸውን ድጋፍ ሊያበረክቱ ይችላሉ፡፡ ከመምህራን ጋርም በየጊዜው በመገናኘትና በመመካከር ችግሩን በኀብረት ለማስወገድ መጣር አለባቸው፡፡ ትምህርት ቤት ያለውን የልጆች አያያዝና ቤት ወስጥ የሚካሄደውን የአስተዳደግ ዘዴ በማቀናጀትና በማመሳሰል ለልጆቹ አመቺ ሁኔታ መፍጠርና ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ ጥረቱን ውጤታማ ያደርገዋል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ውጤቱ “በአንድ እጅ ማጨብጨብ ይሆናል”፡፡

ስለእያንዳንዱ የባህሪ ችግር በዝርዝር ከማየታችን በፊት መምህራን በአጠቃላይ መከተል ያለባቸውን አንዳንድ መሠረታዊ ስልቶች በአጭሩ እንመልከት፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ መምህራን የሚያስተምሯቸውን ልጆች ባህሪ ለማወቅ ሙከራ ማድረግ አለባቸው፡፡ በእርግጥ የተማሪው ቁጥር በበዛበት አካባቢ ይህ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም ትምህርቱ ተማሪን የአማከለና የተማሪዎችን የቀለም መከታተል ሁኔታ ያገናዘበ መሆን ስለአለበት ከፍተኛ መስዋዕትነት መክፈል ከመምህራን ይጠበቃል፡፡ በተለይም የስነ-ባህሪ ችግር ያለባቸውን ወይም ለየት ያለ ፍላጎትና ባህሪ የሚያሳዩ ልጆችን ለይቶ ለማወቅ የመምህራንን በጎ ፈቃደኝነትና ክትትልን ይጠይቃል፡፡ ከዚህ በመነሣት ከሚመለከታቸው ልጆችና ከወላጆቻቸው እንዲሁም አብረዋቸው ከሚማሩ አርአያነት ካላቸው እኩዮቻቸው ጋር የችግሩን መንስኤ ለመገንዘብና መፍትሂዎችን ለመሻት ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ምናልባት በትምህርት ቤት ውስጥ የምክር አገልግሎት የሚሰጥ የሥነ-ባህሪ ባለሙያ ካለ ሁኔታውን አስረድቶ ሙያዊ ድጋፍ ማግኘት ተገቢ ይሆናል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ይህን የመሰለ የሙያ አገልግሎት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አካባቢ ብቻ የተወሰነ ስለሆነ በቅድመ-መደበኛና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሙያዊ ድጋፍ ማግኘቱ አስቸጋሪ ስለሚሆን ኃላፊነቱ የመምህራንና የወላጆች ከመሆን አያልፍም፡፡ ስለዚህ፡

- የመማር ማስተማሩን ሂደት በፍቅር ላይ የተመሠረተና ከፍርሃት ነፃ ማድረግ፣
- የተለያየ ባህሪ የሚያሳዩ ልጆችን ለይቶ ማወቅ፣
- የችግር መንስኤዎችን መርምሮ ለማወቅ መሞከርና፣
- መፍትሂዎችን ከሌሎች ጋር በመተባበር መሻት ከመምህራን ይጠበቃል፡፡

እነዚህ ተግባራት ከማስተማሩ ጎን ለጎን የሚሄዱ ድርጊቶች መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ልጆች ትምህርት ሊቀስሙ የሚችሉት ችግሮቻቸው ከተወገዱ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ የሆነ ተግባር ግን ትርፉ ድካም ከመሆኑም በላይ በልጆቹ ላይ ከፍተኛ የባህሪ ተፅዕኖ በማስከተል፣ ትምህርት እንዲጠሉ፣ ውጤታቸውም ዝቅተኛ እንዲሆን ብሎም ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡና የመሳሰሉትን መዘዞች

ያስከትላል፡፡ ስለሆነም የቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

#### 1.18.9.1 የዓይነአፋርነት (የገለልተኝነት) ባህሪ

**የችግር ገጽታዎች**

አንዳንድ ልጆች ከእኩዮቻቸው ጋር ተቀላቅለው ከመጫወት ይልቅ ከዳር ቁመው መመልከትን፣ ሰው ከመቅረብ ይልቅ መራቅን፣ ሃሣብን ከማካፈል ይልቅ መቆጠብንና አድማጭነትን ይመርጣሉ፡፡ አዳዲስ አካባቢ ሲሄዱ እራሣቸውን ከአዲሱ አካባቢ ጋር ለማለማመድ ይቸገራሉ፡፡ በክፍል ውስጥ ሃሣባቸውን ለመሰንዘር ከመፍራታቸውም በላይ ያደግታቸዋል፤ ለቡድን ሥራዎች ፈቃደኝነታቸውን አያሳዩም፣ ለሚቀርብላቸው ጥያቄዎች መልስ አይሰጡም፡፡ መልስ ከሰጡ ደግሞ አንገታቸውን አቀርቅረው ነው፡፡ አንገታቸውን ቀና አድርገው የጠያቂውን ዓይን ፊት ለፊት ማየት ይቸገራሉ፡፡ ቀና ካሉም ጣራና ግድግዳውን የማየት ዝንባሌ ያሳያሉ፡፡ የሚያውቁትም ይጠፋባቸዋል፤ ይደናገራሉ፡፡

እነዚህንና ሌሎች እነዚህን የመሳሰሉ ባህሪያት የሚያሳዩ ልጆች ቁጥብ ከመሆናቸው የተነሣ በሌሎች ልጆች ላይ በትምህርት ቤትም ሆነ በቤት ችግር የመፍጠራቸው ሁኔታ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ እነሱም ሰው ጋ አይደርሱም፣ ሰውም እንዲደርስባቸው አይፈልጉም፡፡ በክፍልም ውስጥ መኖር አለመኖራቸው ስለማይታወቅ ከመምህራን ትኩረት የማግኘት ዕድላቸው እጅግ በጣም የመነመነ ነው፡፡ አውቀውም ይሁን ሳያውቁ አዋቂዎችም ሆኑ እኩዮቻቸው እነዚህን ከመሳሰሉ ልጆች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ወይም አብሮ ለመጫወት ፈቃደኛ አይሆኑም፡፡ ይህም ሁኔታ ከቀጠለ በራሣቸውም ሆነ በአካባቢው ላይ እምነት እንዲያጡ፣ ከአካባቢውም እንዲሸሹ በማድረግ ቀስ በቀስ የስነ-ባህሪ ቀውስ ሊያስከትልባቸው ይችላል፡፡

**የችግሩ መንስኤዎች**

ምንም እንኳን ተፈጥሯዊ አዝማሚያዎች ይኖራሉ የሚል አመለካከት ቢኖርም የወላጆች ወይም የአሳዳጊዎች የልጆች አስተዳደግ ዘይቤና ስልት ለዚህ ዓይነት ባህሪ መፈጠርና መዳበር ዋነኛ ምክንያቶች እንደሆኑ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ የትምህርት ቤትም ሚና በቀላሉ የሚገመት አለመሆኑ በተደጋጋሚ ይጠቀሳል፡፡ የችሎታ ማነስም እንደምክንያት መቆጠሩ አልቀረም፡፡ ለመሆኑ እነዚህ የተዛቡ የልጆች አስተዳደግ ዘይቤና ስልቶች ምንድን ናቸው? በምን አይነት መልክስ ይከሰታሉ? የሚከተሉት ነጥቦች መሠረታዊ መንስኤዎችን ይጠቁማሉ፡፡

ሀ. ልጆች ሃሣባቸውን ለመግለጽና ጥያቄያቸውን ለማስረዳት መብት ከተነፈጋቸው፣ እንዳይናገሩ ተፅዕኖ ከተደረገባቸውና የአስተዳደግ ዘይቤው "ዝም አይነቅዝም"፣ "ዝምታ ወርቅ ነው"፣

"ያላረፈ አፍ ዝምብ ይገባበታል" የሚል ከሆነና በዚህ የአስተሳሰብ ፈሊጥ ከአደጉ ዝምታን እንደ ጥሩ ባህል አድርገው በመውሰድ ያዳብሩታል፡፡

ለ. ልጆች ተገልለው ከሌሎች ልጆች ጋር እንዳይገናኙ፣ እንዳይጫወቱና እንዳይቀላቀሉ በማለት በር ተዘግቶባቸው ከአደጉ በማኅበራዊ ግንኙነታቸው ከእኩዮቻቸው ደካማ ሆነው ከመታየታቸውም በላይ ቁጥብነትን ያሳያሉ፡፡ ችሎታቸውን ከሌሎች ጋር የማነፃፀር ዕድል የላቸውም። በዚህም የተነሣ ፍርሃትና ሥጋት ያድርባቸዋል፡፡

ሐ. ከሁሉም በላይ ወላጆች ወይም መምህራን ከልጆቹ ጋር የሚያደርጉት ማንኛውም ግንኙነት ኃይልና ጉልበት፣ ተግሣጽ፣ ትችትና ማንቋሸሽ እንዲሁም አካላዊ ቅጣቶችን የሚጠቀሙ ከሆነ ግንኙነታቸው ከመሻከሩም በላይ ግንኙነቱ በፍርሃትና በጭንቀት ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡ ስሜታቸውም ይነካል፡፡ ከትችቱም ከዱላውም ለመዳን ሲሉ ግንኙነታቸውን ይቀንሣሉ፡፡ መቆጠብን ይመርጣሉ፡፡ እራሣቸውን ማራቅ ወይም ማግለል የችግሩ መፍቻ ዘዴ አድርገው ይወስዳሉ፡፡

መ. በሌላ በኩል ደግሞ በራስ ችሎታና ክህሎት መተማመን አለመቻል ከሌሎቹ ጋር ከመቀላቀል፣ ጥያቄ ከመጠየቅ፣ መልስ ከመመለስ፣ በውይይት ከመሳተፍና ከመሳሰሉት ማኅበራዊ ግንኙነቶች እንዲርቁ ያደርጋቸዋል የሚል ግምት አለ፡፡

**ችግሩን ለማስወገድ የሚረዱ ዘዴዎች**

የችግሩን መንስኤዎች ከተገነዘብን ከሞላ ጎደል መፍትሄውንም አውቀነዋል ማለት ይቻላል፡፡ሆኖም ከዚህ ቀጥለው የተጠቀሱትን ነጥቦች መገንዘቡ ችግሩን ለማስወገድ ይረዳሉ የሚል ግምት አለ፡፡

ሀ. **ችግሩ በምን አይነት ሁኔታ እንደሚከሰትና በምን ጊዜ እንደሚከሰት ለይቶ ማወቅ፤ ለምሣሌ፡-** ክፍል ውስጥ ከሆነ፣ ሁልጊዜ ነው? ወይስ አንዳንድ ጊዜ? በየትኛው ክፍለ ጊዜ ነው? በጨዋታ ጊዜ ከሆነ ከአዋቂዎች ጋር ሲሆን ነው? ወይስ ከእኩዮቹ ጋር? በየትኛው ጨዋታ ዓይነት? ወዘተ…በመለየት የችግሩን መንስኤ በተጨባጭ ለመረዳት ያስችላል፡፡

ለ. **በቤትና በትምህርት ቤት ውስጥ ለልጆቹ ምቹና የሚያደፋፍሩ ሁኔታዎችን መፍጠር ያስፈልጋል፡፡**

ሐ. **አስፈላጊ ያልሆነውን ባህሪ አስወግዶ በምትኩ ተፈላጊ ባህሪ ለማዳበር ደረጃ በደረጃ ከቀላል መስተጋብራዊ ግንኙነት ወደ ውስብስብ መስተጋብራዊ ግንኙነት ልጁን መምራት አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሣሌ፡-** ቤት ውስጥ የአለምንም ተጽእኖ በመጀመሪያ ከወላጆቹ፣ ቀጥሎ ከወንድሞቹና ከህቶቹ፣ ከቤተዘመድ ጋር ተቀምጦ የሚጫወትበት የውይይት መድረክ መክፈት፡፡ በዚህም ጊዜ ሃሣቡንና ጥያቄውን ሲሰነዝር ማበረታት ማሞገስ፡፣ ቀስ በቀስም እንግዳ በሚመጣበት ጊዜ ማስተዋወቅና አብሮ እንዲጫወት መጋበዝ፣ በግንኙነቶች ወቅት

የልጁን ሙሉ ፈቃደኝነት መጠበቅ፣ ከፍላጎቱ ውጭ አስገድዶ ዕቅዱን በተግባር ላይ ለማዋል መሞከር ግንኙነቱን ሊያበላሸውና ሁኔታውን ሊያባብሰው ይችላል፡፡ ስለዚህ በትዕግስትና ተስፋ ባለመቁረጥ የልጁን ስሜት በመጠበቅ ቀስ በቀስ እንዲለማመድና ተፈላጊውን ባህሪ እንዲማር ማድረግ ብልህነት ነው፡፡

መ. **የመደማመጥና ተራ ጠብቆ የመናገር ልምድ ማዳበር፡፡** ልጆች በሚያወሩበት ጊዜ ጆሮን ጣል አድርጎ በጥንቃቄ ማዳመጥ ሃሣባቸውን ለመረዳት ከማስቻሉም በላይ ተፈላጊነታቸውን ያረጋግጥላቸዋል። ይህም የበለጠ የግንኙነት ልውውጥ የማድረግ ፍላጎት ያሳድርባቸዋል፡፡ በራሣቸው አነሳሽነትም ለመቀጠል ይፈልጋሉ፡፡ መደማመጥ ከሌለ ትርፉ ድካም ነው፡፡ የዚህ ጥቅም ደግሞ ለልጆቹ ብቻ ሣይሆን ለቤተሰቡ እንዲሁም ለማንኛውም ማኅበራዊ ግንኙነት መሠረትእንዲሆን ያደርጋል፡፡

ሠ. **የልጁን ፍላጎትና ዝንባሌ ከተለያዩ አቅጣጫዎች መገንዘብና ጨዋታውም ሆነ ውይይቱ በዚሁ አካባቢ እንዲንሸራሸር ማድረግና እንዳይሰለች መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው፡፡** በልጁ አነሳሽነት ለሚጀመሩ ተግባራት እውቅና በመስጠት ዳር እንዲያደርሰው መገፋፋት፡፡

ረ. **ልጁ የሚያሳየውን በጎ የማኅበራዊ ግንኙነት ባህሪ በየትኛውም ቦታና ጊዜ ከማድነቅና ከማበረታታት ችላ አለማለት፡፡**

- የክፍልም ሆነ የቤት ሥራ በቡድን የሚሠራበትን ሁኔታ በመፍጠር፣ የቡድን ተሣትፎን ከፍ ማድረግ፣
- የልጆቹን ጥረትና ሙከራ ዕውቅና መስጠትና ማድነቅ፣
- ልጆች ከትምህርት ውጭ እርስ በርስ የሚወያዩበት፣ በቡድን የሚያጠኑበት ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- የኅብረት ጨዋታዎች እንዲስፋፉ ማበረታታት፣
- ዓይነአፋር ልጆች አንዳንድ ታዋቂነትን የሚያስገኙ ሥራዎችን በክፍል ውስጥ እንዲሠሩ ማድረግ፣ **ለምሣሌ** የፈተና ወረቀትና የቤት ሥራ ደብተር እንዲሰበስቡ ወይም እንዲሰጡ ማድረግ ወዘተ…፡፡
- ቀለል ቀለል ያሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ለአይነአፋር ልጆች ዕድል በመስጠት ተሳትፏቸውን ከፍ ማድረግ፣
- አካላዊ ቅጣትንና አላስፈላጊ ትችትን ከመማር ማስተማሩ ሂደት ማስወገድ፡ በምትኩ ከበሬታና መግባባትን ማስፈን፡፡
- ልጆቹ ከሚያሳዩት የባህሪ ለውጦች ውስጥ በምሳሌነት በመውሰድና በመጥቀስ በክፍል ጓደኞቻቸው እንዲደነቁ ማድረግ፡፡

### 1.18.9.2 የጥገኝነት ባህሪ

**የችግሩ ገጽታዎች**

የጥገኝነት ባህሪ የሚያሳዩ ልጆች ብዙውን ጊዜ ከወላጆች ወይም ከሞግዚቶች አጠገብ መራቅ አይፈልጉም፡፡ አዋቂዎች ከአጠገባቸው ሲለዩ የመጨነቅና የፍርሃት መንፈስ ያድርባቸዋል፤ በዝምታ ይዋጣሉ፡፡ ከአዋቂዎች ትኩረት ለማግኘት ይጥራሉ፡፡ የሙጥኝ በማለት ያስቸግራሉ፡፡ እራሣቸው መሥራት የሚገባቸውን ተግባር ያለአዋቂዎች እርዳታና ድጋፍ ማከናወን ይሳናቸዋል፡፡ **ለምሣሌ** እራሣቸው መመገብ፣ መልበስ፣ መፀዳዳት በሚገባቸው የእድገት ዘመን ወይም እድሜ እነዚህን ተግባራት ለማከናወን የሌላ ሰው እርዳታ ይጠብቃሉ፡፡ በትምህርት ቤት በተለይም በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ወስጥ ከመጫወት ይልቅ ከመምህራንና ሞግዚቶች ሥር ሥር ማለትን ያዘወትራሉ፡፡

በክፍልም ውስጥ ሆነ በጨዋታ ጊዜ ከእድሜያቸው በታች የሆኑ ባህሪያትን ያሳያሉ፡፡ አዳዲስ ነገሮች ሲያጋጥሟቸው በእራሳቸው መፍትሄ ከመፈለግ ይልቅ የሌሎችን ድጋፍ ይፈልጋሉ፡፡ ኃላፊነት የመውሰድና ውሣኔ የመስጠት ችሎታቸውም ዝቅተኛ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በግል መስራት ያለባቸውን የትምህርት ቤት ተግባራት **ለምሣሌ** የክፍል ስራ፣ የቤት ስራ ለመስራት ያዳግታቸዋል፡፡ ሆኖም ይህ ዓይነቱ ባህሪ ችግር ነው ተብሎ የሚወሰደው በተደጋጋሚና ረዘም ላለ ጊዜ ሲከሰትና ሲቆይ ነው፡፡

የጥገኝት ባህሪ ዋና ምክንያት የተዛባ የልጅ አስተዳደግ ዘይቤ ነው፡፡ አንዳንድ ወላጆችና ሞግዚቶች ከመጠን ወይም ከልክ ያለፈ እንክብካቤ ለልጆች ይሰጣሉ፡፡ በዚህም ዘዴ ከልጆች ተወዳጅነትንና ፍቅርን እናተርፋለን የሚል ግምት አላቸው፡፡ ሆኖም ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ አመዝኖ ስለሚገኝ መወገድ ይገባዋል፡፡ በአገራችን በዚህ መልክ ያደጉ ልጆችን ባህሪ የሚያንፀባርቅ አባባሎች አሉ፡፡ **ለምሣሌ** "የቅምጥል ልጅ መች በእጅ ይላል" ይህም የሚያመለክተው በዚህ መልክ የሚያድግ ልጅ ከቤቱ ወጣ በሚልበት ጊዜ የሚያጋጥመውን ችግር ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ ከልክ ያለፈ እንክብካቤ ልጆቹ በወቅቱ ማወቅና መተግበር የሚገባቸውን ችሎታና ክህሎት እንዳያዳብሩ እንቅፋት በመሆን በሰብዕናቸው ላይ ተፅዕኖ ያደርጋል፡፡ በዕድገት ሂደት የሚከሰቱ አዳዲስ አካላዊና አእምሯዊ ለውጦች ተገቢው ፍተሻና ልምምድ እንዳይደረግባቸው ይከላከላል፡፡ **ለምሣሌ** አንድ ሕፃን ድሆ ወይም በእግሩ ተንከላውሶ አካባቢዎን መፈተሽ እና ማወቅ በሚገባው ጊዜ በጀርባ ታዝሎ ከእቅፍ ወይም ከአልጋ ሳይወርድ እንዲውል ከተደረገ በእንቅስቃሴውም ሆነ በማኀበራዊ ግንኙነቱ ላይ ተፅዕኖ ያስከትላል፡፡ ልጆች በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ማከናወን የሚገባቸው ተግባራትን በወላጆች ወይም በአዋቂዎች ዕርዳታ መጠየቅን ባህል ያደርጉታል፡፡ ከእነሱም ትክሻ አይወርዱም፡፡ በዚህም የተነሳ ልጆቹ በራስ የመተማመንና የብቁነት ስሜት ለማዳበር ይቸገራሉ፡፡ ይህም ባህሪ በጊዜ ካልተቀረፈ ስር እየሰደደ በልጆቹ ተከታታይ የዕድገት ዘመኖች ላይ ተፅዕኖ ማድረጉ አይቀሬ ነው፡፡

**ለችግሩ ማስወገጃ የሚረዱ ዘዴዎች**

ሀ. ልጆች የሚያሳዩአቸውን ባህሪያት በዝርዝር ጠንቅቆ መገንዘብ፡ በተለያዩ ሁኔታዎች ምን እንደሚያደርጉ፣ ምን ማድረግ ይገባቸው እንደነበርና በግላቸው ምን ማድረግ እንደሚችሉ ወይም እንደማይችሉ መረዳት ይገባል፡፡

ለ. የልጆቹን አካባቢ በጥንቃቄ መከታተል፣ ቤትም ሆነ ትምህርት ቤት ያሉ ሰዎች የልጆቹን ፍላጎት ለማሟላት ምን ዓይነት እርምጃዎች ይወስዳሉ? **ለምሣሌ** ልጆቹ እርዳታ በሚጠይቁበት ጊዜ፣ የጫማዬን ክር እሰሩልኝ፣ የቤት ሥራዬን ሥሩልኝ፣ የደብተር መያዣዬን ተሸከሙልኝ በሚሉበት ጊዜ የሚያገኙት ምላሽ ምን ይመስላል? አንዳንድ አካባቢዎች ለጥገኝነት ባህሪ መዳበር አመች ሁኔታዎች ስለሚፈጥሩ ዝርዝር ሁኔታዎችን አጥንቶ አካባቢውን ለመለወጥ ጥረት ማድረግ ያሰፈልጋል፡፡

ሐ. ወላጆችም ሆነ መምህራን ልጆች እራሣቸውን ችለው የሚሠሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም ለመጀመሪያ ጊዜ አንዳንድ ነገሮችን በግል ለማከናወን ሊሳናቸው ይችላል፡፡ ስለዚህ ተግባሮችን ከቀላል ወደ ከባድ በቅደም ተከተል በማቀድና በማቀናበር በትዕግስት ቀስ በቀስ እንዲለማመዱ ማበረታታት ተገቢ ይሆናል፡፡ አንዳንድ ተግባራትን በግላቸው ማገባደድ ሲጀምሩ ታላቅ ደስታና የመንፈስ እርካታ ይሰጣቸዋል፡፡ ከዚህም በላይ እኔ እሰራዋለሁ የሚል በራስ የመተማመን ስሜት ማሳደር ይጀምራሉ፡፡ ስለዚህ ልጆች በግል ለሚያከናውኗቸው ተግባራት ወላጆችና መምህራን ልዩ ትኩረትና ክትትል በማድረግ ዕውቅና መስጠትና ማድነቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ **ለምሣሌ** በልጁ አነሳሽነትና ፍላጎት የሚጀመሩ ሥራዎችን በቅርብ በመከታተል፤ ልጆቹ "የጀመርኩትን ሥራ እጨርሳለሁ"፤ "ብቻዬን መሥራት እችላለሁ" የሚለውን አስተሳሰብ እንዲያንፀባርቁ ጥረት ማድረግና በአጸፋው "አንተ ጎበዝ ልጅ ነህ"፤ "የጀመርከውን ሥራ ዳር ታደርሳለህ"፤ "በጥሩ ሁኔታ ጨረስከው"፤ "በርታ በዚህ ቀጥልበት" በማለት አስፈላጊውን ማነቃቂያ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡

መ. የልጆቹን የአካልና የአእምሮ ዕቅም በመገምገምና በመገንዘብ ሊሠሩ የሚችሉትን የጉልበትም ሆነ የአእምሮ ሥራዎች ማመዛዘን ይገባል። ይህም ለልጆቹ የሚሰጠው ተግባር ከአቅማቸው በላይ ወይም በታች እንዳይሆን ለመመጠን ይረዳል፡፡ ተግባሩ ከልጆቹ የእድገት ደረጃ ጋር የማይጣጣም ከሆነ የመሥራት ፍላጎታቸውን ከመቀነሱም በላይ ፍርሃት፣ ጭንቀትና በተግባሩ ላይ ጥላቻ ሊያስከትል ይችላል፡፡

ሠ. ልጆች በግላቸው የመወሰን ልምድ እንዲያዳብሩ ድጋፍ ማድረግና ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡ **ለምሣሌ** ከተለያዩ የቤት ሥራዎች፤ ከሚለበሱ ልብሶች፣ ከጨዋታዎች ውስጥ እንዲመርጡ ወይም ከሱቅ ልብስ ወይም መጫወቻ በሚገዛላቸው ጊዜ አቅም እንደሚፈቅደው ምርጫውን ለእነሱ በመተው ከተፅዕኖ ነፃ እንዲሆኑ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

ረ. ልጆቹ ባህሪያቸውን እያሻሻሉ ሲሄዱ በተደጋጋሚ ሲያገኟቸው የቆዩትን እርዳታና ማበረታታት ወድያውኑ ከማቋረጥ መቆጠብ ተገቢ ነው። ይህን የመሰለው እርምጃ ዱብ እዳ ስለሚሆንባቸው ሊያስደንግጣቸው፤ ሊያበሳጫቸውና ተስፋ ሊያስቆርጣቸው ይችላል፡፡ ወደ ወትሮው ባህሪያቸው የመመለስንም አደጋ ያስከትላል፡፡ ስለዚህ የሚወሰደው እርምጃ ቀስ በቀስ የእነሱን ስሜት በመጠበቅና በማዳመጥ ደረጃ በደረጃና በእርጋታ መሆን አለበት፡፡

### 1.18.9.3 የጠበኝነት (የቁጡነት) ባህሪ

**የችግሩ ገጽታዎች**

የጠበኝነት ወይም የአዋኪነት ባህሪ በተለያዩ መልኮች ይከሰታል፡፡ እነዚህንም በሦስት ዓይነት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

* **የቃል** - መሳደብ፣ ማዋረድ፣ ማንጓጠጥ፣ በሰው ላይ መጮህ፣ ኃይለቃል መጠቀምና የመሳሰሉትን ይይዛል፡፡
* **የጉልበት** - መደባደብን (በዱላ፣ በእጅ፣ በድንጋይ፣ ወዘተ) ንብረት ማውደምና ኃይል መጠቀምን ያመለክታል፡፡
* **የጥቅም** - የራስን ጥቅም በመፈለግ የሌሎችን ንብረት ወይም እቃ ወይም መጫወቻ አስገድዶ መንጠቅ፣ ገፍቶ ቦታ መያዝ ወዘተ ያጠቃልላል።

ልጆች ይህን የመሰለ ባህሪ የሚያሳዩት በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ነው፡፡ ከነዚህም ዋነኞቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ የራሳቸውን ጥቅም ከሌላው አስበልጦ ማዬት፤ በሌላው ላይ የበላይነትን ለማረጋገጥ ወይም ቁርሾ ይዞ ጊዜ በመጠበቅ ብድር ለመመለስ ይሆናል፡፡ ጥቅምን ለማስጠበቅ በማስገደድና ኃይል በመጠቀም የሌሎችን እቃ ይነጥቃሉ፤ ከተቀመጡበት ቦታ በማስገደድ ያስነሳሉ፤ በመግፋት ወይም በመገፋተር የመጫወቻ ቦታዎችን ያስለቅቃሉ፡፡ ምንም እንኳን ብድር መመለስና ቁርሾ መያዝ ልጆቹ እያደጉ ሲሄዱ የሚያሳዩት ባህሪ ቢሆንም የማጥቃት፣ የማውደምና ኃይል የመጠቀም ባህሪ አለው፡፡ ስለዚህ የጠበኝነት ባህሪ የሌሎችን ልጆች ንብረትና መጫወቻ መንጠቅ፣ የማናደድ ባህሪ ነው፡፡ እርግጥ የሰውን ንብረት የመከጀልና የመሳደብ ባህሪ በማንኛውም ልጅ ላይ ሊታይ ይችላል፡፡ ሆኖም ከላይ የተዘረዘሩት ባህሪያት ረዘም ላለ ጊዜ የቆዩና በተለያዩ ቦታዎች በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ሆነው ከተገኙ ባህሪው እንደ ችግር ሆኖ ይወሰዳል፡፡ ያም ሆነ ይህ እራስን ለመከላከልና ለማዳን የሚደረግ ግብ ግብ እንደጠበኝነት ሊወሰድ አይገባም፡፡

**የችግሩ መንስኤዎች**

ልጆች ሲወለዱ ከእናታቸው ማኅፀን የአመፀኝነት ወይም የጠበኝነት ባህሪ ይዘው አይወለዱም፡፡ ምንአልባት የተፈጥሮ አዝማሚያዎች ሊኖሩ ይችሉ ይሆናል፡፡ **ለምሣሌ** በአንዳንድ የአእምሮ ዝግመት ባለባቸው ልጆች ላይ ይታያል፡፡ ይሁንና እነዚህ የተፈጥሮ አዝማሚያዎች አመቺ ሁኔታ

ካላጋጠሟቸው ሊዳብሩና ሊያድጉ አይችሉም፡፡ ስለዚህ ከቤተሰብ ያስተዳደግ ዘይቤና በአካባቢው ከአሉ ማኀበራዊ ግንኙነቶች ጋር በመጣመር የጠበኝነት ባህሪን በምልክቱ ሊቀስሙ ይችላሉ፡፡ በአካባቢው የሚገኙ ማኀበራዊ ግንኙነቶች ከትምህርት ቤት፣ ከጓደኛና ከተለያዩ ተቋማት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ በዚህ ሞጁል ሁኔታው ከቤተሰብ፣ ከትምርት ቤትና ከጓደኛ ግንኙነት አንፃር ምን እንደሚመስል ለማየት ሙከራ ይደረጋል፡፡

**ሀ. ቤተሰብ**

ቤተሰብ የልጆችን የጠበኝነት ባህሪ በመቅረጽ ከዚያም አልፎ በማዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ በቤተሰብ ውስጥ ለአመፀኝነት ወይም ለጠበኝነት ባህሪ መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ በወላጅና በልጅ መተስጋብራዊ ግንኙነት ሁኔታ ላይ የተመሠረቱ ዋና ዋና ምክንያቶች ከዚህ በታች ተጠቅሰዋል፡፡

- **አምባገነናዊነት የሰፈነበት የአስተዳደግ ዘይቤ**

  ይህ የወላጆችን የበላይነትና ማን አለብኝነት የሚያመለክትና የወላጅና የልጅ ግንኙነት በቁጣ፣ በግሳፄ፣ በዱላ ላይ የተመሠረተ የልጅ አያያዝ ስልት ነው፡፡ ከመጠን ያለፈ ቁጥጥር ማድረግን፣ ልጁን ከአቅሙ በላይ ማዘዝንና ተግባራዊ እንዲያደርግ ማስገደድን ያጠቃልላል፡፡ በዚህም መልክ ያደገ ልጅ ይማረራል፣ የጥላቻ ስሜት ያሳድራል፣ ቀስ በቀስም የእምቢተኝነትና የአምባጓሮኝነት ባህሪ ያሳያል፡፡

- **ግድየለሽነት ወይም ልቅነት የሰፈነበት ቤተሰብ**

  ስለልጁ ውሎ፣ አለባበስ፣ ጽዳት፣ ትምህርት፣ የመውጫና መግቢያ ሰዓት ግድ የሌላቸውና ስለልጁ ጉዳይ ክትትል የማያደርጉ ውላጆችን ይመለከታል፡፡ ልጆች እንደማናቸውም ሰብአዊ ፍጡር የመፈጠር፣ የመደነቅ፣ የመወደድ፣ የመከበርና እንክብካቤ የማግኘት መሠረታዊ ፍላጎት አላቸው፡፡ ሆኖም በደንታቢስ ቤተሰብ አካባቢ ልጆችን ዞሮ የሚያያቸው፣ ትክክለኛ አቅጣጫና ዓላማ እንዲይዙ የሚመራቸው የለም፡፡ ይህም ሁኔታ ልጆቹን ከማስከፋቱና ከማበሳጨቱ አልፎ የጠበኝነት ባህሪ እንዲያሳዩ ይገፋፋቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ልጆች ከአዋቂዎች ትኩረት ለማግኘት ሲሉ የአዋኪነት ባህሪን እንደመሣሪያነት ይጠቀሙበታል፡፡ እነዚህ ወላጆች የተለያዩ የማበረታቻና ገንቢ ዘዴዎች ለመጠቀም ምንም ዓይነት ሙከራ ስለማያደርጉ የልጆችን ባህሪ ለማረቅ ወይም ለማስተካከል ያዳግታቸዋል፡፡ በዚህም የተነሳ ልጆቹ እራስን የመቆጣጠር፣ ሥራን በእቅድ የመሥራት ችሎታና ሌሎችንም ተፈላጊ የማኀበራዊ ክህሎቶች አያዳብሩም፡፡ ስለዚህ የእራሣቸውን ባህሪ የመቆጣጠር ልምድ ያላዳበሩ ልጆች ወደ ግልፍተኝነት፣ ጠብ ጫሪነትና ተደባዳቢነት ያመራሉ፡፡

- **የወላጆች የችግር መፍቻ ዘዴ**

  በአንዳንድ ቤተሰብ ውስጥ በትዳር ጓደኞች መካከል አለመግባባት ሲፈጠር መፍትሔው ኃይልና ጉልበት ሆኖ ይገኛል፡፡ ነጋ ጠባ ፀብ፣ ንትርክ፣ ጭቅጭቅ በቤት ውስጥ

ይሰፍናል፡፡ የደረሰውን ግጭት ወይም አለመግባባት ለማብረድ ከኃይለቃልና ስድብ አልፎ ዱላ ዋነኛ አማራጭ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ይህን በመሰለ አካባቢ የተወለዱና ያደጉ ልጆች እነዚህን ባህሪያት በአርአያነት ከወላጆች በመቅሰም ከእኩዮቻቸው ሆነ ከአዋቂዎች ጋር ለሚያጋጥሟቸው አለመግባባቶች ተመሳሳይ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡ የዚህ ዓይነት ቤተሰብ በልጆች ላይ የጠበኝነት ባህሪ እንዲሰርጽና እንዲጎለብት ያደርጋል፡፡

- **ገደብ በግልጽ አለማስቀመጥ**

  በቤት ውስጥ ልጆች ማድረግ የሚገባቸውንና የማይገባቸውን ነገሮች በግልጽ እንዲያውቁ አለማድረግ በልጆች መካከል አለመግባባትና ግጭትን ከማስነሳቱም በላይ በልጆች ላይ ጉዳት ወይም አደጋ ሊያስከትል ይችላል፡፡

ለ. መምህራንም በመማር ማስተማሩ ሂደት ከላይ በቤተሰብ አካባቢ የተጠቀሱትን ስልቶች የሚጠቀሙ ከሆነ የጠበኝነት ባህሪ በልጁ ላይ እየገነነ እንዲሄድ ያደርገዋል፡፡ በክፍል ውስጥ የአለመግባባትና የግጭት ማብረጃ፣ የስነ-ምግባር መገንቢያ ዘዴ ስድብ፣ ጩኸት፣ ማንቋሸሽና ዱላ ከሆነ ትርፉ ጥላቻና ብጥብጥ ይሆናል፡፡ ተማሪዎችም ጥፋት ሲያጠፉ፣ ትምህርቱን በደንብ ሳይከታተሉ ሲቀሩ በግድየለሽነት ችላ ማለት እንዲሁ ችግር ላይ እንዲወድቁ ያደርጋቸዋል፡፡ በአንፃሩ ዘሎ ወደ ዱላና ስድብ መሮጥ ለተማሪው የሚፈለገውን ትምህርት ለማስተላለፍ ካለማስቻሉም በላይ የባሰ እልህ ውስጥ እንዲገባ፣ ሁኔታው እንዲባባስና ወደ አልታሰበ አቅጣጫ እንዲሄድ ሊያደደርገው ይችላል፡፡

ሐ. ልጆች ከጓደኛና ከኗሪው ኅብረተሰብ ትምህርት ይቀስማሉ፡፡ በተለይም ከጓደኞች ጋር በሚያደርጉት የቀን ተቀን የቅርብ ግንኙነት ብዙ ነገር ይማራሉ፡፡ የራሣቸውንም የእኩዮች ቡድን ይፈጥራሉ፡፡ እንግዲህ የቡድኑ አላማና ተግባር እንደ አባሉቱ ስብጥር ይወሰናል፡፡ ቡድኑ በምግባረ ብልሹ ልጆች የተገነባ ከሆነ አላማውም ሆነ ተግባሩ ወደ አልባሌ ሥራ ያዘነብላል፡፡ የቡድኑ አላማ፣ መንጠቅ፣ ማስገደድ፣ መደባደብና የመሳሰሉት ከሆነ ማንኛውም አባል ወደደም ጠላም ይህን አላማ ማራመድ አለበት፡፡ ይህን የመሰለ አላማና ተግባር የሚያራምድ ቡድን በአካባቢው ለሚኖሩ ሌሎች ልጆች መጥፎ አርአያ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የቡድኑ ዓላማ አብሮ ለመዝናናት፣ ለመጫወት፣ ለማጥናት፣ ለአካባቢው ኅብረተሰብ ለማገልገልና ሌሎችን ጠቃሚ ተግባራት ለማከናወን ከሆነ ለአባላቱም ሆነ በአካባቢው ለሚገኙ ልጆች አዎንታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡

**ችግሩን ለማስወገድ የሚረዱ ዘዴዎች**

ከላይ ለማየት እንደሚቻለው የችግሩ መንስኤዎች በተነሱበት ጎን ለጎን መፍትሄዎቻቸውንም ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡ በተጨማሪም የሚከተሉትን ነጥቦች ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት የሚወስዱትን እርምጃዎች ስኬታማ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

ሀ. የጠበኝነት ባህሪ የሚከሰቱባቸውን ሁኔታዎች በዝርዝር ማወቅ ችግሩን ለማስወገድ መንገዱን ይከፍታል፡፡

ለ. የወላጆችን፣ የልጆችን፣ የመምህራንንና የተማሪዎችን እንዲሁም በልጆች መካከል ያለውን መስተጋብራዊ ግንኙነት ከወዲሁ መልክና ሥርዓት በማስያዝ ተፈላጊውን ሥነ-ምግባር ለማራመድ ጥረት ማድረግ፤ ይህ ተግባር ለወደፊቱ በጉርምስናም ሆነ በሌሎች ተከታታይ የዕድገት ዘመናት ሊከሰቱ ለሚችሉ የባህሪ ችግሮች መወገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ የቤተሰብንና የትምህርት ቤትን የተቀናጀ የቅርብ ክትትልንና ድጋፍን ይጠይቃል፡፡ በአንድ ወገን ብቻ የሚደረግ ጥረት ፋይዳቢስ ይሆናል፡፡

ሐ. የወላጆችና የመምህራን አርአያነት ከሁሉም በላይ አስፈላጊ ሆኖ ይገኛል፡፡ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ልጆች፣ ወላጆችና መምህራን የሚያከናውኑትን ተግባር በቀላሉ በመመልከት ይቀስማሉ፡፡ በተግባር ላይም ያውላሉ፡፡ በአንድ በኩል ልጆች የጠበኝነት ባህሪን እንዲያስወግዱ እየሰበክን በሌላ በኩል ደግሞ ዱላ ከእጃችን የማይለይ ከሆነና የልዩነት መፍቻ ዘዴ ዱላ ከሆነ ጥረታችንን ሁሉ ውሃ በላው ማለት ነው፡፡

መ. የአዋኪነት፣ የጠበኝነትና የወንጀለኝነት ባህሪ የሚያራምዱ ፊልሞችን፣ ትርኢቶችንና የመጫወቻ እቃዋችን (የሽጉጥ፣ ጠብመንጃ፣ ታንክ ወዘተ) የመሳሰሉትን ለልጆች አለማሳየት ወይም አለመግዛት የተኛለ አማራጭ ነው፡፡ ልጆች በፊልሞች የሚየዩዋቸውን ነገሮች ሁሉ በተግባር ለማዋል ስለሚሞክሩ፣ የመጫወቻ ቁሳቁሶች ደግሞ ሌሎችን የማጥቃት ባህሪ እንዲያዳብሩ ሊያደርጓቸው ስለሚችሉ ማስወገዱ ተገቢ ነው፡፡ በምትኩ አስተማሪና ተፈላጊ ባሕሪያትን ሊያዳብሩ የሚችሉ የልጆች ፊልሞችንና የመጫወቻ እቃዎችን መግዛት ያስፈልጋል፡፡

ሠ. መደባደብ፣ በተደብዳቢው ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት በጥሞናና እረጋ ባለ መንፈስ ለተደባዳቢው ማስረዳት፣ እራሱን በተደብዳቢው ቦታ አድርጎ እንዲያይና በሰራው ሥራ እንዲፀፀት ማድረግ፣ ተደብዳቢውን ይቅርታ እንዲጠይቅ ለማድረግ መሞከር አስፈላጊ ነው፡፡ ይህን የመሰለውን ውይይት ለመክፈት ተደባዳቢዎች ከንዴታቸው በረድ እንዲሉ ትንሽ ፋታ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ይህን የመሰለውን ስልት መጠቀም ትክክለኛ ግንዛቤና ትምህርት እንዲቀስሙ ሲያደርግ ለወደፊቱም ከእንደዚህ አይነት ድርጊት እንዲቆጠቡ ይረዳቸዋል፡፡

ረ. የሌላ ሰው ንብረት በጉልበት ወይም በማስገደድ ነጥቀው ሲገኙ ይህ አግባብ አለመሆኑን ማስረዳት፤ በምትኩ አግባብ የሆነውን መንገድ ማሳየት፤ **ለምሣሌ** ተራ በተራ የመጫወት፣

በጋራ አብሮ የመጫወት፣ የመተባበርን፣ የመግባባትንና የመተጋገዝን ባህሪ ልምድ ማዳበር፤ የመጫወቻ እቃዎችንና ቦታዎች በጋራ የሚጠቀሙበት ሁኔታዎች ማመቻቸት፤

ሰ. ራስን የመቆጣጠር ችሎታ እንዲያዳብሩ ማስተማር፤ ግንፍልተኝነትና ቁጡነት ወደ ጠበኝነት ባህሪ ሊያመራ ስለሚችል ልጆች ከወዲሁ ይህን ባህሪ የመቆጣጠር ችሎታ እንዲያዳብሩ መርዳት፤ ባህሪን መቆጣጠር መቻል ልጆች አንድ ነገር ከማድረጋቸው በፊት መልሰው መላልሰው እንዲያስቡበት ከማድረጉም በላይ የሚሰሯቸውን ተግባራት ሁሉ ዕቅድና ግብ እንዲኖራቸው ይረዳቸዋል፡፡ በተደጋጋሚ ስህተት ከመሥራትም ያድናቸዋል፡፡ አንድ ድርጊት ወይም እርምጃ ከመውሰዳቸው በፊት በአእምሯቸው የማውጣትና የማውረድ ባህል እንዲያዳብሩ ማስተማር ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ወላጆችም ሆኑ መምህራን በመጀመሪያ ደረጃ የግብታዊነትና የግንፍልተኝነት ባህሪን ማስወገድ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሸ. በልጆች መካከል ምንም ዓይነት አድልዎና ልዩነት ከማሳዬት መቆጠብ፤ በተቻለ መጠን ሁሉንም በአንድ ዓየነት ማየት፤ ለልጆቹ የሚሰጠውን ፍቅርና እንክብካቤ ተለዋዋጭ እንዳይሆን አስፈላጊውን ጥንቃቂ ማድረግ፤

ቀ. በቤትም ውስጥ ሆነ በትምህርት ቤት ከልጆቹ ምን እንደሚጠበቅ፣ ማድረግ የሚገባቸውንና የማይገባቸውን መብትና ግዴታቸውን ለይቶ መጀመሪያውኑ በግልጽ ማሣወቅ በአዋቂዎችና በልጆች መካከል ሊነሳ የሚችለውን ግጭት ሊከላከል ይችላልል፡፡ **ለምሳሌ** ልጆች ደብተሮቻቸውን በሚገባ እንዲይዙ፣ የቤት ሥራና የክፍል ሥራ በተባለው ጊዜ መሥራት እንዳለባቸው የክፍል ውስጥ ስነ-ስርዓት እንዲጠብቁና የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

### 1.18.9.4 የዕረፍተቢስነት ባህሪ

**የችግሩ ገጽታ**

አንዳንድ ልጆች ከመጠን ያለፈ መንቀዥቀዥና በቀላሉ የመረበሽ ባህሪ ከማሳየታቸውም በተጨማሪ የማስተዋልና አንድ ተግባር ላይ ለተወሰነ ጊዚ የመቆየት ችግር ይታይባቸዋል፡፡ አንድ ቦታ ረጋ ብለው መቀመጥ ይሳናቸዋል፡፡ ያዝ ለቀቅን ከመጠን በላይ ያበዛሉ፡፡ የሚነገራቸውንም አይሰሙም። ሁልጊዜ በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛሉ፡፡ በክፍል ውስጥ እቃዎችን በማተራመስ፣ ጎናቸው የተቀመጡትን ዕረፍት በመንሣት የታወቁ ናቸው፡፡ እንዲሁም በጨዋታም ሆነ በሌላ ሥራ ላይ ጣልቃ በመግባት እንቅፋት ይሆናሉ፡፡ ንብረታቸውን ማለትም ደብተር፣ እርሳስ፣ መጫወቻ፣ የመሳሰሉትን በሥርዓት አይዙም፡፡ በእጃቸውም ለብዙ ጊዜ አይቆይም፡፡ ሆኖም እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ባህሪያት እንደ ችግር የሚወሰዱት ከመጠን ሲያልፉና ረዘም ላለ ጊዜ በልጆቹ ላይ በተደጋጋሚ ሲታዩ ብቻ ነው፡፡

**የችግሮቹ መንስኤዎች**

ይህ ባህሪ ተፈጥሮአዊ አዝማሚያ ሊኖረው እንደሚችል ጥናቶች ቢዘግቡም ከአካባቢያቸው ከሚያገኙት የእንክብካቤ ዓይነትና ምላሽ ችግሩን ሊያባብሱት ይችላል፡፡ **ለምሣሌ** አንድ ልጅ የያዘውን ጨዋታ ትቶ ወደ ሌላ ሲቀይር አንድም ተሰላችቶ ሊሆን ይችላል አሊያም ከመጥፎና ቅሬታ ከሚያስከትሉ ችግሮች ለመራቅ ብሎ ይሆናል፡፡ ጨዋታውን በሚገባ መጫወት የማይችል ከሆነ ድክመቱን ለመሸፈን ወደ ሌላ ጨዋታ ዞር ሊል ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ በማስገደድ የጀመረውን ተግባር ወይም ጨዋታ እንዲጨርስ ግብ ግብና እልህ ውስጥ መግባት አያስፈልግም፡፡ እንዲሁም እነዚህ ልጆች በጣም ችኩሎችና ፈጣኖች ስለሆኑ ብዙ ስህተቶች ሲሰሩ ይታያሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ከመምህራንም ሆነ ከወላጅ የሚያገኙት ምላሽ ትችትና ዱላ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ የተነሳ ልጆቹ በተቻለ መጠን መጥፎ ውጤት ያስከትላሉ ብለው ከሚገምቷቸው ተግባራት ለመራቅ ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ **ለምሣሌ** ስህተት ሲሰራ ከመምህሩም ሆነ ከወላጆች የሚሰነዘርባቸው ትችትና ቅጣት ከሆነ ይህንን በመፍራት የጀመሩትን ሥራ ለማገባደድ ፈቃደኛ አይሆኑም፡፡ ስለዚህ የያዙትን ትተው ሌላ ሥራ መሥራትን ይመርጣሉ፡፡ በዚህ ስልት ሥጋታቸውን ያቃልላሉ፡፡ ደካማነትን መሸፈኛና የበታችነት ስሜትን ማስወገጃ ዘዴ ያደርጉታል፡፡ ይሁንና ልጆቹ በተደጋጋሚ ስህተት የሚሠሩት ከችሎታና እውቀት ማነስ የተነሳ ላይሆን ይችላል፡፡ ከችኩልነታቸው የተነሳ የማገናዘቢያና የማሰቢያ ጊዜ የላቸውም፡፡ ይሄም በክፍል ውስጥ ስራ፣ በቤት ስራና በፈተና ጊዜ ዝቅተኛ ውጤት እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል፡፡ በቤት ውስጥ በወላጆች የሚሰጣቸውን ስራ በሚገባ አያጠናቅቁም።

**ችግሩን ለማስወገድ የሚረዱ ዘዴዎች**

ሀ. ልጆች ይህን ባህሪ የሚያሳዩባቸውን ጊዜያትና ሁኔታዎች ለይቶ መገንዘብ፣

ለ. የተለያዩ አጫጭር የግልም ሆነ የቡድን ትኩረትን የሚጠይቁ ጨዋታዎችና ተግባራት በማዘጋጀት ከአጠገባቸው ባለመራቅ ለሚያሳዩት የማተኮርና የመተባበር ባህሪ አስፈላጊውን እውቅናና ሙገሳ ማድረግ፤ ቀስ በቀስም የጨዋታውን ጊዜ ማስረዘም፤ ይህም በሚደረግበት ጊዜ የጨዋታው ወይም የተግባሩ ዓይነት ከልጁ ፍላጎት ጋር የሚሄድና ችሎታቸውን በሚገባ የመጠነ መሆን አለበት፡፡ ተግባሩ ወይም ጨዋታው ከቀላል ወደ ውስብስብ ቀስ በቀስ እያመራ የሚሄድ ቢሆን ይመረጣል፡፡

ሐ. ከልጅ ጋር በሚደረግ ግንኙነት ቁጣን፣ ስድብንና ዱላን በማስወገድ ነፃና ትእግስት የተሞላበት አካባቢን መፍጠር፡፡ ስድብና ዱላ በልጆቹ ላይ ሥነ-ባህሪያዊና አካላዊ ጉዳት ከማድረሱ ባሻገር ዕረፍተቢስነትን የሚያባብስ እንጂ የሚያስታግስ ሆኖ አልተገኘም፡፡

መ. የማስተዋልና ረጋ የማለት ልምድ ማዳበር፤ ልጆቹ በማስተዋልና ረጋ ባለ መንፈስ ሲንቀሣቀሱ ስህተቶችን ከመሥራት እንደሚድኑ በግልጽ ማስረዳት፤ በተግባርም እንዲያሳዩ ማበረታታትና ለሚየሳዩትም የመሻሻል ጥረት ተገቢውን አድናቆት መስጠት፤

ሠ. በአርአያነትም አንዳንድ አስተዋይ ልጆች አንዳንድ ተግባራትን ሲያከናውኑ እንዲመለከቱና እንዲከተሉ መገፋፋት ለውጤቱ መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ ከተቻለ የአስተዋይ ልጆችን ገጽታ የሚያሳዩ ፊልሞችን ማሳየት፤ ስለአስተዋይ ሰዎች የሚተርክ መጽሐፍ ማንበብና ተረት መንገር ጠቃሚ ነው፡፡

ረ. ልጆች በአንድ ጊዜ አንድ ተግባር ላይ አትኩሮት እንዲኖራቸው መምከር፤ ለዚህም መስዕብ ያላቸውን ተግባራት በመምረጥ ተግባራቱን በማድነቅና በመገረም የልጆችን ሃሣብ ለማሰባሰብ መሞከር፤ ለዚህም ይረዳ ዘንድ በተቻለ መጠን የልጆቹን አትኩሮት ሊበትኑ የሚችሉ ሁኔታዎችን ከአካባቢ ማስወገድና በአንፃሩ የልጆቹን ፍላጎት መሠረት በማድረግ የተለያዩ ተግባራትን በመምረጥ በቅደም ተከተል ተግባራቱን አንድ በአንድ የሚያከናውኑበትን መንገድ ማመቻቸት፤

ሰ. የጭንቀት መንፈስ ሲታይባቸው በረጋ መንፈስ ማወያየት፣ መምከርና ከስጋት ነፃ እንዲሆኑ ጥረት ማድረግ፤

### 1.18.10 ለልጆች ትምህርት ስኬታማነት የሚረዱ መሰረታዊ ጉዳዮች

የትኩረትን ምንነት ግለፁ?

________________________________________

________________________________________

#### 1.18.10.1 የትኩረት ምንነት

ትኩረት የአእምሮን በአንድ ነገር ወይም ጉዳይ ላይ የማስተዋልን ችሎታ ያመለክታል፡፡ ልጆቹ እያደጉ ሲሄዱ ከአንድ ነገር ወይም ጉዳይ በላይ የማስተዋል ችሎታ እያዳበሩ ይሄዳሉ፡፡ ይህን ተግባር ማከናወን የሚቻለው የተለያዩ የስሜት ሕዋሳትን በመጠቀም ነው፡፡ ምንም እንኳን ሁሉም የስሜት ሕዋሳት የግንዛቤን አድማስ ለማስፋት አስተዋጽኦ ማድረጋቸው ቢታመንበትም በተለይ የማየትና የመስማት ስሜቶች ከሁሉም በላይ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ስለሆነም በምልከታ፣ በማዳመጥ፣ በንባብና በጽሑፍ የሚቀሰሙ የቀለም ትምህርቶች በማየትና በመስማት ሕዋሳት አጋዥነት ይከናወናሉ፡፡ የአትኩሮት ችሎታ ከግለሰብ ግለሰብ ይለያያል፡፡ አንዳንድ ልጆች በቀላሉ የማተኮርና በያዙት ተግባር ላይ ረዘም ላለ ጊዜ መቆየት ሲችሉ ሌሎቹ ደግሞ ለማተኮር ጊዜ ሲወስዱና ቶሎ አትኩሮት የማጣት ሁኔታ ይታይባቸዋል፡፡

#### 1.18.10.2 የትኩረት አስፈላጊነት

ትኩረት ለማንኛውም ሰው በየትኛውም የዕድገት ዘመን አንድን ተግባር በሚገባ ለማከናወን እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ልጆችም ሆኑ አዋቂዎች የሚሰሩት ስራ ውጤታማ ሊሆን የሚችለው አእምሯቸው ሙሉ በሙሉ በተግባሩ ላይ ማተኮር ሲችል ነው፡፡ ትኩረት ከቀላል የዕለት ከእለት ተግባር እስከ ከፍተኛ የንድፈ ሃሣብ ተግባር ለማከናወን አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ በመንገድ ላይ

እየሄድን ትኩረት ስናጣ ከሰው ጋር ልንጋጭ እንችላለን፣ ገደል እንገባለን፣ የመኪና አደጋ ሊያጋጥመን ይችላል፡፡ ትኩረት ከሌለ አእምሮ ስለአካባቢው ተገቢን ግንዛቤ ማግኘት ያዳግተዋል፣ እንዲሁም ምላሽ መስጠት ይሳነዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በአጭር ጊዜ ውስጥ ውጤት ያለው ሥራ ሲሰራ አንዳንዴ ደግሞ በመዋዠቅና ውጤት አልባ በመሆን ብዙ ጊዜ የሚጠፋው ምናልባትም በዚህ ትኩረት በማጣት ምክንያት ሊሆን ይችላል። የማተኮር ልምድ ከልጅነት ዘመን ጀምሮ ተኮትኩቶ ማደግና መበልፀግ ይኖርበታል፡፡ ልጆች አካባቢያቸውን በሚገባ ጠለቅ ብለው እንዲገነዘቡና የአእምሮም ሆነ የማኀበራዊ ዕድገት አድማሳቸው እንዲሰፋ ይረዳል፡፡ ይህም የሚኖራቸው ግንዛቤ ላይ ላዩን ወይም ግልብ ሳይሆን ሥር የሰደደና የበለጠ ትኩረትና ምርምር እንዲያደርጉ ይገፋፋቸዋል፡፡ በዚህ በኩል ወላጆች ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡ **ለምሣሌ** ልጆች በቤት ውስጥ በቅጥር ግቢ በጎረቤት አካባቢ፣ በመንገድ ላይ ወዘተ. ያሉትን ሁኔታዎች እንዲያስተውሉና በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ለመሆኑ ስንቶቻችን ነን በቤት ውስጥ ያሉ ቁሣቁሶችን ስምና አገልግሎት፣ ግቢ ውስጥ የሚገኙ አበባዎችንና ዛፎችን፣ እንዲሁም ወፎችን በስም ለይተን የምናውቅ? የእነዚህ ጥያቄዎች መልስ በአብዛኛው ከአደግንበት የአስተዳደግ ዘይቤ ጋር የተቆራኘ ይሆናል፡፡ በአጭሩ ዛሬ በቤት ውስጥና በግቢ ውስጥ ስላሉ ቆሣቁሶች፣ እንስሳትና አበባዎች ጉዳይ ማስተዋል የጀመረ ልጅ ነገ በትምህርቱ ተመራማሪ፣ ጠያቂና ውጤታማ የመሆን ተስፋው ከፍተኛ ነው፡፡

የቅደሙ-መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራንም አስቀድመው ቁጥርና ፊደል ቆጠራ ከመግባታቸው በፊት ልጆች መሠረታዊ የመማሪያ ክህሎቶችን እንዲያዳብሩና በአእምሮም ሆነ በሥነ-ባህሪ ለመደበኛ ትምህርት ዝግጁ እንዲሆኑ ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ ዘሎ ወደ ቀለም ትምህርት መሄድ በልጆቹ ላይ ጫናና ጭንቀት ሊያመጣ ይችላል፡፡ ትምህርቱን ከአካባቢው ጋር በማዛመድ ልጆች ከሕይወታቸው ጋር በማገናዘብ እንዲያጣጥሙት በማድረግ የልጆቹን የመማር ትኩረት ለመሳብ ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ የዚህ ዓይነቱ ችሎታ በልጆቹ አእምሮ ውስጥ ሰርፆ በመዳበር ልምድ እንዲሆን ከተፈለገ ከቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤት ዘመን ጀምሮ ተኮትኩተው ማደግ አለባቸው፡፡ የልጆቹ ትኩረት በትምህርቱ ላይ ከሌለ ልፋቱ ሁሉ ከንቱ ነው፡፡ በአንድ ተግባር ወይም ጉዳይ ላይ በተመስጦ የማተኮር ልምድ ተኮትኩቶ እንዲያድግ የቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ከፍተኛ ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል፡፡

አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ጎበዝ ተማሪዎች አለወትሯቸው ዛሬ የተማርኩት ምንም አልገባኝም ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ዋነኞቹ ምክንያቶች ግን የተማሪው ትኩረት ማጣት ወይም መምህሩ ትምህርቱን በሚገባ ባለማቅረብ የተነሳ ሊሆኑ ይችላሉ። ምናልባትም በመምህሩ የአቀራረብ ጉድለት ምክንያት ተማሪው አትኩሮት ሊያጣ ይችላል፡፡ በአገራችን “ልብ ካላየ ዓይን አያይም” የሚለው አባባል የትኩረት አስፈላጊነትን ያንፀባርቃል፡፡

በአካል ክፍል ውስጥ መቀመጥ ብቻ ትምህርት መቅሰም አያስችልም፡፡ የአእምሮን ትኩረት ማግኘት አስፈላጊ ነው፡፡ የትኩረት አስፈላጊነት ይህን ያህል መሆኑን ከተገነዘብን በትምህርት ላይ የማተኮር ድክመት መንስኤዎች ምን ምን እንደሆኑ ለማየት እንሞክራለን፡፡

### 1.18.10.3 በትምህርት ላይ የማተኮር ድክመት መንስኤዎች

የማተኮር ድክመት መንስኤዎችን በሁለት ክፍሎ ማየት የሚቻል ቢሆንም ተወራራሽና እርስ በርሳቸው የተያያዙ ሆነው ይገኛሉ፡፡

**I. ከግለሰቡ ሊመነጩ ከሚችሉ ጉዳዮች**

**ሀ. የጤንነት አለመስተካከል**

የተለያዩ ውስጣዊ የበሽታ ስሜቶች ተማሪውን ትኩረተቢስ ሊደደርጉት ይችላሉ፡፡ የግለሰቡ ትኩረት ወደሚሰማው ውስጣዊ ስቃይ ስለሚሆን ተማሪው ትኩረቱን ወደ ትምህርቱ ወይም ጥናቱ ላይ ማድረግ ይሳነዋል፡፡ ለምሣሌ ሆዱን የሚቆርጠው፣ ራሱን የሚያመው ወይም መቀመጥ የሚሳነው ከሆነ ትኩረቱን ወደሚፈልገው አቅጣጫ ለመውሰድ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

**ለ. የራስን ንጽህና አለመጠበቅ**

የአካልን፣ የፀጉርንና የልብስን ንጽህና በሚገባ አለመያዝ የተማሪውን አትኩሮት ይበታትነዋል፡፡ አካሉን የሚያሳክከው፣ ፀጉሩን የሚበላው፣ ልብሱ የቆሸሸና ጠቅላላ ጽዳቱ ያልተጠበቀ ተማሪ ትምህርቱን ክፍል ውስጥ ለመከታተል ወይንም ጥናቱ ላይ አትኩሮት ለማግኘት አስቸጋሪ ይሆንበታል፡፡

**ሐ. ዓላማቢስነት**

ዓላማ የሌለው ተማሪ ለትምህርቱ ደንታቢስ ይሆናል፡፡ ይህም ቸልተኝነትን፣ ጥላቻንና ስንፍናን በማስከተል ውስጣዊ የመማር ግፊት ያሳጣዋል፤ በትምህርቱ ላይ የማተኮር ፍላጎት አይኖረውም፤ ዓላማና ግብም ስለሌለው ስራውን በዕቅድ መስራት ያዳግተዋል፤ ድርጊቱም ግብታዊ ይሆናል፡፡ ለምሣሌ፡- ሲፈልግ ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳል፤ ካልፈለገ ደግሞ ይቀራል፤ የቤት ሥራ የሚሠራበትና የሚያጠናበት ጊዜም የለውም፡፡

**መ. በቂ አእምሯዊና አካላዊ ዝግጁነት አለመኖር**

ውስጣዊ ደስተኝነትና አእምሮአዊ ዝግጁነት ሳይኖር በማስገደድ ለማስተማር ወይም ለማስጠናት መሞከር ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊብስ ይችላል፡፡ የአእምሮና የአካል ንቃት በመማርና መመራመር ሂደት ውስጥ እጅግ ተፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ የእነዚህ ሁኔታዎች አለመኖር የተማሪውን የመማር ሂደት አደጋ ላይ ይጥለዋል፡፡

**ሠ. የእንቅልፍ እጦት**

አእምሯችንና አካላችን መደበኛ ዕረፍት ካላገኘ የሚፈለገውን ተግባር ለማከናወን ጉልበትና ኃይል ያንሰዋል፡፡ የእንቅልፍ እጦት ድካም፣ መፍዘዝ፣ ማዛጋትና ራስ ምታትን የመሳሰሉ ስሜቶችን ያስከትላል፡፡ አእምሮም ማተኮር ይሳነዋል፡፡ አካልንም ይደክመዋል፡፡

**ረ. ጭንቀት**

ጭንቀት ሃሳብን ይበታትናል፣ ትኩረትን ያሳጣል፡፡ በመሰረቱ ጭንቀት የሰው ልጅ ሕይወት አካል ነው፡፡ ማንኛውም ሰው መጠነኛ ጭንቀት ሊሰማው ይችላል፡፡ ሃሣብን አሰባስቦ ችግርን ለማቃለል፣ አደጋን ለመከላከልና አላማን ከግብ ለማድረግ አስፈላጊነቱ አያጠራጠርም፡፡ በሌላ በኩል ጭንቀት ከመጠን ሲያልፍ በስብዕና ላይ ሥነ-ባህሪያዊ ተፅዕኖ በማስከተል ጉዳት ላይ ይጥላል፡፡ ትኩረትም እንዲበታተን ያደርጋል፡፡

የቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን እነዚህን ከግለሰብ ሊመነጩ የሚችሉ የማተኮር ድክመት መንስኤዎችን በመለየት ተገቢውን ድጋፍ ለተማሪዎቻቸው ሊሰጡ ይገባል፡፡

## II. ከአካባቢ ሊመነጩ የሚችሉ ምክንያቶች

**ሀ. ከቤተሰብ**

በልጆች ላይ የሚደርሱ ብዙ በደሎች በቤተሰብ አካባቢ እንደሆኑ ብዙ ጥናታዊ ጽሑፎች በተደጋጋሚ ዘግበዋል፡፡ አንዳንዶቹ ምክንያቶች የሚከተሉትን ይመስላሉ፡፡ ከቤተሰብ ጋር የተያያዙ ምክንያቶች፡- በቤተሰብ መካከል ሰላም አለመኖር፣ ፍቺ፣ የቤተሰብ ገቢና የትምህርት ደረጃ ዝቅተኝነት፣ የአስተዳደግ መዛባት ወይም ሥርዓት ማጣት፣ የወላጆች መጥፎ አርአያ መሆን፣ ልጅ ከቤተሰብ የሚጠብቀውን ድጋፍና ፍቅር ክትትል አለማግኘት ወዘተ… ልጆች በትምህርታቸው ላይ ትኩረት እንዳይሰጡ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

**ለ. ትምህርት ቤት**

የትምህርት ቤት ስነ-ባህሪያዊና ማኅበራዊ ሁኔታዎች አለመመቻቸት በተማሪዎች ላይ ለሚታዩ የስነ-ባህሪ ጉድለቶች መንስኤ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የሚከተሉት ነጥቦች በመንስኤነታቸው በተደጋጋሚ በጥናቶች ተዘግባዋል፡፡

- አሉታዊ የስነ-ምግባር መገንቢያ ዘዴ መጠቀም፡- መምህራን በኃይልና በጉልበት ሥርዓት ማስከበርን እንደ መሣሪያ አድርገው የሚጠቀሙ ከሆነ የመምህራንና የተማሪዎች ግንኙነት በጭንቀትና በፍርሃት ላይ የተመሠረተ ይሆናል፤
- የአንዳንድ መምህራን የትምህርት አቀራረብ ብቃት ማነስ፣ ለምሣሌ በቂ ዝግጅትና የማስተማር ዕቅድ አለመኖር፤
- የአንዳንድ መምህራን ስነ-ምግባር ለተማሪዎች መልካም አርአያ ሆኖ አለመገኘት፡- ለምሣሌ ጠጥቶ ትምህርት ቤት መምጣት፣ ከሥራ ገበታ መቅረት፣ ጽዳትንና አለባበስን በሚገባ አለመጠበቅና እራስን መጣል፤
- የፈተና አወጣጥና ግምገማ መዛባት፡- ለምሣሌ የጥያቄ አወጣጥ ስልቶችን ጠንቅቆ አለማወቅና የተማሪውን ውጤት በዘፈቀደ መስጠት፤

- በቂ የማስተማሪያ ቁሳቁስ አለመኖር፡- ለምሣሌ መጻሕፍት፣ ጠመኔ፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ ለቤተ ሙከራ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎች እጥረት፤
- የስርዓተ ትምህርቱ ይዘታ ከተማሪው ሕይወትና ፍላጎት ጋር አለመዛመድ፤
- ደካማና ስርዓት ያጣ የትምህርት ቤት አስተዳደርና አስተዳደሩም ከመምህራን ጋር ያለው ግንኙነት የተበላሸ መሆን፤
- በተማሪዎች መካከል ያለው የስነ-ምግባር መዘበራረቅ፤
- አንዳንድ መምህራን በተማሪዎች ስነ-ምግባር ጉዳይ ላይ ግድ የለሽ መሆን እና
- በቤተሰብና በመምህራን መካከል ግንኙት አለመኖር ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

**ሐ. ቡድን/ጓደኛ**

ልጆች በሰፈርም ሆነ በትምህርት ቤት አካባቢ ከእኩዩቻቸው ጋር በጓደኝነት የተመሠረተ ቡድን ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ልጆች በቡድን አማካይነት ብዙ በጎም ሆነ መጥፎ ነገሮችን ይማራሉ፡፡ በተለይም በዕድሜ እየጎለበቱ ሲሄዱ በቡድናቸው ላይ ያላቸው እምነትና አክብሮት እየጨመረ ስለሚሄድ ተቀባይነትን ለማግኘት የቡድኑን ደንብና ስርዓት በተግባር የማዋል ግዴታ ውስጥ ይገባሉ፡፡ ቡድኑ በማን አለብኝነት፣ በአጥፊነት፣ በዱርዬነትና በጨካኝነት ተግባር ላይ የተሰማራ ከሆነ አባላቱም ይህን ከማንፀባረቅ ውጭ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ይህን ካላደረጉ ከቡድኑ አባልነት እንዲወገዱ ይገደዳሉ፡፡

መምህራንም አንዳንድ በትምህርታቸው ላይ ትኩረት የማያደርጉ ተማሪዎችን በመከታተል፣ በጥሞና ውይይት በመክፈትና ችግራቸውን በመረዳት ተገቢውን ድጋፍ መለገስ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህን የመሰለ ችግር በኃይልና በዱላ ለማስተካከል መሞከር ሆኔታውን ከማባባስ በስተቀር ሌላ የተለየ ጥቅም አይኖረውም፡፡

### 1.18.10.4 መሰረታዊ የአጠናን ዘዴ

ተማሪውን ውጤታማ ሊያደርገው የሚችለው ክፍል ውስጥ የሚከታተለው ትምህርት ብቻ አይደለም፡፡ ከክፍል ውጭ በሚሆንበት ጊዜ የቀሰመውን ትምህርት በበለጠ ለመረዳትና ለማበልፀግ በግልም ሆነ በቡድን የሚያደርገው ጥናትና ምርምር ለተማሪው ውጤታማነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ይህንንም ሁኔታ ከግንዛቤ በማስገባት በዚህ ንዑስ ክፍል ለተማሪዎች ስኬታማ ውጤት ሊያስገኙ ይችላሉ የሚባሉ አመላካች የጥናት ስልቶችን ለመጠቆም ሙከራ ተደርጓል፡፡ መምህራን ከእነዚህ ነጥቦች ግንዛቤ በመውሰድ የልጆቹን ያጠናን ዘዴ ከወዲሁ መልክ ለማስያዝና ለመምራት ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ልጆች በልጅነት ዘመናቸው ትክክለኛውን አቅጣጫና ፈር እንዲይዙ ከተደረገ ለወደፊቱ በትምህርታቸው አመርቂ ውጤት ለማምጣት ይጣጣራሉ፡፡

ቀደም ሲል በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የትኩረትን አስፈላጊነት በአጠቃላይ ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡ አሁንም በተለይ ተማሪዎች ከክፍል ውጭ በሚያደርጉት ጥናት ሙሉ አትኩሮት ኖሮአቸው ጥናቱም ውጤታማ ይሆን ዘንድ የሚከተሉትን ነጥቦች እንደመመሪያ አድርገው በተግባር ላይ ቢያውሉ ከፍተኛ አገዛ ያደርጋሉ የሚል ግምት አለ፡፡

**ሀ. አካላዊ ዝግጅት**

- ንጽሕናን መጠበቅ፣ የአካል፣ የፀጉር፣ የእግር፣ የልብስ ወዘተ፣
- ጤናን ከበሽታ ከወዲሁ መከላከል ይህ ካልሆነ ደገሞ መታከም፡፡
- በቂ እንቅልፍ መተኛት አእምሮን ከማደሱም በላይ ብርታትና ኃይል ይሰጣል፡፡
- ምግብን በልክ መብላት፣ ከመጠን በላይ በልቶ በቁንጣን መጨነቅ በአትኩሮት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅእኖ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ምግብ እንደበሉ ተቻኩሎ ለማጥናት አለመጣደፍ፣ ከፅሩብ እስከ ግማሽ ሰዓት ፋታ ማግኘት፤ በጥናት ጊዜ ቀና ብሎ ነቅቶ መቀመጥ ያስፈልጋል፡፡ አልጋ ላይ ተጋድሞ ለማጥናት አለመሞከር፤ ምቹ ወንበሮችን እንደሶፋ የመሳሰሉትን አለመጠቀም፤

**ለ. ስነ-ባህሪያዊ ዝግጅት**

- በውስጣዊ ስሜት፣ በእራስ አነሳሽነትና ፍላጎት ካለምንም የውጭ ግፊት የማጥናት ባህል ማዳበር፤ መልፈስፈስንና መዳከምን አስወግዶ በፍላጎትና በንቃት ጥናቱን ማካሄድ፤
- ዓላማን ጠንቅቆ ማወቅ፣ አእምሮን ለዚሁ ተግባር ማዘጋጀት፤
- የአጭርና የረዥም ጊዜ የጥናት ዕቅድ የማውጣት ልምድ ማዳበር፤
- ጥናቱን ከሕይወት ጋር በማዛመድና በማመዛዘን ለማጣጣም መሞከር፤
- አእምሮንና አካልን ማዝናናት፣ ከጭንቀት ነፃ ማድረግ፣ ጥናቱ ውጤት እንዲኖረው ችክ ብሎ ራስን ከማድከም መታቀብና በአንፃሩ በጥናቱ ጣልቃ አእምሮን ማዝናናት፣ ለምሣሌ፡ ሰውነትን ማፍታታት፣ ሙዚቃ ማዳመጥ፣ ሥራን መለዋወጥ (ከአእምሮ ሥራ ወደ ጉልበት ሥራ መቀየር)፣ ሻይ ወይም ዳቦ ወይም ሌላ ነገር ከተገኘ በጥናቱ ጣልቃ መቅመስ፣ በጥናቱ መካከል የሚደረገው ዕረፍት ከ 5 - 10 ደቂቃ ቢሆን መልካም ነው፡፡

**ሐ. የማጥኛ ስፍራ ማመቻቸት**

- ክፍሉ ወይም ቦታው በቂ ብርሃንና ንፁህ አየር እንዳለው ማረጋገጥ፤
- የጥናቱ ቦታ ከጥናቶች ጋር ያልተያያዙ ነገሮች እንዳያጣብቡት ጥንቃቄ ማድረግ፣ ይህም ሃሳብ እንዳይበታተን ይረዳል፤
- ጥናቱ ከመጀመሩ በፊት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑና ከጥናቱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን እንደ መጽሃፍት፣ መዝገበ-ቃላት፣ እርሳስ፣ መቅረጫ፣ ወረቀት ወዘተ በቅድሚያ ማዘጋጀት፤

- በተቻለ መጠን የጥናቱን ሥፍራና ጊዜን አለመለዋወጥ፤
- ቤተ መጻሕፍት ሄዶ የማጥናትና መጽሐፍትን የማንበብ ልምድ ማዳበር፡፡

**መ. ተግባራትን የማከናወኛ ዕቅድ ማውጣት**

የጥናት፣ የመዝናኛና የማኅበራዊ ጉዳዮች መፈጸሚያ ጊዜ መወሰን፤ ይህም ተማሪዎች ጊዜያቸውን አላግባብ አልባሌ ቦታ እንዳያውሉ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ሥራን በዕቅድና በስርዓት የመሥራት ልምድ ከወዲሁ እንዲያዳብሩ ይረዳል፡፡ በተጨማሪም "ምን ላጥና?" "ምን ልሥራ?" "የት ልሂድ?" በማለት ሊወሰዱ ከሚችሉ ግብታዊ እርምጃዎች ይገታል፡፡ ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀም ይገፋፋል፡፡እንዲሁም ሃሳብ እንዳይበታተን፣ የማመንታት ዝንባሌ እንዳይኖርና በሥራችን ላይ ለማተኮር አዎንታዊ ተፅእኖ ይኖረዋል፡፡ ያዝ ለቀቅ ነገ ከነገወዲያ እየተባለ በቀጠሮ እየተላለፈ የሚከመር ጥናት በተማሪው ላይ ከፍተኛ ጫናና ስጋት ያስከትላል፡፡ ይህም "ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ" የሚባለውን አገርኛ አባባል ያስታውሰናል፡፡ ፈተናው ነገ ሆኖ ዛሬ የሚደረገው መሯሯጥ አንድም ተማሪውን ጭንቀትና ፍርሃት ውስጥ ሲጥለው በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ መልክ የሚካሄደው ጥናት በተማሪው አእምሮ ውስጥ ሰርፆ መግባቱ ያጠራጥራል፡፡ ተማሪዎች በአንደኛው ሴሚስተር በጥሩ ውጤት ያለፉበትን ትምህርት በሁለተኛው ሴሚስተር ሲጠየቁ ማስታወስ የሚሳናቸው በዚህ ምክንያት ሊሆንይችላል። ይህም ማለት ሳያጣጥሙት እንደተዋጠ እህል ማለት ነው፡፡ ተማሪው የሚያወጣውን የተግባር ዕቅድ አበክሮ ለወላጆችና ለጓደኞች ማሣወቅ መልካም ነው፡፡ ይህም በወላጆችና በጓደኞች ምክንያት ሊመጣ የሚችለውን ጣልቃ ገብነት ብሎም የፕሮግራም ማፋለስ ለመከላከል ያስችላል፡፡ ከዚህ አንጻር ቢቻል መጀመሪያውኑ ከወላጆች ወይም ከጓደኞች ጋር የተግባር ዕቅዱ አብሮ ቢወጣ መልካም ነው፡፡ ወላጆችም ዕቅዶችን በማክበር ግብታዊ የሆኑ ትዕዛዞችን ከማስወገድ ባሻገር ሆኔታዎችን የማመቻቸት ኃላፊነትም አለባቸው፡፡

**ሠ. የሚጠኑ ትምህርቶችን መርጦ ጊዜ መደልደል**

ለእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት የሚሰጠው የጥናት ጊዜ እንደተማሪው ችሎታና እንደሥራው ብዛት መወሰን ይኖርበታል፡፡ በሚጠናበት ጊዜ መሰላቸት እንዳይመጣ የሚጠናውን የትምህርት ዓይነት መለዋወጥ፣ ስርዓቱንም መቀያየር ለምሣሌ፡ ከንባብ ወደ ጽሁፍ፣ ከጽሁፍ ወደ ማዳመጡ ወዘተ መቀየር ይገባል። ያጠናኑን ቅደም ተከተል በተመለከተ ከበድ የሚሉ ትምህርቶችን አእምሮ ንቁ በሆነበት ጊዜ ለማጥናት ዕቅድ ማውጣት የተሻለ ውጤት ያስገኛል፡፡ ሆኖም ምርጫውን ለግለሰቡ መተው መልካም ነው፡፡

**ረ. የጥናት ጊዜን ድካም በማይሰማበት ጊዜ ማድረግ**

ለጥናት የሚመደበው ሰዓት ተማሪው ድካም በሚሰማው ጊዜ ሳይሆን፣ አእምሮው ትምህርት ለመቀበል ዝግጁ በሚሆንበት ጊዜ እንዲሆን ጥረት ማድረግ የተሻለ ውጤት ያስገኛል።

**ሰ. የሚጠናውን ነገር ፍሬ ሃሳብ መረዳት**

ጥናት በሚጠናበት ጊዜ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ፍሬ ነገሩን ለመጨበጥ ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ **ለምሣሌ** ፍሬ ነገሩን ከሕይወት ወይም የዕለት ከዕለት ተግባራት ጋር ለማዛመድና ለማገናኘት መሞከር፣ አጫጭር ማስታወሻ መያዝ፣ ፍሬ ነገሮችን ለቅሞ ማውጣትና፣ በፍጥነት መከለስ፣ ጥናቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ምን አጠናሁ ወይም ተገነዘብኩ ብሎ እራስን መጠየቅና በአእምሮ ለማውጣትና ለማውረድ ወይም ለማሰላሰል መሞከር አስፈላጊ ነው፡፡ "አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ" እንዳይሆን በጥናት ጊዜ ጭብጡን መያዝ አስፈላጊ ነው፡፡

**ሸ. የቡድን ጥናት ማዘጋጀት**

ከግል ጥናት በተጨማሪ የቡድን ጥናት ማደራጀትና ለውይይት የሚያመች ዕቅድ ማውጣት ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡ ይህ ዘዴ ጠንካራና ደካማ ጎንን ለመገምገም ከመርዳቱም በላይ የተማሪዎችን የመመርመርና የግንዛቤ አድማሳቸውን ያሰፋል፡፡ በተለይ በግል ጥናት ጊዜ ግልጽ ያልሆኑትን በመጠያየቅ በቀላሉ ለመረዳትና ጠለቅ ያለ ዕውቀት ለመጨበጥ ያስችላል፤፡ በቡድን ማጥናት በማኅበራዊ ግንኙነት ዘርፍም የሚያስገኘው ጥቅም በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡

በመጨረሻም የጥናት ፍቅር በልጆች አእምሮ ውስጥ እንዲሰርጽ በማድረግ ሂደት የቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለባቸው ሊያውቁ ይገባል፡፡

**ተግባር 7**

1. ልጆች መልካም ስነ-ምግባር እንዲያጎለብቱ የሚያስችሉ ስልቶችን ግለፁ ፡፡

2. በልጅነት ወቅት ሊጎለብቱ የሚችሉ ተገቢ ያልሆኑ ባህሪያትን በመለየት እንዴት ሊሻሻሉ እንደሚችሉ ግለፁ ፡፡

3. የልጆች ትኩረት እንዳይበታተን/ትኩረታቸዉ ወደ ትምህርቱ እንዲሆን ከቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ምን ይጠበቃል?

## 1.19 የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ መለማመጃ ጥያቄዎች

**ክፍል አንድ፡ - የእውነት-ሀሰት ጥያቄዎች**

***መመሪያ፡***የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥንቃቄ ከአነበባችሁ በኋላ ትክክል የሆኑትን **እውነት**፣ትክክል ያልሆኑትን **ሀሰት** በማለት ከጥያቄዎች በስተግራ በኩል በተሰጠዉ ቦታ ላይ ፃፉ።

________1. የጨቅላነት ዘመን ከፍተኛና ውስብስብ ራስን የማስማማት ወቅት ነው፡፡

________2. ጡት ማጥባት በሕፃኑና በእናቲቱ መካከል ጠንካራ ግንኙነት እንዲፈጠር ያግዛል፡፡

________3. ሕፃናት አካላዊ እንቅስቃሴን የሚጠቀሙት በንግግር ቦታ በመተካት እነጂ ንግግርን ለመደገፍ አይደለም፡፡

________4.እንደ ትምህርት ባለሙያዎች ስያሜ የቀዳማይ የልጅነት ወቅት የእቃ እቃ ጨዋታ ዕድሜ ነው፡፡

________5. ትኩረት የአእምሮን በአንድ ነገር ወይም ጉዳይ ላይ የማስተዋልን ችሎታ ያመለክታል፡፡

________6. ተማሪዎችን ውጤታማ ሊያደርጋቸው የሚችለው ክፍል ውስጥ የሚከታተሉት ትምህርት ብቻ አይደለም፡፡

________7. የቀዳማይ የልጅነት ወቅት ፈጣን የሆነ የቋንቋ መዳበር የሚታይበት ዘመን ነው፡፡

________8. በአገራችን በቤትም ሆነ በትምህርት ቤት አካባቢ ገኖ የሚታየው የልጆች አስተዳደግና አያያዝ ስልት ከሞላ ጎደል የግድየለሽነት ገጽታ ያለው ነው።

________9. የቀዳማይ የልጅነት እድሜ ክህሎቶችን የመማሪያ ምቹ ወቅት ነው፡፡

________10. ጨዋታ ለልጆች የማኅበራዊ ግንኙነት መሠረት ነው፡፡

**ክፍል ሁለት፡ - የምርጫ ጥያቄዎች**

***መመሪያ፡*** የሚከተሉትን የባለ አራት አማራጭ መልስ ጥያቄዎች በጥንቃቄ ከአነበባችሁ በኋላ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመክበብ መልሱ።

11. ከሚከተሉት የመዳበር ወቅቶች ውስጥ ፈጣን አካላዊ እድገት የሚታይበት የቱ ነው?

ሀ) ሕፃንነት ለ) ጨቅላነት ሐ) የቀዳማይ ልጅነት መ) ድኅራይ የልጅነት ወቅት

12. ከሚከተሉት ውስጥ የሕፃናትን ማህበራዊ ግንኙነት በማጎልበት ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱት የትኞቹ ናቸው?

ሀ) መምህራን ለ) ወላጆች ሐ) የዕድሜ አቻዎች መ) ወንድምና እህት

13. ከሚከተሉት የቀዳማይ የልጅነት ወቅት ስያሜዎች መሐከል የስነ-ባህሪ ባለሙያዎች የተጠቀሙበት ስያሜ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ) የአሰሳ ዕድሜ ለ) የቅድመ ጓድ ምስረታ ዕድሜ
ሐ) የመጠይቅ ዕድሜ መ) የቅድመ ትምህርት ቤት ዕድሜ

14. ከሚከተሉት ውስጥ ስለቀዳማይ የልጅነት ወቅት አእምሮአዊ መዳበር ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ) ነጠላ አትኩሮት ይታያል ፡፡
ለ) አካባቢያቸውን ለመረዳት ከፍተኛ ፍላጎት ያሳያሉ ፡፡
ሐ) የምክንያትና ውጤትን ግንኙነት በአግባቡ ይረዳሉ፡፡
መ) ሁሉም ነገር በሰው ነው የተሰራው ብለው ያስባሉ፡፡

15. የልጆች ስነ-ምግባር መገንቢያ ስልት የሆነው የቱ ነው?
ሀ) የደንቦች ግልፅነት
ለ) ምክንያቶችን በግልፅ ማስረዳት
ሐ) መልካም ስነ-ምግባርን ማበረታታት
መ) ሁሉም መልስ ናቸው

**ማጠቃለያ**

የልጆች ስነ-ባህሪን በአራት ምዕራፎች ውስጥ በማካተት በተለይ ለቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ሊያግዝ በሚያስችል መልኩ በዚህ ሞጁል ቀርቧል።በመጀመሪያው ምዕራፍ የስነ-ባህሪ ትርጉም፣ተፈጥሮና አካባቢ በባህሪ ላይ ያላቸው ሚና፣የልጆች ስነ-ባህሪ ትርጉምና አስፈላጊነት፣እንዲሁም የልጆች ባህሪ ሳይንሳዊ የማጥኛ ዘዴዎች በስፋት ተዳሰዋል።

በሁለተኛው ምዕራፍ ከሰው ልጅ የመዳበር ሂደት ጋር ተያያዥነት ያላቸው የቁልፍ ቃላቶች ትርጓሜ፣የመዳበር ዘርፎችና መርሆዎች፣የመዳበር መሠረታዊ እውነታዎች፣የሰው ልጅ አብይ የመዳበር ወቅቶች ተብራርተዋል ። በሶስተኛ ምዕራፍ የቅድመ-ልደት የመዳበር ወቅት ንዑሳን

ክፍሎች፤በቅድመ-ልደት የመዳበር ወቅት ተፅዕኖ የሚያስከትሉ ሁኔታዎች፤የቅድመ-ልደት የመዳበር ወቅትን ማጥናት አስፈላጊነት ተገልፀዋል።

በመጨረሻው ምዕራፍ የጨቅላነትና የሕፃንነት ወቅትን ባህሪያት በተመለከተ በምሳሌ የተደገፈ ገለጻ ተካቷል።በተለይ በዚህ ምዕራፍ በዋናነት የቀዳማይ የልጅነት ወቅት ባህርያት፤የአካል፣ የእንቅስቃሴ፣የአእምሮአዊ፣የኃይለ-ስሜት፣የማህበራዊ ግንኙነትና የስነ-ምግባር መዳበር ሂደቶች በሰፊው ተዳሰዋል።በተጨማሪም በልጅነት ዘመን የሚከሰቱ የባህሪ ችግሮች ገጽታና የማሻሻያ ዘዴዎች ተካተዋል።በምዕራፉ መገባደጃ ላይ ለልጆች ትምህርት ስኬታማነት የሚረዱ መሠረታዊ ጉዳዮች ተነስተዋል።

**ዋቢ መጻሕፍት**


Aggarwal, J.C. (1994). **Essentials of Educational Psychology**. New Delhi: Vikas Publishing House Private Ltd.

Berger, K.S. (1983).**The Developing Person through the Lifespan**. New York: Worth Publishers Inc.

Dacey, J.S. and Travers, J.F. (2004). **Human Development: Across the Lifespan** (5th ed.). Boston: McGraw-Hill Companies, Inc.

Hetherington, E.M. and Parke, R.D. (1986).**Child Psychology: A Contemporary Viewpoint** (3rd ed.). Singapore: McGraw- Hill, Inc.

Hurlock, E.B. (1980). **Developmental Psychology: A Life-Span Approach** (5th ed.) New Delhi: TATA McGraw-Hill Publishing Company Ltd.

Kaplan, P.S. (1986). **A Child's Odyssey: Child and Adolescent Development.** New York: West

Morgan, C.T., King, R.A., Weisz, J.R., and Schopler, J. (1986). **Introduction to Psychology** (7th ed.). New York: McGraw- Hill Book Company.

Papalia, D.E. and Olds, S.W. (1992). **Human Development** (5th ed.). New Delhi: TATA McGraw Publishing Company Limited.

Santrock, J.W. (2006).**Life-Span Development (**10th ed.). Boston: McGraw-Hill Companies, Inc.

ዳንኤል ዘውዴ፣ አንበሱ ቢያዝንና ፍቅሬ ባይለየኝ (1994 ዓ.ም.) **የትምህርት ጥናትና ምርምር አተገባበር፡፡** አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ፍስሃ ወልደ ሚካኤል (1990 ዓ.ም.) **የልጆች እድገትና መዳበር ስነ-ባህሪ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸውን ጠቋሚ፡፡** አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፡፡

ጥሩሰው ተፈራ (1991 ዓ.ም.) **ሕፃናትን ለመርዳትና ለመረዳት አስፈላጊ ስልቶች፡- ለመምህራንና ለወላጆች፡፡** አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ (2002 ዓ.ም.) **ከ 4- 5 ዓመት እድሜ ክልል ላሉ ሕፃናት የተዘጋጀ የሕፃናት አስተዳደግና ትምህርት አጋዥ ጽሁፍ፡፡** አዲስ አበባ (ያልታተመ)፡፡

**አባሪዎች**

**1.20 አባሪ - 1፡ የየምዕራፎቹ ማጠቃለያ መለማመጃ ጥያቄዎች መልስ**

**የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ መለማመጃ ጥያቄዎች መልስ**

**ክፍል አንድ፡ - የእውነት-ሀሰት ጥያቄዎች**

1. ሀሰት 2. ሀሰት 3. እውነት 4. ሀሰት 5. እውነት

**ክፍል ሁለት፡- የአጭር መልስ ጥያቄዎች**

6. ስነ-ባህሪ 7. መግለፅ 8. ምልከታ 9. ባህሪ 10. ሳይንሳዊ

**የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ መለማመጃ ጥያቄዎች መልስ**

**ክፍል አንድ፡ - የእውነት-ሀሰት ጥያቄዎች**

1. ሀሰት 2. ሀሰት 3. ሀሰት 4. እውነት 5. እውነት

**ክፍል ሁለት ፡ - የምርጫ ጥያቄዎች**

6. ለ 7. ሐ 8. ሀ 9. ሀ 10. መ

**የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ መለማመጃ ጥያቄዎች መልስ**

**ክፍል አንድ ፡ - የእውነት-ሀሰት ጥያቄዎች**

1. ሀሰት 2. እውነት 3. ሀሰት 4. እውነት 5. እውነት

**ክፍል ሁለት ፡- የአጭር መልስ ጥያቄዎች**

6. 20 እስከ 35 7. የፅንስ 8. ውህደ ህዋስ 9. ውህደ ህዋስ 10. ዘጠኝ

**የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ መለማመጃ ጥያቄዎች መልስ**

**ክፍል አንድ፡ - የእውነት-ሀሰት ጥያቄዎች**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1. እዉነት | 2. እውነት | 3. እውነት | 4. ሀሰት | 5. እውነት |
| 6. እውነት | 7. እውነት | 8. ሀሰት | 9. እውነት | 10. እውነት |

**ክፍል ሁለት ፡ - የምርጫ ጥያቄዎች**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 11. ሀ | 12. ለ | 13. መ | 14. ሐ | 15. መ |

## 1.21 አባሪ - 2፡ የአካላዊ እንቅስቃሴ መዳበር ምልከታ መከታተያ ቅጽ

የቅድመ መደበኛ ት/ቤቱ ስም ______________________________
የልጁ ስም ____________________________ እድሜ __________ ፆታ ____________
የመምህሩ ስም __________________________ ዓመተ ምህረት ____________________

ስለ ልጁ ምልከታውን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅፁ ውስጥ ምልከታ በሚለው ስር ይመዝግቡ፡፡

**ደረጃዎቹ፡**

1. መሻሻል የሚያስፈልገው
2. የታለመው ግብ የተገኘበት
3. ከታለመው በላይ የተገኘበት

**ማሳሰቢያ፡-** የክትትል ሰንጠረዡ በዓመቱ መጀመሪያ፣ በዓመቱ አጋማሽ እና በዓመቱ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል፡፡

| መድረሻ /ግብ/ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | በዓመቱ መጀመሪያ | በዓመቱ አጋማሽ | በዓመቱ መጨረሻ |
| 1. ጉልህ የእንቅስቃሴ ክህሎት ማዳበር | | | |
| 1.1. መሠረታዊ የእንቅስቃሴ ክህሎትን ማከናወን መቻል | | | |
| 1.2. ቀለል ያሉ የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን መቻል | | | |
| 1.3. ራስን ችሎ የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን መቻል | | | |
| 1.4. የተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን መሥራት መቻል | | | |
| 1.5. የተለያዩ እንቅስቃሴያዊ ጨዋታዎችን በተናጠልም ሆነ በሕብረት በመጫወት መደሰት መቻል | | | |
| 2. ረቂቅ የእንቅስቃሴ ክህሎት ማዳበር | | | |
| 2.1. መሠረታዊ የንጽህና አጠባበቅ እና የአመጋገብ ሥርዓቶችን መለማመድ | | | |
| 2.2. መቀስን በመጠቀም ወፍራም ወረቀቶችን መቆራረጥን መለማመድ | | | |
| 2.3. ከወረቀት የተለያዩ ነገሮችን መሥራት መለማመድ | | | |
| 2.4. ስዕሎችን መሣልና ቀለም መቀባትን መለማመድ | | | |
| 2.5. ከፔፐር ማሼ፣ ከፕላስትሊን /ከጭቃ/ የተለያዩ ቅርፆችን መሥራት መለማመድ | | | |
| 2.6. የዓይንና የእጅ ቅንጅትን ሊያዳብሩ የሚችሉ ጨዋታዎችን መጫወት መቻል | | | |

### 1.22 አባሪ - 3፡አካባቢን የማወቅና የመረዳት ግንዛቤ መዳበር ምልከታ መከታተያ ቅጽ

የቅድመ መደበኛ ት/ቤቱ ስም ______________________________
የልጁ ስም __________________________ እድሜ __________ ፆታ __________
የመምህሩ ስም __________________________ ዓመተ ምህረት ____________________

ስለ ልጁ ምልከታውን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅፁ ውስጥ ምልከታ በሚለው ስር ይመዝግቡ፡፡

**ደረጃዎቹ፡**

1. መሻሻል የሚያስፈልገው
2. የታለመው ግብ የተገኘበት
3. ከታለመው በላይ የተገኘበት

**ሳሰቢያ፡-** የክትትል ሰንጠረዡ በዓመቱ መጀመሪያ፣ በዓመቱ አጋማሽ እና በዓመቱ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል፡፡

| መድረሻ /ግብ/ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | በዓመቱ መጀመሪያ | በዓመቱ አጋማሽ | በዓመቱ መጨረሻ |
| 1. አካባቢን መፈተሽ፣ ማወቅና መረዳት | | | |
| 1.1. በቤታቸውና በቅድመ መደበኛ ት/ቤት የሚገኙ ሰዎችና ቁሳቁሶችን መለየት መቻል | | | |
| 1.2. ስለተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ነገሮች ግንዛቤ ማዳበር | | | |
| 1.3. በአካባቢያቸው ስለሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ቦታዎች መረዳት መቻል | | | |
| 1.4. ሀገርን የማወቅና የመውደድ ዝንባሌ ማሣደር መጀመር | | | |
| 2. የስሜት ሕዋሳቶቻቸውን በመጠቀም በደረጃቸው ቀላል የሆኑ ሙከራዎችን በማከናወን የነገሮችን ባህሪ መረዳት | | | |
| 2.1. በስሜት ሕዋሳቶቻቸውና በቋንቋ አማካኝነት የነገሮችን ባህሪ መረዳት መቻል | | | |
| 2.2. በደረጃቸው ቀላል የሆኑ ሙከራዎችን ማከናወን መቻል | | | |
| 3. በደረጃቸው ከጤናና ከደህንነት ጋር የተያያዙ ጠቃሚ ልምዶችን መተግበር | | | |
| 3.1. የግልና የአካባቢ ንጽህናን በመጠበቅ አካባቢን የመንከባከብ ዝንባሌን ማዳበር | | | |
| 3.2. ራስንና ሌሎችን በአካባቢያቸው ከሚገኙ አደገኛ ነገሮች መከላከልን መለማመድ | | | |

### 1.23 አባሪ - 4፡የማኅበራዊና ስሜታዊ ክንዋኔ መዳበር ምልከታ መከታተያ ቅጽ

የቅድመ መደበኛ ት/ቤቱ ስም ____________________

የልጁ ስም ____________________ እድሜ __________ ፆታ __________

የመምህሩ ስም ____________________ ዓመተ ምህረት ____________________

ስለ ልጁ ምልከታውን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅፁ ውስጥ ምልከታ በሚለው ስር ይመዝግቡ፡፡

**ደረጃዎቹ፡**

1. መሻሻል የሚያስፈልገው
2. የታለመው ግብ የተገኘበት
3. ከታለመው በላይ የተገኘበት

**ማሳሰቢያ፡-** የክትትል ሰንጠረዡ በዓመቱ መጀመሪያ፣ በዓመቱ አጋማሽ እና በዓመቱ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል፡፡

| መድረሻ /ግብ/ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | በዓመቱ መጀመሪያ | በዓመቱ አጋማሽ | በዓመቱ መጨረሻ |
| 1. ማንነትን የመገንዘብና ራስን የመርዳት ክህሎትን ማዳበር | | | |
| 1.1. ራስን ከሌሎች ሰዎች ለይቶ ማወቅና መግለጽ መቻል | | | |
| 1.2. ራስን ችሎ የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን መቻል | | | |
| 2. ከሰዎች ጋር ከሚኖራቸው ግንኙነት ተቀባይነት ያላቸውን ባህርያት መረዳትና በተግባር የማሣየት ክህሎትን ማዳበር | | | |
| 2.1. ተቀባይነት ያላቸውን ባህሪያት መለየትና መተግበርን መለማመድ | | | |
| 2.2. በጨዋታና በሌሎች የሕብረት ተግባራት በተገቢው መልኩ መሣተፍ መቻል | | | |
| 3. ስሜትን በተገቢው መንገድ መግለጽና የሌሎችን ሰዎች ስሜት መረዳትና የመጋራት ዝንባሌን ማዳበር | | | |
| 3.1. ሌሎችን በማይጎዳ መልኩ የራስን ስሜት በአግባቡ መግለጽን መለማመድ | | | |
| 3.2. ሌሎች ሰዎች የሚገኙበትን ስሜት መረዳትና መጋራትን መለማመድ | | | |